# ሀገር አቀፍ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ

መስከረም 2006 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

# ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ ..........1
2. የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዓላማዎች ..........3
2.1 አጠቃላይ ዓላማ ..........3
2.2 ዝርዝር ዓላማዎች ..........3
3. የኢንስፔክሽን መሪ መርሆዎች ..........3
4. የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች /Focus Areas of Inspection/ ..........4
5. ግብዓት (Input) ..........5
5.1 የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች /Focus Areas of Inspection/ ..........5
5.1.1 የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች ..........5
5.1.2 ምቹ የመማሪያ አካባቢ ..........7
5.1.3 የትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴቶችና ዕቅዶች ..........7
6. ሂደት (Process) ..........8
6.1 መማር-ማስተማር፡- ..........8
6.1.1 መማር ..........8
6.1.2 ማስተማር ..........9
6.2 ሥርዓተ ትምህርት ..........11
6.3 ምዘና ..........11
6.4 ክትትልና ግምገማ ..........12
6.5 የትምህርት ቤት፣ የወላጆችና የማህበረሰብ አጋርነት ..........13
7. ውጤት (Output) ..........13
7.1 ትምህርት ቤቱና ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት ..........13

7.2 የተማሪዎች ግለ-ስብዕና ........................................................................ 14
7.3 የመምህራንና የትምህርት አመራር ግለ - ስብዕና ............................................ 15
7.4 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ ..................................................... 15
8. የኢንስፔክሽን ሂደት፡- ............................................................................... 16
8.1 ትምህርት ቤቶች ለኢንስፔክሽን እንዴት ይመረጣሉ? ......................................... 16
8.2 የኢንስፔክሽን ቡድን አመሰራረት፡- ............................................................... 16
8.3 ከኢንስፔክሽን በፊት ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት፡- ........................ 17
8.4 ኢንስፔክሽንና የትምህርት ቤት ግለ-ግምገማና ደረጃ ምደባ ፡- ............................ 17
8.5 የኢንስፔክሽን ሥራ እንዴት ይጀመራል? ..................................................... 17
8.6 ኢንስፔክተሮች እንዴት መረጃ ይሰበስባሉ? .................................................. 18
8.7 ውሳኔ ላይ መድረስ፡- .................................................................................. 18
8.8 ለደረጃ ውሳኔ የመለኪያዎች ክብደት አሰጣጥ፡- ................................................ 18
8.9 የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፡- .............................................................................. 19
8.10 ግብረ-መልስ መስጠት፡- ............................................................................. 20
8.11 የፅሁፍ ሪፖርት ፡- ..................................................................................... 20
8.12 ክትትል ስለማድረግ፡- ................................................................................. 20
8.13 የቅሬታ አቀራረብ ...................................................................................... 21
9.የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነ-ምግባር ................................................................ 21
ተቀጽላ-1 የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ስታንዳርዶችና አመልካቾች.....................23
ተቀጽላ-2፡ ገላጮች /Descriptors/ ................................................................... 36
ተቀጽላ 3 የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ቀመር ምሳሌ .......................................................71
ተቀጽላ 4 የኢንስፔክሽን ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ.......................................................75

# 1 መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትን ማሻሻል ዋነኛ የቅድሚያ ትኩረት ጉዳይ አድርጐ በመስራት ላይ ይገኛል። በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ተደራሽነትን ከማረጋገጥ አኳያ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል። በሌላ በኩል የትምህርት ተደራሽነትን ከማረጋገጥ ጐን ለጐን የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ በትምህርት ቤቶች የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ተግባር በሚፈለገው ደረጃ በማከናወን የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል እንደ አንድ ቁልፍ ጉዳይ በመለየት ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ መርሃ ግብር በመቅረጽ በሀገራችን በመተግበር ላይ ይገኛል። በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ መርሃ ግብሩ ውስጥ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን እንደ አንድ አካል ተወስዶ መተግበር እንደሚያስፈልግ ያመላክታል።

በዓለም ላይ ባለፉት 30 ዓመታት ትምህርት ቤቶች ራሳቸውን በራሳቸው በኃላፊነትና ተጠያቂነት ስሜት እንዲያስተዳድሩ እና እንዲመሩ የማድረግ ዝንባሌ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ ላይ ነው። በዚህ ረገድ እየታየ ያለው መሻሻል የተማሪዎችን ውጤት ከማሳደግ ጋር ቀጥታ ተያያዥነት ያለው መሆኑን ያሳያል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአንድ በኩል በትምህርት ቤቶች ተጠያቂነት እና ግምገማ፣ በሌላ በኩል በትምህርት ቤቶች የስራ አፈፃፀም መካከል ጠንካራ ግንኙነት መኖሩን ጥናቶች ያሳያሉ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የብቃት ደረጃ ላይ የሚገኝ ትምህርት ቤት የተሻለ ትምህርት ቤት ሆኖ የቀጠለበትን ሁኔታ አስመልክቶ Mckinsey (2010) በፃፈው ሪፖርት ከታች የተመለከቱትን ሁለት ነጥቦች በመለየት አስፍሯል፦

- ትምህርት ቤቶች ተፈላጊውን (Minimum) የብቃት ደረጃ እንዲያሟሉ ለማድረግ በሂደት የሚከናወኑ ተግባራት ትምህርት ቤቶችን ከደካማ /Poor/ የብቃት ደረጃ አፈፃፀም ወደ ደህና /Fair/ ደረጃ የሚያሳድግ መሆን አለበት።
- የትምህርት ቤቶች እና መምህራንን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚካሄደው ዋና የማስተካከያ እርምጃ አወሳሰድ ሂደት የትምህርት ሥርዓቱን ደረጃ ከደህና /Fair/ ወደ ጥሩ /Good/ ደረጃ የሚያሸጋግር መሆን አለበት።

ኢንስፔክሽን በነፃ እና ውጫዊ በሆነ አካል የሚካሄድ ግምገማ ነው። ኢንስፔክሽን የመማር ማስተማሩን ሂደት ትምህርት ቤቶች በምን ደረጃ እየተገበሩት እንደሆነ፣ የሚሰጠው የትምህርት ጥራት ደረጃ እና ተማሪዎች ያስመዘገቡትን ውጤት በተጨባጭ መረጃና ትክክለኛ አካሄድ የምንመረምርበት ሂደት ነው። በዚህም መሠረት ትምህርት ቤቶች የተቀመጠላቸውን ተፈላጊ የትምህርት ጥራት የብቃት ደረጃ በማስጠበቅ ለሚያሳዩት መሻሻል እውቅና ለመስጠትና እንዲሁም ላሳዩት የአፈፃፀም ጉድለት የተጠያቂነት ስር¯ƒ" ለማስፈን ከሚረዱ ቁልፍ መሳሪያዎች ኢንስፔክሽን አንዱ ነው።

በአሁኑ ወቅት በክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ በዞን/ክፍለ ከተማ የትምህርት ፅ/ቤቶች እና በወረዳ የትምህርት ጽ/ቤቶች በሚገኙ አደረጃጀቶች የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተቋቋሙ የሥራ ክፍሎች ቢኖሩም በትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን ሥራ በለጋ የዕድገት ደረጃ ላይ ይገኛል። በትምህርት ቤቶች ደረጃ የትምህርት ቤት ግለ-ግምገማና የደረጃ ምደባ ማድረግ እየዳበረ ያለ ልምድ ቢሆንም በውጭ አካል ከሚደረግ ግምገማና ደረጃ ምደባ ጋር የተዛመደ አልነበረም። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ያለው ኢንስፔክሽን ወይም የጥራት ኦዲት በአቀራረቡ ከክልል ክልል የሚለያይና በአገር አቀፍ ደረጃ በት/ቤቶች መካከል ያለውን ብቃት በመለካት ት/ቤቶችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመፈረጅና በደረጃ ለማስቀመጥ የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም።

ትምህርት ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ቤቶችን ኢንስፔክሽን ወጥ በሆነ መንገድ የሚካሄድበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽንን በዳይሬክቶሬት ደረጃ አቋቁሟል። በዚሁ መሠረት የኢንስፔክሽን ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ያዘጋጀ ሲሆን ማዕቀፉ በትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን በምን መልክ መካሄድ እንዳለበት አጠቃላይ ሁኔታዎችንና በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚካሄደው የኢንስፔክሽን ሥራ ወጥ በሆነ መንገድ እና በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ የት/ቤቶችን ደረጃ አውጥቶ መፈረጅና ለመደገፍ በሚረዳ አግባብ መከናወኑን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልክ ተዘጋጅቷል። ማዕቀፉ ኢንስፔክሽን የሚካሄድባቸውን የትኩረት መስኮች፣ ኢንስፔክተሩ/ሯ የሚያተኩሩባቸውን ንኡስ የትኩረት መስኮች፣ የኢንስፔክሽን ሂደት የሚያሳይ ማጠቃለያ እና በኢንስፔክሽን ሥራ ላይ ከኢንስፔክተሮች የሚጠበቁ የሥነ ምግባር መርሆዎችን በዋናነት ይዟል።

# 2 የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዓላማዎች

## 2.1 አጠቃላይ ዓላማ

የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዋና ዓላማ የትምህርት ጥራትንና ውጤታማነትን በማረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተማሪዎችን ውጤትና ሥነ-ምግባር ማሻሻል ነው።

## 2.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- ትምህርት ቤቶች የሚጠበቅባቸውን ተፈላጊ (Minimum) የአፈጻጸም ደረጃ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ፣
- ት/ቤቶችን በደረጃ በመመደብና ሞዴል ት/ቤቶችን በመለየት የጉድኝት ማዕከላት ሆነው ሌሎችን እንዲያበቁ ማስቻል፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ መርሃ ግብር በተለይም የትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ ግብሮች አተገባበርና ውጤታማነትን በመፈተሽ ለፖሊሲ አውጭዎችና ለትምህርት ባለሙያዎች መረጃ ለመስጠት፣
- በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ስራ ወላጆች፣ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ትምህርት ቤታቸው ስላለበት ደረጃ መረጃ ለመስጠትና መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ተሳትፏቸውን ለማጎልበት፣
- ትምህርት ቤቶች ሶስቱን የልማት ሰራዊት አቅሞች/ የድርጅት፣ የመንግስትና የህዝብ ክንፎች/ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ተጣምረው በትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ ብቃት፣ አግባብነትና ጥራት ላይ መረጃ በመስጠት ተሳትፏቸውን በማጎልበት የተማሪዎችን ውጤትና ስነምግባር እንዲያሻሽሉ ለማድረግ፣
- የትምህርት ቤቶች መሻሻልና አፈጻጸምን አስመልክቶ በየደረጃው የተጠያቂነት ስርአት ለማስፈን፣

# 3 የኢንስፔክሽን መሪ መርሆዎች

የኢንስፔክሽን ሂደት የሚከተሉትን መሠረታዊ መሪ መርሆዎችን ይከተላል።እነርሱም፡-

- ነጻ ወይም የት/ቤቱ አካል ባልሆኑ የትምህርት ኢንስፔክተሮች ይካሄዳል፣
- የአንድን ትምህርት ቤት አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ለመገምገም ተጨባጭ፣ ወጥነትናቀጣይነት ባላቸው መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ይካሄዳል፣

- ግምገማው ሁሉንም ት/ቤቶች ባካተተ መልኩ በተቀመጡት ግልጽ ስታንዳርዶችና መስፈርቶች መሠረት የሚካሄድ እንጂ የኢንስፔክተሮች ግላዊ አመለካከት ፈጽሞ አይንጸባረቅበትም ፣
- ገንቢ እና ለጉዳዮች ትኩረት የሚሰጥ ፤የተከናወኑ መልካም ተግባራትን የሚያበረታታና እጥረቶችን ለይቶ በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ የሚሰጥበት ተግባር ነው።
- የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ስብእና በማክበር ይከናወናል፣
- የግምገማ ተግባራት ት/ቤቶች እንደ ተቋም ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ያተኮረ እንጂ በግለሰቦች የሥራ አፈጻጸም ላይ መሆን አይገባውም፣

# 4 የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች /Focus Areas of Inspection/

የኢንስፔክሽን ርዕሰ ጉዳይ ከአምስት የትኩረት መስኮች የተውጣጣ ነው። እነዚህ አምስት የትኩረት መስኮች አንድ ትምህርት ቤት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብአቶች፣ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲሁም የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ የብቃት ደረጃ እና ውጤታማነት ከሚወስኑ የተማሪዎች ውጤትና ሥነ-ምግባር መሻሻል ጋር የተያያዙ ናቸው። የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች ከትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ማእቀፍ እና ግለ-ግምገማ ቅጽ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው።

አራቱ የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች ከትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ ግብር አብይ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም ከመማር-ማስተማር፣ ምቹ የትምህርት አካባቢ፣ የትምህርት ቤት አመራር እና የህብረተሰብ ተሳትፎ ጋር በስፋት የሚዛመዱ ሲሆን ከነዚህ በተጨማሪ የተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር መሻሻል ለኢንስፔክሽን ሥራ እንደ አምስተኛ ቁልፍ የትኩረት መስክ ተደርጎ ይወሰዳል።

በኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች ውስጥ ከተካተቱት የመጀመሪያዎቹ አራቱ ንዑሳን የትኩረት መስኮች (Aspects) እና ስታንዳርዶች በትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር ማዕቀፍ ውስጥ በእያንዳንዱ ዐቢይ ርእስ ጉዳይ ስር ከተቀመጡት ንዑሳን ጉዳዮች እና ስታንዳርዶች ጋር በስፋት የተገናኙ ናቸው። ስታንዳርዶቹ በሀገራችን የሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ተፈላጊ /Minimum/ የብቃት ደረጃዎችን በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን የትምህርት ቤት የትኩረት መስኮች ከግብአት፣ ሂደት እና ውጤት መስተጋብር አንፃር በአምስት አበይት ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

| መለኪያዎች | የትኩረት መስክ |
|---|---|
| • ግብዓት/Input/ | የትኩረት መስክ 1 - የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች<br>የትኩረት መስክ 2 - ምቹ የመማሪያ አካባቢ |
| • ሂደት /Process/ | የትኩረት መስክ 3 - መማርና ማስተማር<br>የትኩረት መስክ 4- ትምህርት ቤቱ ከወላጆች እና ከህብረተሰቡ ጋር ያለው ግንኙነት |
| • ውጤት/Output/ | የትኩረት መስክ 5 - የተማሪዎች ውጤትና ሥነ-ምግባር |

የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮችን የተመለከተ ይዘት ከዚህ በታች የቀረበ ሲሆን እያንዳንዱ ዐቢይ የትኩረት ጉዳይ በውስጡ አንድ እና ከአንድ በላይ ንኡሳን የትኩረት መስኮችን ይዟል። በአንፃሩ ከእያንዳንዱ ንኡሳን የትኩረት መስኮች ስር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡ ስታንዳርዶች ይገኛሉ። እንዲሁም እያንዳንዱን ስታንዳርድ ትምህርት ቤቱ ማሟላት አለማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አመልካቾች /ጠቋሚዎች/ በዝርዝር ተያይዘው ቀርበዋል።

# 5 ግብዓት (Input)

## 5.1 የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች /Focus Areas of Inspection/

### 5.1.1 የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች

**ስታንዳርድ** 1

ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል።

**አመልካቾች ፡-**

- ትም/ቤቱ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንፃዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ባካተተ መልኩ (በቂ ብርሃን፣ስፋት፣ወለል ወዘተ) የታነፁና የተሟሉ ናቸው፣
- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍ ፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ የመምህሩ/ሯ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን፣ ብሬይል አሟልቷል፣
- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የስፖርት ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።

- በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ ገዥ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት ወዘተ እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣

## ስታንዳርድ 2

ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል።

## አመልካቾች፡-

- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ቤት ጥቅል በጀት /Block grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤
- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የት/ቤት ድጎማ በጀት /School grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤
- ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣
- ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል፣
- ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት አሰባስቧል።
- ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ዶክመንቶች አሉት፣

## ስታንዳርድ 3

ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል።

## አመልካቾች፡-

- ሁሉም የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራንና መምህራን የሙያ ፈቃድና ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት አላቸው፣
- ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት፣
- ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ /Guidance and Counselling/ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ አለው፣
- ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን አሉት።

### 5.1.2 ምቹ የመማሪያ አካባቢ

**ስታንዳርድ 4**

ትምህርት ቤቱ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ የመማር - ማስተማር አካባቢ ፈጥሯል።

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣
- ትምህርት ቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ አለው፣
- በትምህርት ቤቱ  የሚገኙ ህንፃዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው፣
- የትምህርት ቤቱ ግቢ በአጥር ተከብሯል፣
- ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፣
- በትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር ተሟልቷል።
- ትምህርት ቤቱ በቂ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው።

**ስታንዳርድ 5**

ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል ግብዐት፣አደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት ተፈጥሯል።
- በትምህርት ቤቱ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦችን ተልዕኮዎችን የተገነዘበና ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምንርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል።
- በትምህርት ቤቱ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል።

### 5.1.3 የትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴቶችና ዕቅዶች

**ስታንዳርድ 6**

ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣  ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት።

**አመልካቾች፡-**

- የትምህርት ቤቱ አመራር ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አዘጋጅቷል፤

**ስታንዳርድ 7**

ትምህርት ቤቱ አሳታፊ የት/ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፣

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለይቷል፣
- ትምህርት ቤቱ የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቷል፣

# 6 ሂደት (Process)

## 6.1 መማር-ማስተማር፡-

### 6.1.1 መማር

**ስታንዳርድ 8**

የተማሪዎች መማርና ተሳትፎ ጎልብቷል።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች የተሰጧቸውን ሥራዎች በትጋት ይሰራሉ፣
- ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅና መልሶችን ለመመለስ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፣
- ተማሪዎች በ1 ለ 5 (ኔትወርክ) አደረጃጀት ተደራጅተው በትምህርታቸው ይረዳዳሉ፣
- ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ነው፣
- ተማሪዎች በህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል ተደራጅተው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ውሳኔ በመስጠት ተሳትፎ እያደረጉ ነው።

**ስታንዳርድ 9**

ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች የትምህርት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣
- ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር መፍጠር፣መመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች መፍታት ችለዋል።
- ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ሁሉ ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ፣
- ተማሪዎች በፈተና/ምዘና ፣ የሚፈፀም ኩረጃ ጸያፍ መሆኑን ተገንዝበዋል፣

**ስታንዳርድ 10**

ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው በጎ አመለካከት አላቸው።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ በሚሰጣቸው አገልግሎት ረክተዋል።
- ት/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ድጋፍ አድርገዋል፣
- ተማሪዎች መምህሮቻቸውን በአግባቡ መገምገም ችለዋል፣
- ተማሪዎች ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት ይሰጣሉ፣
- ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ አድርገዋል፣

### 6.1.2 ማስተማር

**ስታንዳርድ 11**

*መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደ፣ በአመቺ የትምህርት መርጃዎች የተደገፈ እና ከፍተኛ የትምህርት ውጤትን ለማስገኘት አልሞ የተዘጋጀ ነው።*

**አመልካቾች፡-**

- *የመምህራን የትምህርት እቅድ የሚያስተምሩትን ትምህርት አላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ስነ ዘዴ… ወዘተ በአግባቡ አካቷል፣*
- *መምህራን የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ አውለዋል፣*
- *መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ ፣ ፕላዝማ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም ሰጥተዋል፣*
- *መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ቤተ-ሙከራ በመጠቀም ሰጥተዋል፣*
- *መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎቻቸው የአካባቢ ቁሳቁስ ተጠቅመው የፈጠራ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታታሉ፣*
- *መምህራን ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸውና በውጤታቸው እንዲሻሻሉ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እገዛ አድርገዋል።*

**ስታንዳርድ 12**

*መምህራን የሚስተምሩትን የትምህርት ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ።*

**አመልካቾች፡-**

- *መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት በቂ እውቀትና ክህሎት አላቸው፣*
- *መምህራን ለተማሪዎች በሚመጥን ቋንቋ እና አቀራረብ ይዘቱን ቀለል አድርገው ያቀርባሉ፡*
- *መምህራን በትምህርቱ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦችን ለተማሪዎች በግልጽና አብራርተው ያቀርባሉ፣*

## ስታንዳርድ 13

የት/ቤቱ አመራርና መምህራን ለሁሉም ተማሪዎች ተስማሚና ዘመናዊ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ጎልብቷል።

**አመልካቾች፡-**

- መምህራን ተማሪዎች በትምህርታቸው ተመራማሪ፣ ፈጣሪ፣ ችግር ፈቺ እና ራሳቸውን የሚመሩ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፣
- የትምህርት ቤቱ አመራር ዘመናዊና አሳታፊ የመማር-ማስተማር ስነ ዘዴ በት/ቤቱ እንዲተገበር ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፣
- መምህራን ተማሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በጥንድ፣ በቡድን እና በግል ትምህርታቸውን እንዲማሩ አድርገዋል፣
- መምህራን ለሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣
- መምህራን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣
- መምህራን የመማር ማስተማሩን ችግር ለመፍታት የተግባር ምርምር አካሂደዋል።

## ስታንዳርድ 14

ትምህርት ቤቱ ለሴቶችና እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።

**አመልካቾች፡-**

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎች ትምህርት ቤቱ መዝግቦ ይዟል፤
- ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣
- ትምህርት ቤቱ የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣

## ስታንዳርድ 15

መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር /CPD/ ተግባራዊ አድርገዋል።

**አመልካቾች፡-**

- ነባር መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ቤቱን የመማር ማስተማር ችግር ለመፍታት የሚያስችል ችግሮችን በቅደም ተከተል ለይተው ሞጁል አዘጋጅተው ቢያንስ በዓመት ለ60 ሰዓት በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ላይ ተሳትፈዋል፣

- አዲስ ጀማሪ መምህራን አማካሪ መምህራን ተመድበውላቸው የሙያ ትውውቅ መርሃ ግብር /Induction Course/ አጠናቀዋል፣

**ስታንዳርድ 16**

የትምህርት ቤቱ አመራር፣ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልማት ሠራዊት በመደራጀት በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው።

**አመልካቾች፡-**

- የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ተማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው የትምህርት ልማት ሰራዊት በመገንባት ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መልክ ተወጥተዋል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፣ እርስ በእርስም በውስጥ ሱፐርቪዥን አማካኝነት ተገነባብተዋል።
- የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጥሩ ስነ ምግባር የታነፁ፣ ለሙያቸው ተገቢ ክብር ያላቸው፣ትምህርት ቤቱን ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑ ናቸው፣

## 6.2 ሥርዓተ ትምህርት

**ስታንዳርድ 17**

ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው ፣ አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ መሆኑን መምህራን ይገመግማሉ፣ግብረ መልስ ይሰጣሉ፣ ያሻሽላሉ።

**አመልካቾች፡-**

- መምህራን በሥራ ላይ ያለውን ሥርዓተ ትምህርት ጠንቅቀው ያውቃሉ፣
- መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአገር አቀፍና በክልል የተዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርቶችን ያገናዘበ ነው፣
- መርሃ-ትምህርቶቹና ሌሎች የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች አሳታፊና ከተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃና ፍላጎት ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው ግብረ መልስ ተሰጥቶባቸዋል፣

## 6.3 ምዘና

**ስታንዳርድ 18**

ተማሪዎች በትክክል ተመዝነዋል፣ አስፈላጊው ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ የሚዘጋጅ ምዘና ስርአተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ በቢጋር /Table of Specifications/ የተዘጋጀ ነው፣
- ተማሪዎች በክልል/ከተማ አስተዳደር፣በዞን/ክፍለ ከተማ በወረዳና በጉድኝት ማዕከል በሚዘጋጁ ፈተናዎች ይመዘናሉ፣
- መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለመለካት በተቀመጠው ዝቅተኛ የመማር ብቃት /MLC/ መሠረት የንድፈ ሃሳብና የተግባር ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ፣
- መምህራን የተማሪዎችን ውጤት በመተንተን ድጋፍ ሰጥተዋል፣
- መምህራን ተማሪዎች ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ ግብረ-መልስ በመስጠት ድጋፍ ያደርጋሉ፣
- ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን ውጤት ለወላጆች በማሳወቅ ግብረ መልስ ይቀበላል።

## 6.4 ክትትልና ግምገማ

**ስታንዳርድ** 19

የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች ያቀዷቸው እቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላሉ።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ ማህበረሰቡ የተደራጁ የትምህርት ልማት ሰራዊት እቅዶች በአግባቡ መታቀዳቸውንና መከናወናቸውን ይከታተላል፣ለችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፣
- የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራምን አተገባበርን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣
- የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ኮሚቴ በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የተዘረጉ ስልጠናዎችን አፈፃፀማቸውንና መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች እየለየ ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣
- የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደትና የክበባት ዕቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣
- ት/ቤቱ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አካላትን ያበረታታል፣ ዕውቅና ይሰጣል፣

**ስታንዳርድ** 20

ትምህርት ቤቱ የሰው ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል።

**አመልካቾች፡-**

- ት/ቤቱ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፣
- መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ተመድበው ያስተምራሉ፣
- ርዕሰ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ ተመድበው ይሰራሉ፣
- በት/ቤቱ ያሉ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች እና ተጨማሪ ግብዓቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ውለዋል፣
- የት/ቤቱ በጀት ቅድሚያ ለተሰጣቸው የትምህርት ቤት መሻሻል እቅድ ላይ በተቀመጡና አግባብነት ያላቸው አካላት በወሰኑት መሠረት በተገቢ መንገድ ሥራ ላይ ውሏል።

## 6.5 የትምህርት ቤት፣ የወላጆችና የማህበረሰብ አጋርነት

### ስታንዳርድ 21

ትምህርት ቤቱ ከተማሪ ወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው።

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ ወላጆች በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤ በትምህርት ቤትና በክፍል ደረጃ ወላጆች ትርጉም ያለው ተሳትፎ በተደራጀ መልኩ እንዲያደርጉ ያደርጋል።
- ትምህርት ቤቱ በየወቅቱ ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበልና ውጤት፣ ባህርይ፣ የፋይናንስ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃ ይሰጣል፣ ግብረ መልስም ይቀበላል፣
- ወላጆች ልጆቻቸው በቤት ውስጥ በትምህርታቸው እንዲበረታቱ ያግዛሉ፣
- ወላጆች በወላጅ፣ተማሪ፣ መምህር ህብረት(ወመህ/ወተመህ) እንቅስቃሴ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣
- ትምህርት ቤቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ በአንጻራዊነት የልህቀት ማዕከል በመሆን ያገለግላል፣
- ወላጆች በትምህርት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም መርካታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ፣

# 7 ውጤት (Output)

## 7.1 ትምህርት ቤቱና ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት

### ስታንዳርድ 22

ትምህርት ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት/Internal Efficiency/ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ተደርጓል፣
- ትምህርት ቤቱ የጥቅል ተሳትፎ ዕቅዱን አሳክቷል፣
- ትምህርት ቤቱ የንጥር ተሳትፎ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል፣
- የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ጾታዊ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል።፣
- የትምህርት ቤቱ መጠነ ማቋረጥ በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል፣
- የትምህርት ቤቱ መጠነ መድገም በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል።

**ስታንዳርድ 23**

የተማሪዎች የክፍል ፣ የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች ከሚጠበቀው ሃገራዊና ክልላዊ መመዘኛ ጋር ሲነፃፀር ተሻሽሏል።

**አመልካቾች፡-**

- ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣
- ትምህርት ቤቱ ለሁሉም ሴት ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣
- ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣
- የተማሪዎች የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች በትምህርት ቤቱ ዕቅድ መሰረት ተሳክቷል፣

## 7.2 የተማሪዎች ግለ-ስብዕና

**ስታንዳድ 24**

ተማሪዎች በስነ ስርዓት የታነጹ፣ መልካም እሴቶችና ባህልን የተላበሱ፣አካባቢን የመንከባከብ ሃላፊነት የሚሰማቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።

**አመልካቾች**

- ተማሪዎች በስነ ምግባር የታነጹ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያከብሩ፣እርስ በርስ የሚከባበሩ፣ የሚተጋገዙና ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚታገሉ ሆነዋል፣
- ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ንብረት ተንከባክበዋል፣

- ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን እሴቶች፣ደንቦችና መመሪያዎችን አውቀው ስራ ላይ በማዋል ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል።
- በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች መካከል የመቻቻልና ልዩነትን በውይይት የመፍታት ባህል ዳብሯል፣
- ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል።

## 7.3 የመምህራንና የትምህርት አመራር ግለ - ስብዕና

### ስታንዳርድ 25

በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ተፈጥሯል፣ ኪራይ ሰብሳቢነትን የመታገልና የተጠያቂነት ስሜት ዳብሯል ።

### አመልካቾች፡-

- የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩና ተግባቢ በመሆናቸው የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት አጎልብቷል፣
- በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣
- የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል።

## 7.4 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ

### ስታንዳርድ 26

ትምህርት ቤቱ ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል ፣

### አመልካቾች፡-

- ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣
- ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በመጨመሩ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል፣

# 8 የኢንስፔክሽን ሂደት፡-

## 8.1 ትምህርት ቤቶች ለኢንስፔክሽን እንዴት ይመረጣሉ?

ትምህርት ቤቶች ለኢንስፔክሽን ሥራ በናሙናነት የሚመርጡባቸው አካሄዶች ሁሉንም ትምህርት ቤቶች በፍትሃዊነት ለማሳተፍ እንዲቻል አስተዳደራዊ መዋቅር፣ ሥነ-ምድራዊ አቀማመጥ፣ገጠር እና ከተማን እና የትምህርት ቤቶች የብቃት ደረጃን ማዕከል በማድረግ ይሆናል። አመራረጡም እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ሁሉንም የትምህርት እርከኖች በማመጣጠን ካሉት ተቋማት በመጀመሪያው ዓመት 20%፣ በሁለተኛው ዓመት 40% እና በሶስተኛው ዓመት 40% የሆኑትን በመውሰድ የኢንስፔክሽን ሥራ እንዲከናወን ይደረጋል። ስብጥሩም የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑትን ጨምሮ

- ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ/መሰናዶ ትምህርት ቤቶች፣
- አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች/መዋዕለ ህጻናት/
- አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት በየደረጃው የሚታዩ ይሆናል።

በየዓመቱ ኢንስፔክሽን የሚደረግባቸው ትምህርት ቤቶች ናሙና የሚመረጡት በክልል ትምህርት ቢሮ፣ በዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መመሪያ/ጽ/ቤት እና በወረዳ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት በጋራ በመሆን ይሆናል። ለድጋፍና ክትትል ያመቸ ዘንድ የጋራ የኢንስፔክሽን ሥራ የሚካሄድባቸውን ተቋማት ሙሉ መረጃ እና የጊዜ ሰሌዳ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ለትምህርት ሚኒስቴር በወቅቱ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። ትምህርት ሚኒስቴርም እንደ አስፈላጊነቱ ተቋማትን የሚያይበት አግባብ ሲፈጠር ከሚመለከተው ክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጋር በጋራ ወይም በተናጠል የክትትልና ድጋፍ/ የኢንስፔክሽን ሥራ ያከናውናል።

በኢንስፔክሽን ወቅት አንድ ትምህርት ቤት በአጠቃላይ ውጤት መመዘኛውን ካላሟላ ማለትም ከደረጃ 3 በታች የተገኘ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ በድጋሚ ይታያል ።

## 8.2 የኢንስፔክሽን ቡድን አመሰራረት፡-

የክልል ትምህርት ቢሮ የዞን/የክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ/ጽ/ቤት እና ወረዳ ት/ቤቶች ጽ/ቤት ትምህርት ቤቶችን ግምገማ ሲያካሂዱ ቢያንስ ሁለት አባላት ያለው የኢንስፔክሽን ቡድን በማዋቀር ለሶስት ወይም ለአራት ቀናት በተቋሙ ስራዎችን ሲያከናውኑ ይቆያሉ። የወረዳ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤቶች በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሠጠውን ትምህርት ጥራት የማስጠበቁን ሂደት በአግባቡ መከናወኑን ያስተባብራሉ። የሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን ስርዓት ሲዘረጋ የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት የራሱን የኢንስፔክሽን መዋቅር ያዘጋጃል።

## 8.3 ከኢንስፔክሽን በፊት ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት፡-

የኢንስፔክሽን ስራ የሚከናወንባቸው ት/ቤቶች ከሁለት ሳምንት በፊት እንዲያውቁ ይደረጋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከታች የተመለከቱትን መረጃዎች አስቀድመው እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡-

- የትምህርት ቤት ግለ-ግምገማ፣ የት/ቤት ደረጃ ምደባ፣
- የአንድ ዓመት ዕቅድና እና የሦስት ዓመት የትምህርት ቤት መሻሻል ስትራቴጅክ ዕቅድ፣
- የተማሪዎች የመምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም የህንጻዎችና አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃዎች፣
- የትምህርት ክፍለ ጊዜ ስርጭትና የጊዜ ሰሌዳ፣
- የተማሪዎችን ተከታታይ ምዘናዎችና የማጠቃለያ ፈተናዎች ውጤት የሚያሳይ የተጠናቀረ መረጃ፣
- በትምህርት ዙሪያ ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ ት/ቤቱን አስመልክቶ የቀረቡ መሠረታዊ መረጃዎች፣
- የትምህርት ቤቱን የተለያዩ አደረጃጀቶች የሚያሳዩ ሰነዶች።

## 8.4 ኢንስፔክሽንና የትምህርት ቤት ግለ-ግምገማና ደረጃ ምደባ ፡-

የኢንስፔክሽን ሥራ በትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር ጋር ከተካተተው የትምህርት ቤት ግለ-ግምገማ እና የትምህርት ቤት ደረጃ ምደባ አካሄድ ጋር ተደጋጋፊ ነው። የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች በአካል ተገኝተው በት/ቤቱ ግምገማ ከማካሄዳቸው በፊት የትምህርት ቤት የግል ግምገማውን እንዲሁም የትምህርት ቤቱን ደረጃ ምደባ በመመልከት መረጃውን ይተነትናሉ። በኢንስፔክሽን ወቅት የትምህርት ቤቱ የግል ግምገማ እና ፍረጃ በትክክል መካሄዱን ኢንስፔክተሮች ማረጋገጥ ይገባቸዋል። ይህም ነፃና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የት/ቤቱን አፈጻጸም መገምገም መቻሉ ትምህርት ቤቱ ራሱን በተሻለ መልኩ ማየትና መገምገም እንዲሁም የት/ቤቱን ደረጃ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ ያስችለዋል።

## 8.5 የኢንስፔክሽን ሥራ እንዴት ይጀመራል?

የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ትምህርት ቤት እንደደረሱ ከትምህርት ቤቱ ር/መምህር/ት እና ሌሎች የትምህርት ቤቱ አመራሮች ጋር በመገናኘት ስለሚከናወነው የኢንስፔክሽን ሥራ ዓላማና አጠቃላይ ሁኔታ ገለፃ ካደረጉ በኋላ አመራሮቹን በመጋበዝ ጥያቄ ወይም አስተያየት እንዲያቀርቡ ይደረጋል። በተጨማሪም ር/መምህሩ/ሯ ስለትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ አጠቃላይ መረጃ እና በጥንካሬና በድክመት እንዲሁም ወደፊት እድገቱ ትኩረት በሰጣቸው ጉዳዮች ላይ አጭር ገለጻ እንዲሰጡ ይደረጋል ። ኢንስፔክተሮቹ በኢንስፔክሽን ወቅት በየጊዜው ከትምህርት ቤቱ

ር/መምህር/ት ጋር በመገናኘት ከስራው ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና ችግሮች በአፋጣኝ ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ።

## 8.6 ኢንስፔክተሮች እንዴት መረጃ ይሰበስባሉ?

ኢንስፔክተሮች ትምህርት ቤቱን አስመልክቶ ትክክለኛ የአፈጻጸም ውሳኔ ደረጃ ለመስጠት የሚያስችላቸውን መረጃ ለማሰባሰብ ሙሉ ጊዜያቸውን ይጠቀማሉ ። በዚህም መሠረት፡-

- ግማሹን ያህል ጊዜያቸውን የክፍል ምልከታ በማድረግ ያሳልፋሉ፣
- የተማሪዎችን ስራ ይመለከታሉ፣
- ከር/መምህሩ/ሯ፣ከመምህራን፣ከተማሪዎች ጋር ውይይት ያደርጋሉ፣
- ከተማሪ ወላጆች ጋር እና ከአካባቢ ማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት ያደርጋሉ፣
- ትምህርት ቤቱ ከዚህ በፊት ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን ይመለከታሉ፣

## 8.7 ውሳኔ ላይ መድረስ፡-

ኢንስፔክተሮች ትምህርት ቤቱ የተቀመጡትን ስታንዳርዶች ማሟላት ወይም አለማሟላቱን በመገምገም ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። የመለኪያ ነጥቦቹም፡-

- **ደረጃውን ያላሟላ - ደረጃ** 1
- **ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ - ደረጃ** 2
- **ደረጃውን ያሟላ - ደረጃ** 3
- **ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ - ደረጃ** 4 **ናቸው።**

ለየስታንዳርዱ የተቀመጡ አመልካቾችን በመጠቀምና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር ኢንስፔክተሮች የትምህርት ቤቱን የአፈጻጸም ደረጃ የሚያሳይ ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፣

ኢንስፔክተሮች ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ የሰጡትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ በአራት ተመሳሳይ የደረጃ መለኪያዎች ይመዝናሉ። ይህም አጠቃላይ የሆነና ሁሉንም የተሰበሰቡ መረጃዎችን ጥቅም ላይ ያዋለ ሙያዊ ውሳኔ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል።

## 8.8 ለደረጃ ውሳኔ የመለኪያዎች ክብደት አሰጣጥ፡-

ሀገራችን ለተማሪዎች መማር እና ውጤታማነት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች። በመሆኑም የትምህርት ጥራትና ውጤታማነትን በትምህርት ቤት ደረጃ ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ስልቶች አንዱ ትምህርት ቤቶችን በደረጃ በመለየት የውድድር መንፈስ በመፍጠር የአፈጻጸም ብቃታቸውን በማሳደግ

ውጤታማነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ነው ከዚህ አኳያ የትምህርት ቤት ደረጃ ምደባን ለማከናወን በመለኪያነት ለተቀመጡት ግብዓት ፣ ሂደት እና ውጤት ክብደት በመስጠት እንደሚከተለው ይከናወናል፡-

**<u>መለኪያዎች</u>** **<u>ክብደት</u>**

- ለግብዓት /Input/------------- 25%
- ለሂደት /Process/ ----------- 35%
- ለውጤት /Output/ ----------- 40% ድርሻ ተሰጥቷቸዋል::

በተመሳሳይ ለግብዓት፣ ሂደትና ውጤት በተሠጣቸው ክብደት መሠረት በስራቸው ለተቀመጡት ስታንዳርዶችና አመልካቾች ከይዘታቸው አኳያ ተከፋፍሎ በዚሁ ሰነድ በተቀጽላ 1 እና 2 ላይ ተመልክቷል።

## 8.9 የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፡-

የትምህርት ቤት ደረጃ አሰጣጥ ሂደት በትምህርት ቤት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ውስጥ በተመለከቱት ስታንዳርዶችና አመልካቾችን መሰረት ያደረገ ሆኖ፡-

1. በተዘጋጀው የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎች/ቼክሊስት እና የአመልካች ገላጮችን /Descriptors/ መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ አመልካች/Indicator/ ውጤት መስጠት፤
2. በእያንዳንዱ ስታንዳርድ ውስጥ የሚገኙ አመልካቾች አማካይ ውጤትን በመውሰድ ለስታንዳርዱ ደረጃ መስጠት፤
3. በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት ስር ያሉ ስታንዳርዶች አማካይ ውጤት እንደየቅደም ተከተላቸው የግብዓት፣ የሂደት እና የውጤት ደረጃ ይሆናል፤
4. የግብዓት፣ሂደት እና ውጤት ድምር የትምህርት ቤቱ ደረጃ ይሆናል።
   በዚሁ መሠረት የሁሉም መለኪያዎች (ግብዓት ፣ ሂደትና ውጤት) ድምር ውጤት፦

- ከ50% በታች ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 1 ይመደባል።
- ከ50% - 69.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 2 ይመደባል።
- ከ70% - 89.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 3 ይመደባል።
- ከ90% - 100% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 4 ይመደባል።

በመጨረሻም የደረጃ አሰጣጥ ሂደት ዝርዝር አሰራሩ በዚህ ሰነድ መጨረሻ በተያያዘው ተቀጽላ 3 ይመልከቱ።

## 8.10 ግብረ-መልስ መስጠት፡-

ኢንስፔክተሮች በክፍል ውስጥ ስለተደረጉ ምልከታዎች ለመምህሩ/ሯ ግብረ - መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። የሚሠጡትም ግብረ መስሶች ገንቢ ፣ በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል፣ በትምህርት አሠጣጡ፣ ወደፊት መሻሻል በሚገባቸው እና በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል።

የኢንስፔክሽን ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ኢንስፔክተሮች ለትምህርት ቤቱ ር/መምህር/ት እና ሌሎች አመራሮች በኢንስፔክሽኑ ግኝት፣ ስለተደረሰበት ውሳኔ፣ እና ስለተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦች አጠር ያለ የቃል ግብረ መልስ ይሰጣሉ ።ከኢንስፔክተሮች የሚሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማስተግበርና ለትምህርት ቤቱ የወደፊት መሻሻል ጠቃሚነቱን በቀላሉ መገንዘብ እንዲቻል በማጠቃለያ ስብሰባው ላይ የጉድኝት ማዕከሉ ሱፐርቫይዘር መገኘት ይኖርበታል።

## 8.11 የፅሁፍ ሪፖርት ፡-

ከኢንስፔክሽን መጠናቀቅ በኋላ በትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በሚያዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ መሠረት በኢንስፔክሽን የተገኙ ውጤቶችን፣ አስተያየቶችንና የመፍትሔ ሃሳቦችን አጠቃሎ የያዘ አጭር የጽሑፍ ሪፖርት ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

ኢንስፔክሽን ያካሄደው አካል ሪፖርቱን ከሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አጠናቅሮ ለትምህርት ቤቱ እንዲሁም ለወረዳው ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት፣ ለዞን ትምህርት መምሪያና ክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የአንስፔክሽን ዘርፍ የሚልክ ሲሆን የየክልሉ/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች በክልል/ከተማ አስተዳደር የተካሄደ ኢንስፔክሽን አፈጻጸም ሪፖርትን በማጠቃለል ለትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ይልካሉ። ትምህርት ቤቶቹም ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ አባላትና ወላጆችን ጨምሮ ለአካባቢው ማህበረሰብ በሪፖርቱ ላይ የቀረቡትን ሃሳቦች ማካፈል ይኖርባቸዋል። ሪፖርቶች በድረ-ገጽ ሊለቀቁ ይችላሉ።

## 8.12 ክትትል ስለማድረግ፡-

በግምገማው ጊዜ ከስታንዳርድ በላይ ያገኙ ትምህርት ቤቶች የበለጠ እንዲያሻሽሉ በማበረታታት እንደገና ያለውን ለውጥ ለማየት ከ3 ዓመት በኋላ ይጎበኛሉ። ነገር ግን የተቀመጠውን ስታንዳርድ ያላሟሉ ትምህርት ቤቶች ከአንድ አመት በኋላ እንደገና ይታያሉ።ትምህርት ቤቶቹ የሚፈለገውን መሻሻል ካላመጡ በየደረጃው የሚመለከተቻው አካላት ተጠያቂ ይሆናሉ። የጉድኝት ማዕከሉ ሱፐርቫይዘር ትምህርት ቤቱን በቅርብ በመካታተልና በመደገፍ እንዲሻሻሉ የተሰጡ

አስተያየቶችን መተግበራቸውን ያረጋግጣል። አንድ ትምህርት ቤት ቢያንስ በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ በኢንስፔክሽን ቡድን መታየት ይኖርበታል።

### 8.13 የቅሬታ አቀራረብ

በኢንስፔክሽን ወቅት ትምህርት ቤቱ በኢንስፔክተሮቹ በአግባቡ አልታየሁም የሚል ቅሬታ ካሳደረ ወዲያውኑ ከ5 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በቅርብ ለሚመለከተው አካል ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።በተሰጠው ምላሽ ካልረካ በሚቀጥለው ከፍተኛ አካል ጉዳዩ ሊታይ ይችላል። በቅሬታ አፈታት ሂደት ቅሬታ የቀረበለት አካል ቅሬታ በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ የማረጋገጥና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎች እንዲያደርጉ በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ ተመርኩዞ ማከናወን ይጠበቅበታል።

## 9. የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነ-ምግባር

ማንኛውም ኢንስፔክተር፡-

- በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚያከናውናቸው/በምታከናውናቸው ተግባራት ሙያዊ አቀራረብ እንዲኖረው/ራት ይጠበቃል። ኢንስፔክተሩ/ሯ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር የሚያደርጋቸው/የምታደርጋቸው ውይይቶችና ግንኙነቶች በመከባበር ላይ የተመሰረቱ ሊሆን ይገባል፣
- በተቻለ መጠን የትምህርት ቤቱን መማር ማስተማር ሳያስተጓጉል/ሳታሰተጓጉል ስራውን ለማከናወን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል/ባታል፤ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያበሳጩ ወይም የማያስደስቱ ተግባራት አያከናውንም / አታከናውንም ፣
- በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት ሥራውን ያከናውናል / ታከናውናለች፣
- ውሳኔዎች ላይ ሲደርስ/ስትደርስ በተጨባጭ መረጃ ፣ ሚዛናዊነትና ፍትሃዊነትን በጠበቀ መልኩና ግልፅነት በተሞላበት ሁኔታ መከናወን ይኖርበታል፣
- ከትምህርት ቤቱ ጋር የሚደረግ ውይይት ት/ቤቱን የሚገነባ፣ ውጤትን ሊያመጣ የሚችል እንጂ ስህተት ፈላጊ መሆን የለበትም። በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱን የወደፊት መሻሻል የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፣
- የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማሻሻል አስተያየቶች የሚኖራቸው አሰተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም በስራ አጋጣሚ የተሰበሰበ መረጃ ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ሀላፊት አለበት።

ኢንስፔክተሮች ገለልተኛና ውጫዊ አካል በመሆን በተጨባጭ መረጃዎች ላይ ተመስርተው አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር አንድ ትምህርት ቤት ያለበትን ደረጃ ወስነው ከአጠቃላይ አስተያየት ጋር ያቀርባሉ።

## ተቀጽላ-1 (Appendix -I)
## የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ስታንዳርዶችና አመልካቾች

### 1.ግብአት (Input) /25%/

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 1.1 የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች (School facility, physical, human and financial resources) | 1. ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል።/4%/ | • ትም/ቤቱ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንፃዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ባካተተ መልኩ (በቂ ብርሃን፣ስፋት፣ወለል ወዘተ) የታነፁና የተሟሉ ናቸው፣<br>• ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍ ፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ የመምህሩ/ሯ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን፣ ብሬይል እንዲሁም አሟልቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የስፖርት ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።<br>• በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ፣ ገዥ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት ወዘተ እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣ | • የት/ቤቱን ህንፃና የመማሪያ ክፍሎቹን በመመልከት፣<br>• የትም/ቤቱን የተለያዩ ፋሲሊቲዎች/ ቁሳቁሶች/ በመቁጠር፣<br>• ተማሪዎችን፣ርእሰ መምህሩ/ሯንና የሚመለከታቸውን የአስተዳደር ሠራተኞች በመጠየቅ።<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| | 2. ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት | • ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ቤት ጥቅል በጀት /Block grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤<br>• ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የት/ቤት ድጐማ በጀት /School grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤ | • ስለ ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ ምንጭና አጠቃቀም የሚያሳዩ ሰነዶች፣ |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል።/4%/ | • ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት አሰባስበዋል።<br>• ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ዶክመንቶች አሉት፣ | |
| | 3. ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል።/4%/ | • ሁሉም የትምህርት ቤቱ ርእሳነ መምህራንና መምህራን የሙያ ፈቃድና ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት አላቸው፣<br>• ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት፣<br>• ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ/Guidance and Counselling/ አገልግሎት የሚሰጥ/የምትሰጥ ባለሙያ አለው።<br>• ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት የሰለጠኑ መምህራን አሉት። | • የመምህራኖቹን ፕሮፋይል የሚያሳይ መዝገብ፣<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት፣ |
| 1.2 ምቹ የመማሪያ አካባቢ | 4. ትምህርት ቤቱ ለት/ ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ የመማር -ማስተማር አካባቢ ፈጥሯል።/4%/ | • ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ አለው፣<br>• በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ህንፃዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው፣<br>• የትምህርት ቤቱ ግቢ በአጥር ተከብሯል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፣ | • ምድረ ግቢውን በመመልከትና ካርታ በመመልከት<br>• መረጃዎችን በመመልከት<br>• ህንጻዎችን በመመልከት፣<br>• ጥገናን የሚመለከቱ ሪከርዶች<br>• ደህንነትን የተመለከቱ |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | • በትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር ተሟልቷል።<br>• ትምህርት ቤቱ በቂ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው። | ሪፖርቶች<br>• የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በማወያየት |
| | 5. ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል።/3%/ | • በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል ግብዐት፣አደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት ተፈጥሯል።<br>• በትምህርት ቤቱ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦችን ተልዕኮዎችን የተገነዘበና ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምንርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል።<br>• በትምህርት ቤቱ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል። | • ከተማሪዎች ጋር መወያየት፣<br>• ከመምህራንና ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት<br>• ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ጋር በመወያየት<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት |

## 1. 3 የትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴቶችና ዕቅዶች

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| አመራር (Leadership) | 6. ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት።/3%/ | • የትምህርት ቤቱ አመራር ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አዘጋጅቷል፤ | • ከርእሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ሌሎች ሠራተኞች እንዲሁም ከተማሪዎችና ከወላጆች ጋር በመወያየት፡ <br>• በወላጆች፣ መምህራንና ተማሪዎችን መጠይቅ አዘጋጅቶ በማስሞላት መረጃውን በማጠናቀር በሚገኝ ውጤት፣ <br>• ትም/ቤቱን በሥራ ላይ በመመልከት፣ <br>• የትም/ቤቱን መረጃ በመመልከት |
| | 7. ትምህርት ቤቱ አሳታፊ የት/ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፣/3%/ | • ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለይቷል፣ <br>• ትምህርት ቤቱ የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቷል፣ | • ርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት፣ ሰነዶችን በመመልከት፣የት/ቤት መሻሻል ኮሚቴን በማወያየት <br>• ትምህርት ቤቱ ራሱን የገመገመበት ሰነድ |

## II. ሂደት (Process) /35%/

### 2.1 መማር- ማስተማር /Learning and Teaching/

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 2.1.1. መማር (Learning) | 8. የተማሪዎች መማርና ተሳትፎ ጎልብቷል። /3%/ | • ተማሪዎች የተሰጧቸውን ሥራዎች በትጋት ይሰራሉ፣<br>• ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅና መልሶችን ለመመለስ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፣<br>• ተማሪዎች በ1 ለ 5 (ኔትወርክ) አደረጃጀት ተደራጅተው በትምህርታቸው ይረዳዳሉ፣<br>• ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ነው፣<br>• ተማሪዎች በህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል ተደራጅተው በመማር ማስተማር የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተሳትፎ እያደረጉ ነው። | • የተማሪዎች ደብተር በመመልከት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ በማካሄድ፣<br>• ተማሪዎች፣ መምህራንን እና ር/መምህራን ጋር በማወያየት<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| | 9. ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል።/3%/ | • ተማሪዎች የትምህርት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣<br>• ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር መፍጠር፣ መመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች መፍታት ችለዋል።<br>• ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ሁሉ ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ፣<br>• ተማሪዎች በፈተና/ምዘና የሚፈፀም ኩረጃ ጸያፍ መሆኑን ተገንዝበዋል፣ | • የተማሪዎች ስም መቀጣጠሪያ በመመልከት<br>• ያርፋጅ፣የቀሩ፣ያቋረጡና የደገሙ ተማሪዎች መመዝገቢያ ቅጽ እና የተማሪ ውጤት ማጠቃለያ/ሮስተር/ በመመልከት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ<br>• ከተማሪ፣መምህራን እና ር/መምህራን ጋር በመወያየት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 10. ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው በጎ አመለካከት አላቸው።/2%/ | • ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ በሚሰጣቸው አገልግሎት ረክተዋል።<br>• ት/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ድጋፍ አድርገዋል፣<br>• ተማሪዎች መምህሮቻቸውን በአግባቡ መመዘን ችለዋል፣<br>• ተማሪዎች ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት ይሰጣሉ፣<br>• ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ አድርገዋል፣ | • ሰነዶችን በመመልከት፣<br>• ከተማሪዎች፣መምህራን፣ር/መምህራን እና የአስተዳደር ሰራተኞች ጋር በመወያየት፣<br>• የተለያዩ የዲሲፒሊን ሰነዶችን በመመልከት |
| 2.1.2 ማስተማር | 11. መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደ፣ በአመቺ የትምህርት መርጃዎች የተደገፈ እና ከፍተኛ<br><br>የትምህርት ውጤትን ለማስገኘት አልሞ የተዘጋጀ ነው።/3%/ | • የመምህራን የትምህርት እቅድ የሚያስተምሩትን ትምህርት አላማ፣ ይዘት፣የማስተማር ስነ ዘዴ… ወዘተ በአግባቡ አካቷል፣<br>• መምህራን የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ አውለዋል፣<br>• መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ፕላዝማ፣ቴሌቪዥን፣ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ቤተ-ሙከራ በመጠቀም ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎቻቸው የአካባቢ ቁሳቁስ ተጠቅመው የፈጠራ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታታሉ፣<br>• መምህራን ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸውና በውጤታቸው እንዲሻሻሉ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እገዛ አድርገዋል። | • የትምህርት እቅድ፣<br>• የትምህርት ማእከሉን በመመልከት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ<br>• የኢ.ኮ.ቴ ማእከልን በመመልከት<br>• የቤተ-ሙከራ አጠቃቀም እቅዶችን በመመልከትና ተጠቃሚዎችን በማወያየት<br>• የተሰሩ ስራዎችን በመመልከት<br>• ተማሪዎችን፣መምህራንን እና ር/መምህራንን በማወያየት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 12. መምህራን የሚስተምሩትን የትምህርት ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ። /3%/ | • መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት በቂ እውቀትና ክህሎት አላቸው፣<br>• መምህራን ለተማሪዎች በሚመጥን ቋንቋ እና አቀራረብ ይዘቱን ቀለል አድርገው ያቀርባሉ፡<br>• መምህራን በትምህርቱ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦችን ለተማሪዎች በግልጽና አብራርተው ያቀርባሉ | • የክፍል ውስጥምልከታ በማካሄድ ፣<br>• የተማሪዎችን ፓርላማ/ካውንስል፣መምህራን የትምህርት ክፍል ሃላፊዎችን እና ር/መምህራንን በማወያይት |
| | 13. የት/ቤቱ አመራርና መምህራን ለሁሉም ተማሪዎች ተስማሚና ዘመናዊ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ጎልብቷል።/3%/ | • መምህራን ተማሪዎች በትምህርታቸው ተመራማሪ፣ ፈጣሪ፣ ችግር ፈቺ እና ራሳቸውን የሚመሩ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፣<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር ዘመናዊና አሳታፊ የመማር-ማስተማር ስነ ዘዴ በት/ቤቱ እንዲተገበር ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፣<br>• መምህራን ተማሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በጥንድ፣ በቡድን እና በግል ትምህርታቸውን እንዲማሩ አድርገዋል፣<br>• መምህራን ለሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን የመማር ማስተማሩን ችግር ለመፍታት የተግባር ምርምር አካሂደዋል። | • የክፍል ውስጥምልከታ በማካሄድ ፣<br>• የተማሪዎችን ፓርላማ/ካውንስል፣መምህራን የትምህርት ክፍል ሃላፊዎችን እና ር/መምህራንን በማወያይት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 14. ትምህርት ቤቱ ለሴቶችና እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።/3%/ | • ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎች ትምህርት ቤቱ መዝግቦ ይዟል፤<br>• ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር በመወያየት፣<br>• መረጃዎችን በመመልከት |
| | 15. መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር /CPD/ ተግባራዊ አድርገዋል። /2%/ | • ነባር መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ቤቱን የመማር ማስተማር ችግር ለመፍታት የሚያስችል ችግሮችን በቅደም ተከተል ለይተው ሞጁል አዘጋጅተው ቢያንስ በዓመት ለ60 ሰዓት በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ላይ ተሳትፈዋል፣<br>• አዲስ ጀማሪ መምህራን አማካሪ መምህራን ተመድበውላቸው የሙያ ትውውቅ መርሃ ግብር /Induction/ አጠናቀዋል፣ | • የትም/ቤቱ የተሙማ ዕቅድ ግላዊ ግምገማ ሠነድ፣<br>• የመምህራን የግል ተሙማ ዕቅድ ግላዊ ግምገማና የሙያ ማሻሻያ ግል<br>• ማህደረ ተግባር /Portfolio/፣<br>• ከመምህራን ጋር መወያየት፣<br>• የክፍል ምልከታ ማድረግ። |
| | 16. የትምህርት ቤቱ አመራር ፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልማት ሠራዊት በመደራጀት በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው። /3%/ | • የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ተማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው የትምህርት ልማት ሰራዊት በመገንባት ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መልክ ተወጥተዋል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፣ እርስ በእርስም በውስጥ ሱፐርቪዥን አማካኝነት ተገነባብተዋል።<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጥሩ ስነ ምግባር የታነፁ፣ ለሙያቸው ተገቢ ክብር ያላቸው፣ትምህርት ቤቱን ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑ ናቸው፣ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር መወያየት።<br>• ሰነዶችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 2..2 ሥርዓተ ትምህርት (Curriculum) | 17. ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው፣አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ መሆኑን መምህራን ይገመግማሉ፣ግብረ መልስ ይሰጣሉ፣ ያሻሽላሉ።/2%/ | • መምህራን በሥራ ላይ ያለውን ሥርዓተ ትምህርት ጠንቅቀው ያውቃሉ፣<br>• መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአገር አቀፍና በክልል የተዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርቶችን ያገናዘበ ነው፣<br>• መርሃ-ትምህርቶቹና ሌሎች የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች አሳታፊና ከተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃና ፍላጎት ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው ግብረ መልስ ተሰጥቶባቸዋል፣ | • የክፍል ምልከታ፣<br>• የሥርዓተ ትምህርት እቅዶችን ማቴሪያሎችን መፈተሽ፣<br>• የተጓዳኝ ትምህርት ሥራዎችን በመመልከት፣<br>• ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር መወያየት። |
| 2.3 ምዘና (Assessment) | 18. ተማሪዎች በትክክል ተመዝነዋል፣አስፈላጊው ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል። /3%/ | • በትምህርት ቤቱ የሚዘጋጅ ምዘና ስርአተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ በቢጋር /Table of Specifications/ የተዘጋጀ ነው፣<br>• ተማሪዎች በክልል/ከተማ አስተዳደር፣በዞን/ክፍለ ከተማ በወረዳና በጉድኝት ማዕከል በሚዘጋጁ ፈተናዎች ይመዘናሉ፣<br>• መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለመለካት በተቀመጠው ዝቅተኛ የመማር ብቃት /MLC/ መሠረት የንድፈ ሃሳብና የተግባር ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ፣<br>• መምህራን የተማሪዎችን ውጤት በመተንተን ድጋፍ ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን ተማሪዎች ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ ግብረ-መልስ በመስጠት ድጋፍ ያደርጋሉ፣<br>• ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን ውጤት ለወላጆች በማሳወቅ ግብረ መልስ ይቀበላል። | • የትምህርት ክፍል ሃላፊዎችንና ይስርአተ ትምህርት ኮሚቴ አባላትን በማወያየት<br>• መምህራንን፣ ሱፐርቫይዘርና ር/መምህርራንን በማወያየት<br>• የተከታታይ ምዘና ሪከርዶችን በመመልከት<br>• ወላጆችን በማወያየት<br>• የተለያዩ ሰነዶችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 2.4 ክትትልና ግምገማ- አመራር (Leadership) | 19. የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች ያቀዱቸው እቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላሉ። /2%/ | • በትምህርት ቤቱ ማህበረሰቡ የተደራጁ የትምህርት ልማት ሰራዊት እቅዶች በአግባቡ መታቀዳቸውንና መከናወናቸውን ይከታተላል፣ለችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፣<br>• በትምህርት ቤቱ የተደራጀው የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራምን አተገባበርን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣<br>• በትምህርት ቤቱ የተደራጀው የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ኮሚቴ በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የተዘረጉ ስልጠናዎችን አፈፃፀማቸውንና መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች እየለየ ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደትና የክበባት ዕቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣<br>• ት/ቤቱ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አካላትን ያበረታታል፣ ዕውቅና ይሰጣል፣ | • ትም/ቤቱ ራሱን የገመገመበት ሰነድ፣<br>• በወላጆች፣ በመምህራንና በተማሪዎች የተሞላ መጠይቅ ውጤት፣<br>• የአንድ እና የሶስት ዓመት የት/ቤት እቅድ ሰነድ፣<br>• የትም/ቤት መሻሻል በኮሚቴ ቃለ ጉባዔና ተዛማጅ መረጃዎች/ሰነዶች<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯና ከሌሎች አመራሮች ጋር ውይይት ማካሄድ፣<br>• ከጉድኝት ማእከሉ ሱፐርቫይዘር ጋር ውይይት ማካሄድ። |
| ክትትልና ግምገማ - አስተዳደር(Management | 20. ትምህርት ቤቱ የሰው ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል። /2%/ | • ት/ቤቱ የመረጃ አሰባሰብ፣አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፣<br>• መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ተመድበው ያስተምራሉ፣<br>• ርዕሰ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ ተመድበው ይሰራሉ፣<br>• በት/ቤቱ ያሉ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች እና ተጨማሪ ግብዓቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ውለዋል፣ | • የትምህርት ቤቱን ህንፃ የውስጥ ግብዓቶችን በመመልከት፣<br>• ከርእሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ሌሎች ሠራተኞች ጋር በመወያየት፣<br>• የገንዘብና ሌሎች መረጃ ቋቶችን በመፈተሽ |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | • የት/ቤቱ በጀት ቅድሚያ ለተሰጣቸው የትምህርት ቤት መሻሻል እቅድ ላይ በተቀመጡና አግባብነት ያላቸው አካላት በወሰኑት መሠረት በተገቢ መንገድ ሥራ ላይ ውሏል። | |
| 2.5 የትምህርት ቤት፣የወላጆችና የማህበረሰብ አጋርነት /Engagement with parents and the community/ | 21. ትምህርት ቤቱ ከተማሪ ወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው።/2%/ | • ትምህርት ቤቱ ወላጆች በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤ በትምህርት ቤትና በክፍል ደረጃ ወላጆች ትርጉም ያለው ተሳትፎ በተደራጀ መልኩ እንዲያደርጉ ያደርጋል።<br>• ትምህርት ቤቱ በየወቅቱ ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበልና ውጤት፣ ባህርይ፣ የፋይናንስ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃ ይሰጣል፣ ግብረ መልስም ይቀበላል፣<br>• ወላጆች ልጆቻቸው በቤት ውስጥ በትምህርታቸው እንዲበረታቱ ያግዛሉ፣<br>• ወላጆች በወላጅ፣ተማሪ፣ መምህር/ት ህብረት(ወመህ/ወተመህ) እንቅስቃሴ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣<br>• ትምህርት ቤቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ በአንጻራዊነት የልህቀት ማዕከል በመሆን ያገለግላል፣<br>• ወላጆች በትምህርት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም መርካታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ፣ | • ከወላጆች ጋር መወያየት፣<br>• ለወላጆች የቀረበ ሪፖርት፣<br>• ከወላጆች ጋር ውይይት የተደረገባቸው ቃለ ጉባዔ ሠነዶች፣<br>• ለቀረበላቸው መጠይቅ ወላጆች የሰጡት ምላሽ፣<br>• ከርእሰ መምህሩ/ሯና አግባብ ካለው የሥራ ባልደረባ ጋር ውይይት ማድረግ፣፣ |

## 3. ውጤት (Output) /40%/

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 3.1 ትምህርት ቤቱና ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት (Students' Attainment) | 22. ትምህርት ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት/Internal efficiency/ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።/10%/ | • በትምህርት ቤቱ አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ተደርጓል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የጥቅል ተሳትፎ ዕቅዱን አሳክቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የንጥር ተሳትፎ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል፣<br>• የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ጾታዊ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል።፣<br>• የትምህርት ቤቱ መጠነ ማቋረጥ በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል፣<br>• የትምህርት ቤቱ መጠነ መድገም በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል። | • የተማሪዎች የመዝገብ ሠነዶች፣<br>• የተማሪዎች መከታተያ ሠነዶች፣<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር ውይይት ማካሄድ፣ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበሰብ ውይይት ማካሄድ። |
| | 23. የተማሪዎች የክፍል ፣ የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች ከሚጠበቀው ሃገራዊና ክልላዊ መመዘኛ ጋር ሲነፃፀር ተሻሽሏል። /8%/ | • ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣<br>• ትምህርት ቤቱ ለሁሉም ሴት ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣<br>• ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣<br>• የተማሪዎች የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች በትምህርት ቤቱ ዕቅድ መሰረት ተሳክቷል፣ | • የተማሪዎች የሙከራና የማጠቃለያ ፈተናዎች መረጃ፣<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.1.2 የተማሪዎች ግለ-ስብዕና እድገት (Students' personal development) | 24. ተማሪዎች በሥነ-ስርዓት የታነጹ፣ መልካም እሴቶችና ባህልን የተላበሱ፣ አካባቢን የመንከባከብ ኃላፊነት የሚሰማቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።/10%/ | • ተማሪዎች በስነ ምግባር የታነጹ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያከብሩ፣እርስ በርስ የሚከባበሩና የሚተጋገዙና ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚታገሉ ሆነዋል፣<br>• ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ንብረት ተንከባክበዋል፣<br>• ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን እሴቶች፣ደንቦችና መመሪያዎችን አውቀው ስራ ላይ በማዋል ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል።<br>• በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች መካከል የመቻቻልና ልዩነትን በውይይት የመፍታት ባህል ዳብሯል፣<br>• ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል። | • ከተማሪዎች ጋር ውይይት ማድረግ፣<br>• የክፍል ምልከታ፣<br>• በትምህርት ቤት አካባቢ እየተዘዋወሩ ተማሪዎች የሚያደርጉትን ድርጊት መመልከት። |
| | 25. በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ተፈጥሯል፣ ኪራይ ሰብሳቢ ነትን የመታገልና የተጠያቂ ነት ስሜት ዳብሯል።/6%/ | • የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩና ተግባቢ በመሆናቸው የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ዳብሯል፣<br>• በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣<br>• የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል። | • የክፍል ምልከታ፣<br>• ከመምህራንና ተማሪዎች ጋር ውይይት ማካሄድ። |
| 3.4 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ | 26. ትምህርት ቤቱ ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል፣ /6%/ | • ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣<br>• ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በመጨመሩ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል፣ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራን እና ከሌሎችም የት/ቤቱ ሰራተኞች እንዲሁም ከአካባቢው ማህበረሰብ አባላት ጋር ውይይት ማድረግ<br>• የተከናወኑ ተግባራት መዝገብ ላይ<br>• የገንዘብ ወጪ መዝገቦች ላይ |

## ተቀጽላ-2 (Appendix – II)

## ገላጮች /Descriptors/

**ቁልፍ/key/፡-** በውሳኔ አሰጣጥ /ደረጃ ምደባ ሂደት ላይ ውሳኔ ሰጪው አካል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተገንዝቦ ውሳኔ እንዲሰጥ ይጠበቃል። እንደ አጠቃላይ በዚህ ሰነድ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉና በአተረጓጎም ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ታስቦ በመስፈርትነት የተቀመጡ ቃላቶች ከዚህ በታች ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል።

- ከፍተኛ እጥረት/በጣም ዝቅተኛ/አነስተኛ /ውሱን ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር ከ50 በመቶ በታች ያገኘ፣
- አብዛኛው/አብዛኞቹ/ከፍተኛ ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር 50-69.99 በመቶ ያገኘ፣
- ሙሉ በሙሉ/ሁሉንም ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ 70-89.99 በመቶ ያገኘ፣
- በጣም ከፍተኛ የሚለው ከ90 ከመቶ እና በላይ ያገኘ፣

በሚል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል።

## I.ግብዓት /25%/

| 1.1- የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ስታንዳርድ 1 ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል።/4%/ | | | | |
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትም/ቤቱ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንፃዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ባካተተ መልኩ (በቂ ብርሃን፣ስፋት፣ወለል ወዘተ) የታነፁና የተሟሉ ናቸው፣ /1%/ | በአብዛኛው ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የታነፁ የመማሪያና የመገልገያ ህንፃዎች የሉትም። | ትምህርት ቤቱ መማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንጻዎችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማሩ አስፈላጊ የሆኑ ህንፃዎች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ የተሟሉ የመማሪያ ክፍሎችና ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ ከተቀመጠው ስታንዳርድ ባለይ ህንፃዎች አሉት። |
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ የመምህር መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን፣ ብሬይል አሟልቷል፣ /1%/ | በትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መጽሐፍ፣ የመምህር መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሃፍት፣ ብሬይል ከፍተኛ እጥረት ይታያል። | በትምህርት ቤቱ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መጽሐፍና የመምህር መምሪያ እንዲሁም አጋዥ/ ማጣቀሻ መፃህፍት፣ ብሬይል በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው ተሟልተዋል። | በትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መጽሐፍ እንዲሁም አጋዥ/ ማጣቀሻ መፃህፍት የመምህር መምሪያ፣ ብሬይል በስታንዳርዱ መሰረት ተሟልተዋል። | ትምህርት ቤቱ ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መፃህፍ፣ የመምህር መምሪያ ፣አጋዥ/ ማጣቀሻ መፃህፍት፣ ብሬይል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ነው |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።/1%/ | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አላሟላም፡ | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በስታንዳርዱ መሠረት አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን ከስታንዳርዱ በላይ አሟልቷል። |
| በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ገዥ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞ ችና ማእቀፎች ህገ መንግስት እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣ /1%/ | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ዘርፉን አጠቃላይ አቅጣጫ ለመገንዘብ የሚያስችለው አገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው የሉትም ። | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ዘርፉን አጠቃላይ አቅጣጫ ለመገንዘብ የሚያስችለው አገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው አሉት፣ ሥራ ላይም አውሏቸዋል። | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ዘርፉን አጠቃላይ አቅጣጫ ለመገንዘብ የሚያስችለው አገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያ ዎችና መተዳደሪያ ደንብ ተሟልቶ ስራ ላይ ውሏል ። | በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ በዘመናዊ የመረጃ ማደራጃ ዘዴ በመጠቀም ባለድርሻ አካላት አውቀው እንዲጠቀሙበት አድርጓል። |

| ስታንዳርድ 2 - ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሚልቷል። /4%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ቤት ጥቅል በጀት (Block Grant) በተማሪዎች ቁጥር መሠረት ተቀብሎ በአግባቡ ስራ ላይ አውሏል፤ /0.5%/ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት አልተቀበለም፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት የደረሰው ቢሆንም ለታለመለት አላማ አላዋለውም፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ ተጨማሪ በጀት ከተለያዩ ምንጮች በማፈላለግ ሌሎች ተግባራትን አከናውኗል፤ |
| የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩና ተግባቢ በመሆናቸው የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ዳብሯል፣ /2%/ | አብዛኛው የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን በማክበር፣ በመግባባትና የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት በማነሳሳት ዙሪያ እጥረት ይታይባቸዋል። | አብዛኛው የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩ፣ ተግባቢና የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት የሚያነሳሱ ናቸው። | ሁሉም የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩ፣ ተግባቢ በመሆናቸው የተማሪዎች የመማር ፍላጐት ዳብሯል። | ሁሉም የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩ፣ ተግባቢ በመሆናቸው የተማሪዎች የመማር ፍላጐት ዳብሯል። ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርዓያ ሆነዋል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣ /2%/ | በአብዛኛዎቹ የት/ቤቱ አመራር፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዙሪያ እጥረት ይታይባቸዋል። | በአብዛኛዎቹ የት/ቤቱ አመራር፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል መሻሻል አሳይቷል። | በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣ | በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣ በመሆኑም በሁሉም ዘንድ የስራ ተነሳሽነት ጨምሯል። |
| የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል። /2%/ | አብዛኛዎቹ የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን በመታገልና በመጸየፍ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የመስራት እጥረት ይታይባቸዋል። | አብዛኛዎቹ የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል። | ሁሉም የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል። | ሁሉም የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል።ለሌሎች ትምህርት ቤቶችና ማህበረሰቡ አርዓያ ሆነዋል። |
| **ስታንዳርድ 26 - ትምህርት ቤቱ ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል።**/6%/ | | | | |
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትምህርት ቤቱ ወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል። /3%/ | ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በለመፍጠሩ ድጋፍ አላገኘም። | ትምህርት ቤቱ ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠሩ ውስን ድጋፍ አግኝቷል። | ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ በቂ ድጋፍ አግኝቷል። | ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ከፍተኛ ድጋፍ አግኝቷል፤ቀጣይነቱንም ለማረጋገጥ ስልት አስቀምጠዋል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በመጨመሩ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል፣ /3%/ | ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት መንፈስ የመምራት ልምድ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። | ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት መንፈስ የመምራት ልምድ መሻሻል አሳይቷል። | ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል። | ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆነዋል። |

## ተቀጽላ 3 (Appendix –III)

## የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ቀመር ምሳሌ

**ስታንዳርድ-ሁ፡-** ለስታንዳርድ - ሀ የተሰጠ ዋጋ /ድርሻ ያለ ሲሆን በስሩ ለሚገኙ አመልካቾች የሚከፋፈል ሆኖ የስታንዳርዱ የውሳኔ ውጤት ለአመልካቾች የተሰጠ የደረጃ ውሣኔ ውጤት ድምር ይሆናል ። ከታች የተዘረዘሩት ስታንዳርዱን የሚገልጹ አመልካቾች የተከፋፈሉት የስታንዳርዱ የተሰጠ ጠቅላላ ዋጋ/ክብደት 11.6% ነው። ለእያንዳንዱ አመልካች የተለያዩ ደረጃዎች በተለያዩ ተቋማት ቢሰጥ ሊገኝ የሚችለው ውጤት በአመልካችና በደረጃ መገናኛ ሳጥን /cell / ላይ ተመልክቷል። በተመሳሳይ  ለሌሎች የተሰጡ ዋጋዎችና ውሳኔዎች ሊተገበር የሚገባው ሂሳብ ነክ ቀላል የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በተጨባጭ፣ በማያሻማና ወጥነት ባለው ሁኔታ ተቋሙ ከተጠቀሰው አመልካች አኳያ የት ላይ እንዳለ ማሳየት የሚችል ነው።

| አመልካቾች | የአመልካች የተሰጠ ዋጋ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አመ.1 | 0.10% | $\frac{0.10\times1}{4} = 0.025$ | $\frac{0.10\times2}{4} = 0.05$ | $\frac{0.10\times3}{4} = 0.075$ | $\frac{0.10\times4}{4} = 0.10$ | |
| አመ.2 | 0.25% | $\frac{0.25\times1}{4} = 0.0625$ | $\frac{0.25\times2}{4} = 0.125$ | $\frac{0.25\times3}{4} = 0.1875$ | $\frac{0.25\times4}{4} = 0.25$ | |
| አመ.3 | 0.50% | $\frac{0.50\times1}{4} = 0.125$ | $\frac{0.50\times2}{4} = 0.25$ | $\frac{0.50\times3}{4} = 0.375$ | $\frac{0.50\times4}{4} = 0.50$ | |
| አመ.4 | 0.75% | $\frac{0.75\times1}{4} = 0.1875$ | $\frac{0.75\times2}{4} = 0.375$ | $\frac{0.75\times3}{4} = 0.5625$ | $\frac{0.75\times4}{4} = 0.75$ | |
| አመ.5 | 1.0% | $\frac{1.0\times1}{4} = 0.25$ | $\frac{1.0\times2}{4} = 0.50$ | $\frac{1.0\times3}{4} = 0.75$ | $\frac{1.0\times4}{4} = 1.0$ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አመ.6 | 2.0% | $\frac{2.0\times1}{4} = 0.50$ | $\frac{2.0\times2}{4} = 1.0$ | $\frac{2.0\times3}{4} = 1.50$ | $\frac{2.0\times4}{4} = 2.0$ | |
| አመ.7 | 3.0% | $\frac{3.0\times1}{4} = 0.75$ | $\frac{3.0\times2}{4} = 1.50$ | $\frac{3.0\times3}{4} = 2.25$ | $\frac{3.0\times4}{4} = 3.0$ | |
| አመ.8 | 4.0% | $\frac{4.0\times1}{4} = 1$ | $\frac{4.0\times2}{4} = 2.0$ | $\frac{4.0\times3}{4} = 3.0$ | $\frac{4.0\times4}{4} = 4.0$ | |

**የውሳኔ ዋጋ አሠጣጥ፡-** የውሣኔ ዋጋ ማለት በኢንስፔክተሩ/ሯ ወይም ደረጃውን የሚያወጣ አካል ለእያንዳንዱ አመልካችና ስታንዳርድ የተሰጠ የደረጃ ውሣኔ ማለት ነው ፡፡ በቀመር ሲቀመጥ፡-

**የአመልካች የውሳኔ ዋጋ** = $\frac{\text{ለአመልካች የተሰጠ ዋጋ x የተወሰነ ደረጃ (1,2,3 ወይም 4)}}{4}$

1. ለምሳሌ ከላይ ከሰንጠረዥ አመልካች 1 የተሰጠው ዋጋ 0.10% ቢሆንና በውሳኔ የተሰጠው ደረጃ 2 ቢሆን የአመልካች 1 የውሳኔ ውጤት

$$= \frac{0.10\times2}{4} = 0.05\%$$ ይሆናል፡፡

2. ለምሳሌ አመልካች 5 የተሰጠው ዋጋ 1.0% ቢሆንና በውሳኔ የተሰጠው ደረጃ 3 ቢሆን የአመልካች የውሳኔ ውጤት

$$= \frac{1.0\times3}{4} = 0.75\%$$ ይሆናል፡፡

3. በደረጃ 1 ላይ ለሚሠጥ የውሳኔ አሠጣጥ ውጤት ተመሳሳይ ቀመርን መጠቀም ይቻላል። ነገር ግን አንዳንዳድ አመልካቾች ላይ በግልፅ አለመሟላታቸው የሚታይ ከሆነ ዜሮ /ባዶ/ ሊሰጥ ይችላል።

4. የስታንዳርዱ የውሳኔ ውጤት በስሩ የሚገኙ አመልካቾችን የውሳኔ ውጤት በመደመር ሊገኝና ሊወሰን ይችላል። ስለሆነም ከላይ በሰንጠረዥ ከተሰጠው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ለየአመልካቾቹ የተሰጠን የደረጃ ውሳኔ በምሳሌነት ቢሰጥ ብለን እንውሰድና የስታንዳርዱን የውሳኔ ውጤት እንዴት እንደሚገኝ እንመልከት፡-

| አመልካች | የተሰጠ ደረጃ ውሳኔ | የውሳኔ ውጤት በ% |
|---|---|---|
| አመ.1 | ደረጃ 3 | $\frac{0.10\times 3}{4} = 0.075$ |
| አመ.2 | ደረጃ 2 | $\frac{0.25\times 2}{4} = 0.125$ |
| አመ.3 | ደረጃ 4 | $\frac{0.50\times 4}{4} = 0.50$ |
| አመ.4 | ደረጃ 1 | $\frac{0.75\times 1}{4} = 0.1875$ |
| አመ.5 | ደረጃ 2 | $\frac{1.0\times 2}{4} = 0.50$ |
| አመ.6 | ደረጃ 3 | $\frac{2.0\times 3}{4} = 1.50$ |
| አመ.7 | ደረጃ 2 | $\frac{3.0\times 2}{4} = 1.50$ |
| አመ.8 | ደረጃ 4 | $\frac{4.0\times 4}{4} = 4.0$ |
| **የስታንዳርዱ ውሳኔ ውጤት** | **የአመልካቾች ድምር ውጤት** | 8.3875% |

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው የስታንዳርዱ የውሳኔ ውጤት የሚሆነው በሥሩ የሚገኙ የአመልካቾች የውሳኔ ውጤት ድምር በመሆኑ፡-

የስታንዳርድ ውሳኔ ውጤት = አመ.1. ደረጃ 3 + አመ.2 ደረጃ 2 + አመ.3 ደረጃ 4

+ አመ. 4 ደረጃ 1 + አመ.5 ደረጃ 2 + አመ.6 ደረጃ 3

+ አመ.7 ደረጃ 2 + አመ.8 ደረጃ 4

የስታንዳርድ ውሳኔ ውጤት = 0.075 + 0.125 + 0.50 + 0.1875 + 0.50 +1.50

+ 1.50 + 4.0

የስታንዳርድ ውሳኔ ውጤት = 8.3875%

የስታንዳርዱ የውሳኔ ዋጋ/በማጠጋጋት/ ≈ 8.39% ይሆናል።

5. ለስታንዳርዱ የተሰጠው ድርሻ/ዋጋ 11.6% ሲሆን ከአመልካቾች ውጤት ድምር አንፃር የተሰጠው ውሳኔ 8.39% ነው። ስታንዳርዱ የሚወድቅበትን ደረጃ ለመለየት ከተሰጠው ድርሻ ጋር በማነጻጸር ወደ ፐርሰንት/መቶኛ መቀየር ያስፈልጋል። ስለሆነም፡-

   ወደ መቶኛ/ፐርሰንት የተቀየረ የውሳኔ ውጤት = $\frac{8.39}{11.6} \times 100 = 72.33\%$ ይሆናል።

   በተቀመጠው ስኬል መሠረት የአንድ የስታንዳርድ ውጤት□ከ70% - 89.99% ከሆነ ተቋሙ ከተጠቀሰው ስታንዳርድ አንጻር በደረጃ 3 ላይ ይገኛል። ስለዚህ ከላይ የተገኘው 72.33% ውጤት ስታንዳርዱ በደረጃ 3 ላይ እንዲወድቅ የሚያደርገው ይሆናል ማለት ነው።

6. በተመሳሳይ መልኩ የስታንዳርዶች አማካይ ውጤትን በመውሰድ የትምህርት ቤቱን ደረጃ በግብዓት፣ በሂደትና በውጤት እንዲሁም በተቋም ደረጃ የት ላይ እንዳለ ውሳኔ ላይ መድረስ ይቻላል።

## ተቀጽላ 4 (Appendix – IV)

# የኢንስፔክሽን ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

### ሀ. አጠቃላይ መረጃ፡-

1. የትምህርት ቤቱ ስም፡---------------------------------------------------------------
2. የትምህርት ቤቱ ዓይነት---------------------- ደረጃ፡----------------------------
3. ት/ቤቱ የሚገኝበት ቦታ፡ ከተማ----------------- ገጠር ---------- ሌላ-----------
4. ት/ቤቱ የሚገኝበት

   4.1 ክልል----------------- 4.2 ዞን/ክፍል ከተማ----------------- 4.3 ወረዳ----------
5. የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ት ስም፡------------------------------ ጾታ፡-------------

   የርዕሰ መምህሩ/ሯ የትም/ደረጃ፡ -----------------
6. የመምህራን ብዛት፡- ወንድ፡---------------- ሴት፡----------------- ድምር፡-------------
7. የመምህራን ብዛት በትምህርት ደረጃ

| | |
|---|---|
| ከዲፕሎማ በታች፡- | ወ------------ሴ-------------ድ-------------- |
| ዲፕሎማ ፡- | ወ------------ሴ-------------ድ-------------- |
| ዲግሪ ፡- | ወ------------ሴ-------------ድ-------------- |
| ማስተርስ ፡- | ወ------------ሴ-------------ድ-------------- |
| ሌላ ፡- | ወ------------ሴ-------------ድ-------------- |

8. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ወ------------ሴ-------------ድ--------------

ከ10ኛ/12ኛ ክፍል በታች ወ------------ሴ-------------ድ--------------

ሠርተፊኬት ወ------------ሴ-------------ድ--------------

ዲፕሎማ ወ------------ሴ-------------ድ--------------

ዲግሪ ወ------------ሴ-------------ድ--------------

ማስተርስ ወ------------ሴ-------------ድ--------------

ሌላ ወ------------ሴ-------------ድ--------------

9. የተማሪዎች ብዛት፡- ወንድ--------------- ሴት------------------ድምር----------------

10. የት/ቤቱ ፡- ስልክ ---------------------------- ፋክስ -----------------------

ኢሜይል አድራሻ፡-------------------------------------------------

የት/ቤቱ ድረ ገጽ፡---------------------------------------------------

11. ኢንስፔክሽን የተካሄደበት ቀን ከ------------------- እሰከ -------------------

የኢንስፔክተሮች ስም 1.----------------------------------- ፊርማ------------

2.----------------------------------- ፊርማ------------

3.----------------------------------- ፊርማ------------

4. ---------------------------------- ፊርማ------------

5. ---------------------------------- ፊርማ-------------

## 12. ኢንስፔክሽኑን ያካሄደው አካል

12.1 ትምህርት ሚኒስቴር---------------- 12.2 ትምህርት ቢሮ ፡--------------------

12.3 የዞን/ክፍለ ከተማ ትም/ጽ/ቤት----------------- 12.4 ወረዳ ት/ጽ/ቤት--------------

12.5 ሌላ---------------------------------------

## 13. የኢንስፔክሽን ሪፖርት ማጠቃለያ

### 13.1 በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱ የሥራ አፈጻጸም ደረጃና ውጤት

ሀ. ደረጃውን ያላሟላ - **ደረጃ** 1 ውጤት ----------------

ለ. ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ - **ደረጃ** 2 ውጤት ----------------

ሐ. ደረጃውን ያሟላ - **ደረጃ** 3 ውጤት ----------------

መ. ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ - **ደረጃ** 4 ውጤት -------------

### 13.2 በትምህርት ቤቱ አፈጻጸም የታዩ ጠንካራ ጎኖች፡-

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

____________________________________________________________.

## 13.3 መሻሻል የሚገባቸው የትምህርት ቤቱ ንዑስ የትኩረት መስኮች፡-

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________.

## 13.4 የኢንስፔክተሮች አጠቃላይ አስተያየት፡-

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________.

**ማስታወሻ፡** ከላይ በተሰጡት ውሳኔዎች / አስተያየቶች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ መጨመር ወይም መቀነስ ይቻላል።

## ለ. በስታንዳርድ መሠረት የትምህርት ቤቱ የአፈጻጸም ደረጃ

**የውሳኔ አሰጣጥ በደረጃ፡-** 1፡ ደረጃውን ያላሟላ፣ 2፡ ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ፣ 3፡ ደረጃውን ያሟላ

4፡ ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ

| ስታንዳርድ | የተሰጠ የውሳኔ ውጤትና ደረጃ | በኢንስፔክተሮቹ የተሰጠ አስተያየት |
|---|---|---|
| 1. ግብዓት /25%/ | | |
| **ስታንዳርድ 1፡-** ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል።/4%/ | | |
| **ስታንዳርድ 2፡-** ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል።/4%/ | | |
| **ስታንዳርድ 3፡-** ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል።/4%/ | | |
| **ስታንዳርድ 4፡-** ትምህርት ቤቱ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ የመማር - ማስተማር አካባቢ ፈጥሯል። | | |
| **ስታንዳርድ 5፡-** ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል።/3%/ | | |

| ስታንዳርድ | የተሰጠ የውሳኔ ውጤትና ደረጃ | አስተያየት |
|---|---|---|
| 1.3 - **የትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴቶችና እቅዶች** | | |
| **ስታንዳርድ** 6፡- ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት።/3%/ | | |
| **ስታንዳርድ 7፡-** ትምህርት ቤቱ አሳታፊ የት/ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፣/3%/ | | |
| **2. ሂደት/35%/** | | |
| **ስታንዳርድ** 8፡- የተማሪዎች መማርና ተሳትፎ ጎልብቷል። /3%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 9፡- ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል።/3%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 10፡- ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው በጎ አመለካከት አላቸው።/2%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 11፡- መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደ፣ በአመቺ የትምህርት መርጃዎች የተደገፈ እና ከፍተኛ የትምህርት ውጤትን ለማስገኘት አልሞ የተዘጋጀ ነው።/3%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 12፡- መምህራን የሚስተምሩትን የትምህርት ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ። /3%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 13፡- የት/ቤቱ አመራርና መምህራን ለሁሉም ተማሪዎች ተስማሚና ዘመናዊ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ጎልብቷል።/3%/ | | |

| ስታንዳርድ | የተሰጠ የውሳኔ ውጤትና ደረጃ | አስተያየት |
|---|---|---|
| **ስታንዳርድ 13፡-** የት/ቤቱ አመራርና መምህራን ለሁሉም ተማሪዎች ተስማሚና ዘመናዊ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ጎልብቷል።/3%/ | | |
| **ስታንዳርድ 14፡-** ትምህርት ቤቱ ለሴቶችና እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።/2%/ | | |
| **ስታንዳርድ 15፡-** መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር /CPD/ ተግባራዊ አድርገዋል። /2%/ | | |
| **ስታንዳርድ 16፡-** የትምህርት ቤቱ አመራር ፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልማት ሠራዊት በመደራጀት በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው። /3%/ | | |
| **ስታንዳርድ 17፡-** ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው፣አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ መሆኑን መምህራን ይገመግማሉ፣ግብረ መልስ ይሰጣሉ፣ ያሻሽላሉ።/2%/ | | |
| **ስታንዳርድ 18፡-** ተማሪዎች በትክክል ተመዝነዋል፣ አስፈላጊው ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል። /3%/ | | |
| **ስታንዳርድ 19፡-** የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች ያቀዱቸው እቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላሉ። /2%/ | | |
| **ስታንዳርድ 20፡-** ትምህርት ቤቱ የሰው ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል። /2%/ | | |

| ስታንዳርድ | የተሰጠ የውሳኔ ውጤትና ደረጃ | አስተያየት |
|---|---|---|
| **ስታንዳርድ** 21፡- ትምህርት ቤቱ ከተማሪ ወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው።/2%/ | | |
| **3. ውጤት (Output) /40%/** | | |
| **ስታንዳርድ** 22.፦ ትምህርት ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት/Internal efficiency/ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።/10%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 23፡- የተማሪዎች የክፍል ፣ የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች ከሚጠበቀው ሃገራዊና ክልላዊ መመዘኛ ጋር ሲነፃፀር ተሻሽሏል። /8%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 24፡- ተማሪዎች በሥነ-ስርዓት የታነጹ፣ መልካም እሴቶችና ባህልን የተላበሱ፣ አካባቢን የመንከባከብ ኃላፊነት የሚሰማቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።/10%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 25፡- በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ተፈጥሯል፣ ኪራይ ሰብሳቢ ነትን የመታገልና የተጠያቂነት ስሜት ዳብሯል።/6%/ | | |
| **ስታንዳርድ** 26 ፡- ትምህርት ቤቱ ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል፣ /6%/ | | |

# ሀገር አቀፍ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን አፈፃፀም መመሪያ


መስከረም 2006 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

# ማውጫ

ገፅ

መግቢያ ........ 1
1 አጭር ርዕስ ........ 3
2 አውጭው ባለስልጣን ........ 3
3 ትርጓሜ ........ 3
4 የተፈጻሚነት ወሰን ........ 4
5 የጾታ አገላለጽ ........ 4
6 የመመሪያው ዓላማዎች ........ 4
7 የኢንስፔክሽን መሪ መርሆዎች ........ 5
8 የመመሪያው አስፈላጊነት ........ 6
9 የአፈጻጸም መመሪያው ጥቅሞች፡- ........ 6
10 የኢንስፔክሽን ሂደት ........ 7
10.1 ቅድመ ኢንስፔክሽን ........ 7
10.1.1 ለኢንስፔክሽን ሥራ የትምህርት ቤቶች አመራረጥ፡- ........ 7
10.1.2 የኢንስፔክሽን ቡድን አመሰራረት፡- ........ 7
10.1.3 ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት፡- ........ 7
10.1.4 የት/ቤት ደረጃ ምደባ ስለማካሄድ፡- ........ 8
10.2 በኢንስፔክሽን ወቅት ........ 8
10.2.1 የኢንስፔክሽን ሥራ አጀማመር፡- ........ 8
10.2.2 መረጃ አሰባሰብ፡- ........ 8
10.2.3 የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 9
10.2.4 የኢንስፔክሽን ትግበራን በተመለከተ ክትትል ስለማድረግ፡- ........ 9
10.3 ድህረ ኢንስፔክሽን ........ 9
10.3.1 የተጠቃለለ የትምህርት ቤቶች የአፈፃፀም ምዘና ደረጃ አሰጣጥ፡- ........ 9
10.3.2 የኢንስፔክሽን ማጠቃለያ ሪፖርት አቀራረብ፡- ........ 10
11 በአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዘርፍ የፈጻሚ/አስፈጻሚ አካላት ኃላፊነትና ተግባር ........ 11
11.1 በትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት፡- ........ 11
11.2 የክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኢንስፔክሽን ዘርፍ፡- ........ 12

11.3 የዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ ኢንስፔክሽን ዘርፍ፡- 13
11.4 የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኢንስፔክሽን ዘርፍ፡- 14
11.5 ትምህርት ቤቶች፡- 14
12 የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ፕሮፋይል 15
13 የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነ-ምግባር ፡- 16
14 የቅሬታ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ፡- 18
15 በመመሪያው ያልተሸፈኑ ጉዳዮች 18
16 መመሪያውን ስለማሻሻል 18
17 የተፈጻሚነት ጊዜ 18

## መግቢያ

መንግስት ሰፊ መሰረት ያለው ፈጣን፣ ቀጣይነትና ፍትሃዊነቱ የተረጋገጠ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ልማትን የማፋጠንና ድህነትን የማስወገድ ዓላማ ያለው ሲሆን ባለፉት ዓመታት የአገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለመምራት የሚያስችል የረጅምና የመካከለኛ ዘመን የልማት እቅድ ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ነው።

በሀገር ደረጃ የተነደፉ የልማት እቅዶችን ለመተግበር በሁሉም ደረጃ የሚያስፈልገውን የማስፈፀም አቅም ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ትምህርትን በየደረጃው ማስፋፋትና ጥራቱን ማረጋገጥ የግድ ሆኖ ተገኝቷል። በትምህርቱ ዘርፍ የቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ አጠቃላይ ትምህርት ነው። ስለሆነም በ1986 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በመቅረፅ እና ፖሊሲውን ስራ ላይ ለማዋል ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በተነደፉ/በተዘጋጁት ተከታታይ የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች የትምህርት ተደራሽነትን፣ፍትሀዊነትን እና አግባብነትን በየደረጃው ከማሳደግ አኳያ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል።

ትምህርትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ጥራቱን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስልቶችን በመንደፍ በትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማሩ አጋዥ የሆኑትን የትምህርት ግብዓት፣ ሂደትና ውጤት በማሻሻል የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለማጎልበት በ1999 ዓ.ም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ተቀርፆ በሁሉም የሀገራችን ክልሎች በመተግበር ላይ ነው። ፓኬጁ የመምህራን ልማት፤ የሥርዓተ ትምህርት፣ መጻህፍትና ምዘና፤ የትምህርት ቤት መሻሻል፣ የትምህርት አመራርና አስተዳደር፤ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲሁም የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር መርሀ ግብሮችን አካቷል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመርሀ ግብሮቹን አፈጻጸም ለመገምገም የሚያስችል የኢንስፔክሽን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኗል።

አለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት በትምህርት ቤቶች የሚካሄድ ተከታታይ ኢንስፔክሽን የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻልና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። የኢንስፔክሽን የግምገማ ውጤት የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በተለይም ደግሞ የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሀ ግብር አተገባበርን በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን በዚህም ትምህርት ቤቶች ቀዳሚ የትኩረት ጉዳዮችን ለመለየት እንዲረዳቸው የሚያካሂዱት ግለ-ግምገማ ተገቢውን ሂደት የተከተለ መሆኑን ለመፈተሽና የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመጠቀም የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል።

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በመንግስት የተሰጠውን ሃላፊነት መሰረት በማድረግ በ2004 ዓ.ም የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬትን ያቋቋመ ሲሆን የዚህ የስራ ክፍል ሃላፊነት ከክልል/ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፤ በነሱም በኩል ከዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያዎችና ከወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ በየደረጃው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን ስራ ለማከናወን የሚረዳ ሥርዓት መዘርጋት፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት እንደ አስፈላጊነቱ ሙሉ፣ ከፊል፣ ተከታታይና የተወሰነ ጉዳይ ላይ ያተኮረ የኢንስፔክሽን ስራ ሊያካሂድ ይችላል።

በዚሁ መሠረት ትምህርት ሚኒስቴር ት/ቤቶች ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ ከግብዓት፣ ከሂደትና ውጤት አኳያ ለመመዘን የሚያስችል ሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ያዘጋጀ ሲሆን ማዕቀፉም በትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን በምን መልክ መካሄድ እንዳለበት አጠቃላይ ሁኔታዎችን ሲያመለክት፤ይህ ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን መመሪያ የማዕቀፉ ማሟያ ከመሆኑ በተጨማሪ በውስጡ የኢንስፔክሽን ሂደት፣ የአፈጻጸም ስልቶች፣ ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር እስከ ት/ቤት ድረስ ያሉ አካላት ሃላፊነትና የሥራ ድርሻ እንዲሁም የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነምግባርን በውስጡ አካቶ ይዟል።

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የትምህርት ሚኒስቴር ሀገር አቀፍ የአጠ/ትም/ኢንስፔክሽን አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር - - -1/2006 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2 አውጭው ባለስልጣን

የትምህርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህን የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል።

## 3 ትርጓሜ

በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

3.1 "ኢንስፔክሽን" ማለት" - በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የሚያስችል የተቋማት ግምገማ በማካሄድ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግና የተጠያቂነት ስርዓትን የሚያሰፍን የሥራ ዘርፍ ነው።

3.2 "ግብዓት" ማለት - በትምህርት ተቋማት ለመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የሰው፣ የገንዘብና የቁሳቁስ...ወዘተ ሀብትን የሚመለከት ነው።

3.3 "ሒደት" ማለት - በትምህርት ተቋማት ውስጥ የተማሪዎችን ውጤትና ስነምግባር ለማሻሻል የሚከናወን ተግባር ነው ።

3.4 "ውጤት " ማለት በመማር ማስተማር ሂደትና በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ መስተጋብር የሚመጣ የተማሪዎች የእውቀት፣ክህሎት እና አመለካከት አወንታዊ ለውጥ ነው።

3.5 "ግለ-ግምገማ" ማለት የትምህርት ተቋማት አፈጻጸማቸውን ወይም ያሉበትን ደረጃ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያዩበት አግባብ ማለት ነው።

3.6 "የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ" ማለት ትምህርት ቤቶችን ከግብዐት፣ ከሂደትና ከውጤት አኳያ በተቀመጡ ስታንዳርዶችና አመልካቾች መሠረት በመለካት ደረጃ የመስጠት ተግባር ነው።

3.7 "የትኩረት መስኮች" ማለት የትምህርት ኢንስፔክሽን በዋናነት የሚያተኩርባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ማለት ነው።

3.8 "ስታንደርድ" ማለት - ሁሉንም ት/ቤቶች በአንድ አይነት ይዘት ፣ አሰራር ስረዓትና በተገኘ ውጤት ላይ ለመለካት የተቀመጠ መስፈርት ነው።

3.9 "አመልካች " ማለት - ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ የመለኪያውን ቁልፍ ባህርይ የሚያመለክት ማለት ነው።

## 4 የተፈጻሚነት ወሰን

የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን መመሪያ በመላው ኢትዮጵያ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ማለትም በአጸደ ሕጻናት ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ፣ በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና በመሰናዶ ት/ቤቶች ፣ በአማራጭ መሰረታዊ የትምህርት ማዕከላት የመንግስት ፣ የህዝብና የግልና የሌሎች ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ይህ የኢንስፔክሽን መመሪያ አይመለከታቸውም።

ይህ መመሪያ የት/ቤቶችን የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ እንቅስቃሴ ለመገምገም በት/ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ በዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያዎችና በወረዳ ትምህርት ቤቶች በተቋቋሙ የኢንስፔክሽን የሥራ ዘርፎች ተፈፃሚ ይሆናል።

## 5 የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ ቃል ወይም አባባል የሴትንም ጾታ ያካትታል።

## 6 የመመሪያው ዓላማዎች

የመመሪያው ዋና ዓላማ የትምህርት ጥራትንና ውጤታማነትን በማረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተማሪዎችን ውጤትና ሥነምግባር ማሻሻል ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አካቷል፡-

6.1 ትምህርት ቤቶች የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ/ ተፈላጊ የአፈጻጸም ደረጃ ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ፣

6.2 ት/ቤቶችን በደረጃ መመደብና ሞዴል ት/ቤቶች የጉድኝት ማዕከላት ሆነው ሌሎችን እንዲያበቁ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣

6.3 የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በተለይም የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ-ግብርን አተገባበርና ውጤታማነት በመፈተሽ ለፖሊሲ አውጭዎችና ለትምህርት ባለሙያዎች መረጃ ለመስጠት፣

6.4 በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ስራ ትምህርት ቤታቸው ስላለበት ደረጃ ለወላጆች፣ መምህራንና ተማሪዎች መረጃ ለመስጠትና ተሳትፏቸውን ለማጎልበት፣

6.5 ትምህርት ቤቶች ሶስቱን የልማት አቅሞች/ የድርጅት፣ የመንግስትና የህዝብ ክንፎች/ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ተጣምረው በትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ ብቃት፣ አግባብነትና ጥራት ላይ መረጃ በመስጠት ተሳትፏቸውን በማጎልበት የተማሪዎችን ውጤትና ስነምግባር እንዲያሻሽሉ ለማድረግ፣ የትምህርት ቤቶች መሻሻልና አፈጻጸምን አስመልክቶ በየደረጃው የተጠያቂነት ስርዓት ለማስፈን ነው፡፡

# 7 የኢንስፔክሽን መሪ መርሆዎች

የኢንስፔክሽን ሂደት የሚከተሉትን መሠረታዊ መሪ መርሆዎችን ይከተላል፡፡ እነርሱም፡-

7.1 ነጻ ወይም የት/ቤቱ አካል ባልሆኑ የትምህርት ኢንስፔክተሮች ይካሄዳል፡፡

7.2 የአንድን ትምህርት ቤት አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ለመገምገም ተጨባጭ፣ ወጥነትና ቀጣይነት ባላቸው መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ይካሄዳል፡፡

7.3 ግምገማው ሁሉንም ት/ቤቶች ባካተተ መልኩ በተቀመጡት ግልጽ ስታንዳርዶችና መስፈርቶች መሠረት የሚካሄድ እንጂ የኢንስፔክተሮች ግላዊ አመለካከት መንፀባረቅ የለበትም፡፡

7.4 ገንቢ እና ለጉዳዮች ትኩረት የሚሰጥ ፤ የተከናወኑ መልካም ተግባራትን የሚያበረታታና እጥረቶችን ለይቶ በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ የሚሰጥበት ተግባር ነው፡፡

7.5 የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ስብእና በማክበር ይከናወናል፡፡

7.6 የግምገማ ተግባራት ት/ቤቶች እንደ ተቋም ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ያተኮረ እንጂ በግለሰቦች የሥራ አፈጻጸም ላይ መሆን አይገባውም፡፡

## 8 የመመሪያው አስፈላጊነት

ጥራትን የማረጋገጥ ሂደት ለትምህርት ቤቶች መሻሻል መሠረታዊ ሲሆን ኢንስፔክሽን አንዱ የጥራት ማረጋገጫ ዓይነት ነው። በትምህርት ቤቶች የሚካሄደው ኢንስፔክሽን የመማር ማስተማር መስተጋብሩ ጥራቱን በጠበቀና የተማሪዎችን ውጤትና ስነ-ምግባር ማሻሻል ላይ ያነጣጠረ እንዲሁም በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ እና ያልተዛባ ምዘና የሚሰጥበት ተግባር ነው ።

በመሆኑም ሁሉም ትምህርት ቤቶች ሊያሟሉት የሚገባ ዝቅተኛ /ተፈላጊ/ የብቃት ደረጃዎችን በመወሰን ትምህርት ቤቶችን በመልካም አፈጻጸማቸው ለማበረታታት ወይም ላሳዩት ደካማ አፈጻጸም ት/ቤቱና በየደረጃው የሚመለከታቸው አካላት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት ለመፍጠር የትምህርት ቤት ኢንስፔክሽን አስፈላጊ ነው።

## 9 የአፈጻጸም መመሪያው ጥቅሞች፡-

9.1 ትምህርት ቤቶች የሚጠበቅባቸውን የአፈጻጸም ደረጃ በግልጽ ለማሳየት፣

9.2 ትምህርት ቤቶች ችግሮችን በመለየት ለመሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለመጠቆም፣

9.3 ትምህርት ቤቶች ለመሻሻል ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች መለየት እንዲችሉ ለመርዳት፣

9.4 የኢንስፔክተሮችን ልምድና ሙያ በመጠቀም በኢንስፔክተሮች፣ በትምህርት ቤት መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች መካከል የሚደረጉ ገንቢ ውይይቶችን ለማሳለጥ፣

9.5 ትምህርት ቤቶች አፈጻጸማቸውን መገምገም እንዲችሉ ክህሎታቸውን ለማዳበር፣

9.6 በት/ቤቶች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር፣

9.7 በየደረጃው ያሉ አመራር ለት/ቤቶች የሚሰጡትን ድጋፍ ለማመላከት ነው።

# ክፍል ሁለት

## 10 የኢንስፔክሽን ሂደት

የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች የትምህርት ቤት አካባቢን፣ የትምህርት ቤቱ አመራርና አስተዳደርን ፣ መማር-ማስተማርን ፣ ከወላጆችና ከህብረተሰቡ ጋር ያለ ግንኙነትን እና የተማሪዎች ውጤትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ከግብዓት ፣ ከሂደት እና ከውጤት ጋር የተሳሰሩ ናቸው። የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን የሚከተሉትን ሂደቶች በትኩረት መከተልና መተግበር ይገባል።

## 10.1 ቅድመ ኢንስፔክሽን

### 10.1.1 ለኢንስፔክሽን ሥራ የትምህርት ቤቶች አመራረጥ፡-

በሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው የሁሉም ትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ቢያንስ በሦስት አመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል። በየዓመቱ ለሚካሄደው የኢንስፔክሽን ስራ የሚመረጡ ትምህርት ቤቶች በክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፣የዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያዎችና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች በሚያደርጉት ምክክር ይሆናል፡፡ አመራረጡ የትምህርት ቤቶችን ብዛት፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና / ገጠር፣ ከተማ/ የትምህርት ቤቶችን የአፈፃፀም ደረጃ ያገናዘበ መሆን ይጠበቅበታል። የየክልሉ/ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ የተመረጡ ትምህርት ቤቶችን አጠቃላይ መረጃ ለትምህርት ሚኒስቴር ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

### 10.1.2 የኢንስፔክሽን ቡድን አመሰራረት፡-

የክልል ትምህርት ቢሮ የዞን/የክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ/ጽ/ቤት እና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የኢንስፔክሽን ዘርፍ አንድን ትምህርት ቤት ለመገምገም ቢያንስ ሁለት አባላት ያሉት የኢንስፔክሽን ቡድን ማዋቀር ይጠበቅበታል፡፡ የኢንስፔክሽን ቡድኑ በአንድ የትምህርት ተቋም ለሶስት ወይም ለአራት ቀናት ስራዎችን ሲያከናውን ይቆያል። ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ/አንዷ በአስተባባሪነት ይሰየማል/ትሰየማለች።

### 10.1.3 ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት፡-

የኢንስፔክሽን ስራ የሚከናወንበት ት/ቤት ከሁለት ሳምንት በፊት እንዲያውቁት ይደረጋል።ለኢንስፔክሽን ስራም እንደ ግብዓትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ አሰፈላጊ የሆኑ ዋና

ዋና መረጃዎችን ት/ቤቱ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት አስቀድሞ ማቅረብ አለበት። ት/ቤቱ ያቀረበውን መረጃዎች ኢንስፔክተሮች በአግባቡ ተንትነው በኢንስፔክሽን ወቅት ስራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል።

### 10.1.4 የት/ቤት ደረጃ ምደባ ስለማካሄድ፡-

እያንዳንዱ ት/ቤት በሀገር አቀፍ የት/ቤቶች ደረጃ ምደባ ማዕቀፍ መሠረት በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ወይም መጀመሪያ ግለ-ግምገማ በማካሄድ ለትምህርት ቤቱ ደረጃ መስጠት ይጠበቅበታል። ኢንስፔክተሮች በኢንስፔክሽን ጊዜ የትምህርት ቤቶቹን ግለ-ግምገማውንና ደረጃ ምደባውን ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ።

## 10.2 በኢንስፔክሽን ወቅት

### 10.2.1 የኢንስፔክሽን ሥራ አጀማመር፡-

የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ትምህርት ቤት እንደደረሱ ከትምህርት ቤቱ ር/መምህር/ት እና ሌሎች የትምህርት ቤቱ አመራሮች ጋር በመገናኘት ስለሚያከናዉኑት የኢንስፔክሽን ሥራ ዓላማና አጠቃላይ ሁኔታ ገለፃ ያደርጋሉ። የትምህርት ቤቱ አመራር የት/ቤቱን ነባራዊ ሁኔታ በተመለከተ አጭር ገለጻ ያቀርባሉ። ኢንስፔክተሮቹ በኢንስፔክሽን ወቅት በየጊዜው ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ት ጋር በመገናኘት ከስራው ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥያቄዎች እና ችግሮችን በአፋጣኝ ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ።

### 10.2.2 መረጃ አሰባሰብ፡-

ኢንስፔክተሮች ስለ እያንዳንዱ ስታንዳርድ አፈፃፀም ትክክለኛ ውሣኔ ላይ ለመድረስ እንዲያስችላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን ትምህርት ቤቱ ውስጥ የተለያዩ መረጃዎችን/ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ያሳልፋሉ። የሚሰበሰቡት መረጃዎች/ማስረጃዎች በኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ውስጥ የተቀመጡትን ስታንዳርዶች መሠረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል።

## 10.2.3 የክፍል ውስጥ ምልከታ

10.2.3.1 ለኢንስፔክሽን ስራ የተሰማራው ቡድን ከመማር ማስተማር ተግባር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ተግባራት በትኩረት ማከናወን ይጠበቅበታል። በአንድ ጊዜ በሁሉም ክፍሎች በመገኘት ምልከታ ለማድረግ እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ በናሙናነት በተመረጡ ክፍሎችና የተወሰኑ መምህራንን የመማር ማስተማር ሂደት በመመልከት እንዲሁም በየትምህርት አይነቱ ስልት በመቀየስ ይከናወናል።ቡድኑ ለሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎችና ምልከታዎች በቅድሚያ ፕሮግራም ማስያዝ አስፈላጊ ነው።

10.2.3.2 የክፍል ምልከታው በአንድ ሙሉ የትምህረት ክፍለ ጊዜ /Period/ ይከናወናል። በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚከናወን ምልከታ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሲሆን ኢንስፔክተሩ/ሯ በክፍል ውስጥ የሚያከናውነው/የምታከናውነው ተግባር ሁሉ ሥርዓትና አክብሮት ያልተለየውና የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያውክ መሆን አለበት።

## 10.2.4 የኢንስፔክሽን ትግበራን በተመለከተ ክትትል ስለማድረግ፡-

**ሀ. የመጀመሪያ ኢንስፔክሽን አገልግሎት አሰጣጥ፡-**

እያንዳንዱ ት/ቤት ቢያንስ በሶስት አመት አንድ ጊዜ በኢንስፔክሽን ቡድን መታየት ይኖርበታል።

**ለ. የድጋሚ ኢንስፔክሽን አገልግሎት ስለማግኘት፡-**

አንድ ትምህርት ቤት ደረጃውን ካላሟላ ከአንድ አመት በኋላ እንደገና በኢንስፔክሽን ይታያል።

# 10.3 ድህረ ኢንስፔክሽን

## 10.3.1 የተጠቃለለ የትምህርት ቤቶች የአፈፃፀም ምዘና ደረጃ አሰጣጥ፡-

ኢንስፔክተሮች ለየስታንዳርዱ የተቀመጡ አመልካቾችን በመጠቀምና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር የትምህርት ቤቱን የአፈጻጸም ደረጃ የሚያሳይ ትክክለኛ ውሳኔ/ብይን መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ የሰጡትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ በአራት የደረጃ መለኪያዎች ይመዝናሉ።መመዘኛዎችም፡-

ሀ. ከ50% በታች ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 1 ላይ ይመደባል፣

ለ. ከ50% - 69.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 2 ላይ ይመደባል፣

ሐ. ከ70% - 89.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 3 ላይ ይመደባል፣

መ. ከ90% - 100% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 4 ላይ ይመደባል፣

በዚህም መሰረት ኢንስፔክተሮች ሁሉንም ስታንዳርዶች በተቀመጡ አግባቦች መሰረት በመፈተሽ ሙያዊ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

## 10.3.2 የኢንስፔክሽን ማጠቃለያ ሪፖርት አቀራረብ፡-

### 10.3.2.1 የቃል ግብረ-መልስ

የኢንስፔክሽን ስራ እንደተጠናቀቀ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ ሱፐርቫይዘርና ሌሎች የሚመለከታቸው አመራር እንዲሰባሰቡ በማድረግ የኢንስፔክሽን ቡድኑ ያስቀመጣቸውን ውሳኔዎች /Judgements/፤ ለትምህርት ቤቱ መሻሻል ጠቃሚ አስተያየቶች በቃል ያቀርባል። በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ ተዘጋጅቶ በሚቀመጥ አስተያየት መስጫ ካርድ ወይም መዝገብ ላይ ዋና ዋና አስተያየቶችን ማስፈር ይገባል።

### 10.3.2.2 የጽሁፍ ሪፖርት አቀራረብ፡-

ሀ/ ንስፔክሽን ተግባር ከተጠናቀቀ ሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የጽሁፍ ሪፖርት በአግባቡ ተዘጋጅቶ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለተሰጠበት ትምህርት ቤት እና በየደረጃው ኢንስፔክተሮቹ ተጠሪ ለሆኑባቸው ለወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤት፤ ለዞን፤ ለክልሉ ት/ቢሮ ኢንስፔክሽን ዘርፍና ለትምህርት ሚኒስቴር አጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት መቅረብ አለበት።

ለ/ ኢንስፔክሽን ሪፖርት አቀራረብ የተመጠነ፣ ግልጽና በመረጃ ላይ ተመስርቶ በጥንቃቄ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል።

ሐ/ ኢንስፔክሽን ቡድን አባላት በሪፖርት ዝግጅት፣ጥራትና ተገቢነት ላይ የጋራ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት አለባቸው።

መ/ ኢንስፔክሽን ሪፖርት እንደ አስፈላጊነቱ በድረ-ገጽ /Web site/ አማካኝነት እንዲሰራጭ ይደረጋል።

# ክፍል ሶስት

# አደረጃጀት

## 11 በአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዘርፍ የፈጻሚ/አስፈጻሚ አካላት ኃላፊነትና ተግባር

### 11.1 በትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት፡-

11.1.1 ሀገራዊና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ሀገራዊ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ፣ መመሪያዎችን የማዘጋጀትና የማሻሻል ሥራዎችን ያከናውናል።

11.1.2 ከክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ ጋር በመቀናጀት ወይም በተናጠል እንደ አስፈላጊነቱ የኢንስፔክሽን ሥራ ያከናውናል።

11.1.3 ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤ እንደ አስፈላጊነቱም በየክልሉ ለሚገኙ የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች አቅጣጫ አመልካች የሆነ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል።

11.1.4 በክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ ስለሚከናወኑ አመታዊ የኢንስፔክሽን ስራዎች የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ስምምነት ላይ ይደርሳል፡

11.1.5 ከየክልሉ/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ የሚከናወኑ የኢንስፔክሽን ሥራዎች በሀገር አቀፉ ማዕቀፍ (Framework) መሠረት እየተከናወነ ስለመሆኑና ወቅታዊ ሪፖርቶች ተዘጋጅተው እንዲላኩ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል።

11.1.6 ከየክልሉ የሚላኩ ሪፖርቶችንና ዳይሬክቶሬቱ በመስክ በመገኘት ያጠናቀራቸውን መረጃዎች በማሰባሰብ አመታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል።

11.1.7 ከሁሉም ክልሎች/ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ በየሩብ ዓመቱ ተዘጋጅተው የሚላኩ ሪፖርቶችን በማጠናቀርና በመተንተን የኢንስፔክሽን ተግባር ያስገኘውን ጥቅም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል።

11.1.8 መልካም ተሞክሮዎች በመቀመርና በመለየት እንዲስፋፋ ያደርጋል።

11.1.9 የኢንስፔክሽን መረጃ ይሰብስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ወቅታዊነቱን ይጠብቃል።

11.1.10 በኢንስፔክሽንና በሌሎች የተለያዩ መንገዶች የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በተከናወኑ ተግባራት ላይ ከአለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጋር በማመዛዘን ጥናትና ምርምር ያከናውናል።

## 11.2 የክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኢንስፔክሽን ዘርፍ፡-

11.2.1. በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት የኢንስፔክሽን ተግባር ያከናውናል።

11.2.2. የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ተግባር በአመታዊ የዕቅድ መርሃግብር መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል።

11.2.3. የኢንስፔክሽን ሥራዎችን የተመለከተ የየሩብ ዓመት ሪፖርት ለትምህርት ሚኒስቴር ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ይልካል።

11.2.4. በክልሉ/ከተማ አስተዳደር ለሚገኙ የዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያና የወረዳ ት/ቤቶች ፅ/ቤት የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ስልጠና ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፣ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል።

11.2.5. በዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያና በወረዳ ትምህርት ፅ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑ የኢንስፔክሽን ተግባራት በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

11.2.6. ከዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያና ከወረዳ ትምህርት ፅ/ቤት በየወሩ እየተዘጋጁ የሚቀርቡ የኢንስፔክሽን ሪፖርቶች ተገቢነትና የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፤

11.2.7. ከሁሉም ዞን/ክፍለ ከተማ ኢንስፔክሽን ዘርፍ የሚላኩ ሪፖርቶችን በማጠናቀርና በመተንተን የኢንስፔክሽን ተግባር ያስገኘውን ጥቅም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል።

11.2.8. መልካም ተሞክሮዎች በመቀመርና በመለየት እንዲስፋፉ ያደርጋል።

11.2.9. የኢንስፔክሽን መረጃ ይሰብስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ወቅታዊነቱን ይጠብቃል።

11.2.10. በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ተግባር ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያከናውናል።

## 11.3 የዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ ኢንስፔክሽን ዘርፍ፡-

11.3.1 በዞኑ/በክፍለ ከተማው ውስጥ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት የኢንስፔክሽን ሥራ የማከናወን ሃላፊነት አለበት።

11.3.2 በተመሳሳይ ሁኔታ ከክልሉ በተላከው ሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት በወረዳ ደረጃ የትምህርት ኢንስፔክሽን ሥራ ስለመከናወኑ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

11.3.3 ከክልሉ ጋር በተደረገ ስምምነት በተዘጋጀው አመታዊ የኢንስፔክሽን ፕሮግራም መሰረት ኢንስፔክሽን መካሄዱን ያረጋግጣል።

11.3.4 ወቅታዊ የኢንስፔክሽን ሪፖርቶችን በየወሩ በቋሚነት ለክልል ትምህርት ቢሮ ኢንስፔክሽን ዘርፍ ይልካል።

11.3.5 በወረዳዎች የሚከናወኑ የኢንስፔክሽን ስራዎች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

11.3.6 በኢንስፔክተሮች አማካኝነት የሚሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች ሥራ ላይ እንዲውሉ በወረዳዎች በኩል ክትትል የሚደረግ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል።

11.3.7 ከሁሉም ወረዳዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ በየወሩ ተዘጋጅተው የሚላኩ ሪፖርቶችን በማጠናቀርና በመተንተን የኢንስፔክሽን ተግባር ያስገኘውን ጥቅም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል።

11.3.8 መልካም ተሞክሮዎች በመቀመርና በመለየት እንዲስፋፉ ያደርጋል።

11.3.9 የኢንስፔክሽን መረጃ ይሰብስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ወቅታዊነቱን ይጠብቃል።

11.3.10 በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ተግባር ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያከናውናል።

## 11.4 የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኢንስፔክሽን ዘርፍ፡-

11.4.1 ወረዳው ለሁሉም አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ፣አፀደ ህፃና የመጀመሪያ ደረጃ እንዲሁም እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት አለበት።

11.4.2 ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በዞን/ክፍለ ከተማ ደረጃ በሚደረግ አመታዊ የኢንስፔክሽን ተግባር ዕቅድ መሠረት ሃላፊነቱን ይወጣል።

11.4.3 በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት በትምህርት ተቋማት ኢንስፔክሽን በማከናወን ወርሃዊ ሪፖርት ለዞን/ክፍለ ከተማ የኢንስፔክሽን ዘርፍ ይልካል፤ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።

11.4.4 የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ለትምህርት ቤቱ መሻሻል የሚሰጧቸው አስተያየቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የጉድኝት ማዕከሉ ሱፐርቫይዘሮችና የትምህርት ቤቶች አመራሮች በአግባቡ መፈፀማቸውን ክትትል ያደርጋል ፣ ይቆጣጠራል ።

11.4.5 መልካም ተሞክሮዎች በመቀመርና በመለየት እንዲስፋፉ ያደርጋል።

11.4.6 የኢንስፔክሽን መረጃ ይሰብስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ወቅታዊነቱን ይጠብቃል።

11.4.7 በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ተግባር ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያከናውናል።

## 11.5 ትምህርት ቤቶች፡-

11.5.1 የራሳቸውን ግለ-ግምገማና የት/ቤታቸውን ደረጃ ምደባ በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ወይም መጀመሪያ ያከናውናሉ።

11.5.2 በየደረጃው የትምህርት ቤቱን የትምህርት ጥራት ለማሻሻልና ለማረጋገጥ ወደ ተቋሙ ከሚመጡ ባለሙያዎች ጋር ይተባበራሉ፤ አስፈላጊውን መረጃ የመስጠትና ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሃላፊነት አለባቸው።

11.5.3 በኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ለትምህርት ቤቱ መሻሻል ሲባል የተሰጡትን አስተያየቶች በሥራ ላይ ያውላሉ፣

11.5.4 የተማሪዎች መማርና ውጤት ጥራቱን ጠብቆ እንዲሰጥ ያደርጋሉ።

### 11.5.5 በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ዙሪያ የተግባር ጥናትና ምርምር ያከናውናል።

# 12 የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ፕሮፋይል

12.1 የትምህርት ኢንስፔክተሮች በፌዴራል፣ በክልል ፣ ከተማ አስተዳደር፣ በዞን፣ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ በተቋቋሙ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዘርፎች ተመድበው የሚሠሩ ናቸው። ባለሙያዎቹ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል ትምህርት ቤቶች ያሉባቸውን ጠንካራና ደካማ ጐኖች በመለየት አስፈላጊውን ግብረ-መልስ በመስጠት የትምህርት ጥራትንና የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል በዋናነት የሚጠቀስ ነው። በመሆኑም ይህንን ከፍተኛ ሃላፊነት በሚጠይቅ ስራ ላይ የሚመደቡት የትምህርት ኢንስፔክተሮች ምልመላና ስምሪት በጥንቃቄ መከናወን የሚገባው ተግባር ነው። ስለሆነም በየደረጃው ባሉ የትምህርት አስተዳደር እርከኖች የሚመደቡት የትምህርት ኢንስፔክተሮች ምርጫ በሚከተሉት መስፈርቶች መከናወን ይኖርበታል።

ሀ/ በማንኛውም የትምህርት መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው/ያላት፣

ለ/ በመምህርነት ወይም በርዕሰ መምህርነት፣ በትምህርት ሱፐርቫይዘርነት ወይም በትምህርት አመራር ቢያንስ አምስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላት፣

ሐ/ በመምህርነት ወይም በርዕሰ መምህርነት፣ በሱፐርቫይዘርነት ወይም በትምህርት አመራር የላቀ የሥራ አፈፃፀም ያለው/ያላት፣

መ/ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው/ያላት፣

ሠ/ ቢቻል በትምህርት ኢንስፔክሽን የስልጠና ኮርሶች ላይ የተሣተፈ/የተሣተፈች ቢሆን/ብትሆን ይመረጣል።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የትምህርት ኢንስፔክተሮች በሙያቸው የላቀ እውቀትና ክህሎት እንዳላቸው በምልመላው ወቅት መረጋገጥ ይኖርበታል። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ረ/ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ ልዩ ልዩ የትምህርት ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ያላቸው፣

ሰ/ በትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ላይ ከፍተኛ እውቀትና ግንዛቤ ያላቸው፣

ሸ/ በሃገሪቱ በስራ ላይ ባሉ የሥርዓተ ትምህርት ቁልፍ መሣሪያዎች (የአጠቃላይ ትምህርት ስርዓተ ትምርት ማዕቀፍ፣መርሃ ትምህርት፣ዝቅተኛ ተፈላጊ የችሎታ መለኪያ (MLC)፣የይዘት ፍሰት/content flowchart/፣ ወዘተ) ላይ የላቀ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፣

ቀ/ በአሁኑ ወቅት ስላለው ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የትምህርት ትኩረት አቅጣጫዎች በቂ እውቀት ያላቸው፣

በ/ ፕሮጀክቶችን የመምራት ልምድ ያላቸው ፣

ተ/ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተን፣ ማጠናቀርና ማሠራጨት የሚችሉ ፣

ቸ/ አጠቃላይ ሪፖርት የማዘጋጀት ችሎታና ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፣

ነ/ መሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት ያላቸው፣

ከላይ የተጠቀሱት የመመልመያ መስፈርቶች እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታና በተጠና የሲቪል ሰርቪስ መመሪያና ደንብ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

# 13 የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነ-ምግባር

ማንኛውም ኢንስፔክተር፡-

13.1. በትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚያከናውናቸው/ለምታከናውናቸው ተግባራት ሙያዊ አቀራረብ እንዲኖረው/እንዲኖራት ይጠበቃል፡፡ ኢንስፔክተሩ/ሯ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር የሚያደርጋቸው/ የምታደርጋቸው ውይይቶችና ግንኙነቶች በመከባበር ላይ የተመሰረቱ ሊሆን ይገባል፣

13.2. አንድ ኢንስፔክተር በተቻለ መጠን የትምህርት ቤቱን መማር ማስተማር ሳያስተጓጉል/ሳታስተጓጉል ስራውን ለማከናወን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል/ባታል፤

13.3. በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት ሥራውን ያከናውናል/ ታከናውናለች፣

13.4. በኢንስፔክተሩ/ሯ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በተጨባጭ መረጃ ፣ ሚዛናዊነትና ፍትሃዊነትን በጠበቀ መልኩና ግልፅነት በተሞላበት ሁኔታ መከናወን ይኖርባቸዋል፣

13.5. ከትምህርት ቤቱ ጋር የሚደረግ ውይይት ት/ቤቱን የሚገነባ፣ ውጤትን ሊያመጣ የሚችል እንጂ ስህተት ፈላጊ መሆን የለበትም። በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱን የወደፊት መሻሻል የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፣

13.6. የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማሻሻል አስተያየቶች የሚኖራቸው አተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም በስራ አጋጣሚ የተሰበሰበ መረጃ ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ሃላፊነትና ግዴታ አለበት።

13.7. ኢንስፔክተሮች ገለልተኛና ውጫዊ አካል በመሆን በተጨባጭ መረጃዎች ላይ ተመስርተው አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብ የውሳኔ ሀሳቦችን ያቀርባሉ።

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

## 14 የቅሬታ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ፡-

14.1 በኢንስፔክሽን ሥራ ወቅት አንድ ትምህርት ቤት በአግባቡ አልታየሁም ብሎ ቅሬታ ካደረበት በጽሁፍ ውሳኔ በተሰጠው በ5/አምስት/ ቀናት ውስጥ በቅርብ ለሚመለከተው የወረዳ/ የዞን/ የክልል/ የከተማ ትምህርት ጽ/ቤት/ቢሮ ኢንስፔክሽን ዘርፍ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

14.2 ቅሬታውን የተቀበለው የኢንስፔክሽን ዘርፍ ከ15/ አስራ አምስት/ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተገቢውን መልስ ለአቤቱታ አቅራቢው ተቋም ማሳወቅ አለበት።

14.3 ቅሬታ የቀረበበት የኢንስፔክሽን ዘርፍ የሰጠው መልስ ካላረካው ወዲያውኑ ለአቀረበበት ዘርፍ የበላይ ኃላፊ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

14.4 የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቅሬታው በቀረበ 5 /በአምስት/ ቀናት ውስጥ መልስ መስጠት አለበት።

14.5 ቅሬታ አቅራቢው አሁንም በተሰጠው ውሳኔ ካልረካ ለሚቀጥለው የትምህርት ዘርፍ የበላይ አካል በማቅረብ እንዲታይና ውሳኔ እንዲሰጠው በማድረግ የመጨረሻው ውሳኔ ይሆናል።

## 15 በመመሪያው ያልተሸፈኑ ጉዳዮች

በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የክልሉ/ከተማ/ዞን/ወረዳ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዘርፍ በኩል እየቀረቡ እንደ አስፈላጊነቱ ውሳኔ የሚሰጣቸው ይሆናል።

## 16 መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ ተግባር ላይ ውሎ በሚቀርቡ የማሻሻያ ሃሳቦችና የዳሰሳ ጥናቶች መሠረት በትምህርት ሚኒስቴር ሊሻሻል ይችላል።

## 17 የተፈጻሚነት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ-- ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

# ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ ማዕቀፍ




**ደረጃውን የጠበቁ ትምህርት ቤቶች ለህዳሴው ጉዞ መሠረት ናቸው**

መስከረም 2006 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

1. መግቢያ .......... 1
2. የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ ዓላማዎች .......... 2
2.1. አጠቃላይ ዓላማ .......... 2
2.2. ዝርዝር ዓላማዎች .......... 2
3.የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ አስፈላጊነት .......... 3
4.የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ መርሆዎች .......... 3
5. የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ/School Classification/ስታንዳርዶች .......... 4
5.1. ግብዓት (Input) .......... 4
5.1.1. የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች ፣የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች .......... 4
5.1.2. ምቹ የመማሪያ አካባቢ .......... 5
5.1.3. የትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴቶችና ዕቅዶች .......... 6
5.2. ሂደት (Process) .......... 7
5.2..1. መማር-ማስተማር፡- .......... 7
5.2.2. ሥርዓተ ትምህርት .......... 10
5.2.3. ምዘና .......... 10
5.2.4. ክትትልና ግምገማ .......... 10
5.2.5. የትምህርት ቤት፣ የወላጆችና የማህበረሰብ አጋርነት .......... 12
5.3. ውጤት (Output) .......... 12
5.3.1. ትምህርት ቤቱና ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት .......... 12
5.3.2. የተማሪዎች ግለ-ስብዕና .......... 13
5.3.3. የመምህራንና የትምህርት አመራር ግለ - ስብዕና .......... 14
5.3.4. የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ .......... 14
6. የት/ቤቶች ደረጃ ምደባ እንዴት ይካሄዳል? .......... 15
6.1. የት/ቤት ደረጃ ምደባ የአተገባበር ሥልት፡- .......... 15
6.2. የመለኪያዎች ክብደት አሰጣጥ፡- .......... 16
6.3. የደረጃ አሰጣጥ ሂደት .......... 16
ተቀጽላ-1 (Appendix-I) ስታንዳርዶች .......... 18
ተቀጽላ-2(Appendix-II)፡ ገላጮች /Descriptors/ .......... 27
ተቀጽላ 3 (Appendix-III)የውሳኔ አሰጣጥ ቀመር ምሳሌ .......... 52
ተቀጽላ 4 (Appendix-IV) ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ .......... 56

# 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ትምህርት ለልማት ለዲሞክራሲና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ሚና የሚጫወት መሆኑን በማመኑ ለዘርፉ ዕድገት ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በመሆኑም ሁለንተናዊ ስብዕናው የተሟላ በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት እንዲሁም በመልካም ስነ-ምግባርና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የታነፀ ብቁ ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ቀርፆ ሥራ ላይ አውሏል።ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ተደራሽነትን፣ ፍትሃዊነትን፣ ውጤታማነትን፣ ተገቢነትና ጥራትን ለማረጋገጥ በተቀረፁ ተከታታይ የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች የተለያዩ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ ተደርገዋል።

የትምህርት ተደራሽነትንና ፍትሃዊነትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ያለውን የትምህርት ጥራት ችግር እንደ አንድ ቁልፍ ጉዳይ በመውሰድ በ1999 ዓ.ም. የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ተቀርፆ በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመተግበር ላይ ይገኛል።ይህም መንግስት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በየደረጃው በመፍታት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ በማሰለፍ ወደ ከፍተኛ ዕድገት ደረጃ በቀጣይነት ለመሸጋገር በላቀ ተነሳሽነት በሁሉም ዘርፍ በመተግበር ላይ ያለውን የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከማሳካት አኳያ ጥራት ያለው ትምህርትና ስልጠና ወሳኝና የማይተካ ድርሻ አለው።

በዚሁ መሠረት ትምህርት ቤቶች ፓኬጁን ተግባራዊ በማድረግ ለቀጣይ የትምህርት ደረጃዎች ድልድይ የመሆንና መሰረት የመጣል ሚናቸውን በአግባቡ ለመወጣት እስከ አሁን እያስመዘገቡ ያሉትን ውጤት በማሻሻል እና ተቋማዊ ለውጥ በማምጣት እንደ ሀገር በትምህርቱ ዘርፍ የተቀመጡ ግቦችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ትምህርት ቤቶች ያሉበትን ደረጃ በመለየት ወደ ስታንዳርዱ ለመድረስና ብሎም የላቀ ደረጃ መድረስ የሚያስችል ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ አስፈልጓል።

ይህንን በመገንዘብ ትምህርት ሚኒስቴር በሀገራችን የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ይህን ፓኬጅ በመተግበር ረገድ የሚያስመዘግቡትን አፈፃፀም ከግብዓት፣ ሂደት እና ውጤት አንፃር በመገምገም እና ደረጃ በመስጠት የተሻለ የአፈፃፀም ደረጃ ያላቸው ትምህርት ቤቶች ሞዴልነት በተለይተው የጉድኝት ማዕከል ሆነው ሌሎችን ትምህርት ቤቶች በማብቃት በሀገር

አቀፍ ደረጃ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ይህ የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል።

ይህ የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ ማእቀፍ በውስጡ መግቢያ፣አላማ፣አስፈላጊነት፣ የትምህርት ቤት ደረጃ ምደባ መሪ መርሆዎች እንዲሁም የደረጃ ምደባ ስታንዳርዶች፣ ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ የተቀመጡ አመልካቾች እና በአራት ደረጃዎች ሥር ለእያንዳንዱ አመልካች በመለኪያነት የተቀመጡ ገላጮች (Descriptors) አካቶ ይዟል።

# 2. የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ ዓላማዎች

## 2.1. አጠቃላይ ዓላማ

- ትምህርት ቤቶችን ወጥነት ያለው ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በደረጃ በመመደብ ወደሚፈለገው ስታንዳርድ እና ከዚያ በላይ እንዲበቁ በማድረግ ውጤታማነታቸውን ማሻሻል ነው።

## 2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ትምህርት ቤቶችን ወጥነት ባላቸው መስፈርቶች /ስታንዳርዶች በመመዘን በደረጃ ለመመደብ
- ትምህርት ቤቶች ያለባቸውን ጉድለቶች በመለየት ወደሚፈለገው የብቃት ደረጃ ለማድረስ፣
- ትምህርት ቤቶችን በደረጃ በመመደብ የተሻለ የአፈፃፀም ብቃት ያላቸውን በመለየት ሞዴል የሆኑት የጉድኝት ማዕከላት ሆነው ሌሎች ትምህርት ቤቶችን እንዲያበቁ ለማድረግ፣
- በየደረጃው ባሉ ትምህርት ቤቶች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ በመፍጠር የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡትን ለማበረታታት፣
- ትምህርት ቤቶች ሶስቱን የልማት ሰራዊት አቅሞች/ የድርጅት፣ የመንግስትና የህዝብ ክንፎች/ በመጠቀም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ በመስራት የት/ቤቶችን ውጤታማነት ደረጃ እንዲያሳድጉ ለማስቻል፣

## 3.የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ አስፈላጊነት

በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ ሥርዓት ተዘርግቶ ስራ ላይ መዋል የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኛል።

- ወጥ በሆነ መለኪያ ትምህርት ቤቶችን በመመዘን የትምህርት ጥራትን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማረጋገጥ፣
- ትምህርት ቤቶችን ከግብአት፣ ሂደት እና ውጤት አኳያ በመመዘን ደረጃ ለመስጠት፣
- በትምህርት ቤቶች መካከል የሚደረገውን በጐ ፉክክር በማሣደግ የተሻለ አፈፃፀምና ውጤት ያላቸውን ለበለጠ ስኬት እንዲተጉ ለማበረታታት፣
- ዝቅተኛ አፈፃፀምና ውጤት ያስመዘገቡ ትምህርት ቤቶች ድክመታቸውን በግልፅና በማያሻማ መንገድ በመጠቆም እንዲሻሻሉ ለማድረግ፣
- የተጠያቂነት ስርአት በየደረጃው ለማስፈን፣
- ትምህርት ቤቶች ያሉበትን የአፈፃፀምና የውጤት ደረጃ የሚያሣይ መረጃ ለባለድርሻ አካላትና ለህብረተሰቡ ለመስጠትና የተደራጀ የመረጃ ስርዓት ለማስፈን።

## 4.የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ መርሆዎች

የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ ሂደት የሚከተሉትን መርሆዎች ይከተላል። እነርሱም

- ግልፅ በሆነ፣ ተጠያቂነትን በሚያሰፍን፣ ወጪ ቆጣቢ በሆነና በግልፅ በተቀመጡ ስታንዳርዶች /መመዘኛዎች/ መሠረት ይካሄዳል።
- ትምህርት ቤቶች ያሉበትን የአፈፃፀም ደረጃ በግብዓት፣ በሂደት እና በውጤት ይመዝናል፣ ደረጃ ያወጣል።
- ብቃት ባላቸው፣ በሰለጠኑና ገለልተኛ በሆኑ ከት/ቤት ውጪ በሆኑ አካላት ይረጋገጣል።

# 5. የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ/School Classification / ስታንዳርዶች

## 5.1. ግብዓት (Input)

### 5.1.1. የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች ፣የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች

**ስታንዳርድ 1**

ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል።

**አመልካቾች፡-**

- ትም/ቤቱ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንፃዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ባካተተ መልኩ (በቂ ብርሃን፣ስፋት፣ወለል ወዘተ) የታነፁና የተሟሉ ናቸው፣
- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍ ፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ የመምህሩ/ሯ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን፣ ብሬይል አሟልቷል፣
- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የስፖርት ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።
- በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ ገዥ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት ወዘተ እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣

**ስታንዳርድ 2**

ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል።

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ቤት ጥቅል በጀት /Block grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤
- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የት/ቤት ድጎማ በጀት /School grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤
- ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣

- ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል፣
- ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት አሰባስቧል።
- ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ዶክመንቶች አሉት፣

**ስታንዳርድ 3**

ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል።

**አመልካቾች፡-**

- ሁሉም የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራንና መምህራን የሙያ ፈቃድና ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት አላቸው፣
- ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት፣
- ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ /Guidance and Counselling/ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ አለው፣
- ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን አሉት።

## 5.1.2. ምቹ የመማሪያ አካባቢ

**ስታንዳርድ 4**

ትምህርት ቤቱ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ የመማር - ማስተማር አካባቢ ፈጥሯል።

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣
- ትምህርት ቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ አለው፣
- በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ህንፃዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው፣
- የትምህርት ቤቱ ግቢ በአጥር ተከብሯል፣
- ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፣
- በትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር ተሟልቷል።

- ትምህርት ቤቱ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው።

**ስታንዳርድ 5**

ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል ግብዐት፣አደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት ተፈጥሯል።
- በትምህርት ቤቱ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦችን ተልዕኮዎችን የተገነዘበና ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምንርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል።
- በትምህርት ቤቱ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል።

## 5.1.3. የትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴቶችና ዕቅዶች

**ስታንዳርድ 6**

ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት።

**አመልካቾች፡-**

- የትምህርት ቤቱ አመራር ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አዘጋጅቷል፤

**ስታንዳርድ 7**

ትምህርት ቤቱ አሳታፊ የት/ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፣

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለይቷል፣
- ትምህርት ቤቱ የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቷል፣

## 5.2. ሂደት (Process)

### 5.2.1. መማር-ማስተማር፡-

### ሀ. መማር

**ስታንዳርድ 8**

የተማሪዎች መማርና ተሳትፎ ጎልብቷል።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች የተሰጧቸውን ሥራዎች በትጋት ይሰራሉ፣
- ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅና መልሶችን ለመመለስ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፣
- ተማሪዎች በ1 ለ 5 (ኔትወርክ) አደረጃጀት ተደራጅተው በትምህርታቸው ይረዳዳሉ፣
- ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ነው፣
- ተማሪዎች በህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል ተደራጅተው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ውሳኔ በመስጠት ተሳትፎ እያደረጉ ነው።

**ስታንዳርድ 9**

ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች የትምህርት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣
- ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር መፍጠር፣መመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች መፍታት ችለዋል።
- ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ሁሉ ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ፣
- ተማሪዎች በፈተና/ምዘና ፣ የሚፈፀም ኩረጃ ጸያፍ መሆኑን ተገንዝበዋል፣

**ስታንዳርድ 10**

ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው በጎ አመለካከት አላቸው።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ በሚሰጣቸው አገልግሎት ረክተዋል።
- ት/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ድጋፍ አድርገዋል፣
- ተማሪዎች መምህሮቻቸውን በአግባቡ መገምገም ችለዋል፣
- ተማሪዎች ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት ይሰጣሉ፣

- ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ አድርገዋል፣

**ለ. ማስተማር**

**ስታንዳርድ 11**

*መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደ፣ በአመቺ የትምህርት መርጃዎች የተደገፈ እና ከፍተኛ የትምህርት ውጤትን ለማስገኘት አልሞ የተዘጋጀ ነው።*

**አመልካቾች፡-**

- *የመምህራን የትምህርት እቅድ የሚያስተምሩትን ትምህርት አላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ስነ ዘዴ… ወዘተ በአግባቡ አካቷል፣*
- *መምህራን የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ አውለዋል፣*
- *መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ ፕላዝማ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም ሰጥተዋል፣*
- *መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ቤተ-ሙከራ በመጠቀም ሰጥተዋል፣*
- *መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎቻቸው የአካባቢ ቁሳቁስ ተጠቅመው የፈጠራ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታታሉ፣*
- *መምህራን ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸውና በውጤታቸው እንዲሻሻሉ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እገዛ አድርገዋል።*

**ስታንዳርድ 12**

*መምህራን የሚስተምሩትን የትምህርት ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ።*

**አመልካቾች፡-**

- *መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት በቂ እውቀትና ክህሎት አላቸው፣*
- *መምህራን ለተማሪዎች በሚመጥን ቋንቋ እና አቀራረብ ይዘቱን ቀለል አድርገው ያቀርባሉ፡*
- *መምህራን በትምህርቱ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦችን ለተማሪዎች በግልጽና አብራርተው ያቀርባሉ፣*

**ስታንዳርድ 13**

የት/ቤቱ አመራርና መምህራን ለሁሉም ተማሪዎች ተስማሚና ዘመናዊ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ጎልብቷል።

**አመልካቾች፡-**

- *መምህራን ተማሪዎች በትምህርታቸው ተመራማሪ፣ ፈጣሪ፣ ችግር ፈቺ እና ራሳቸውን የሚመሩ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፣*
- የትምህርት ቤቱ አመራር ዘመናዊና አሳታፊ የመማር-ማስተማር ስነ ዘዴ በት/ቤቱ እንዲተገበር ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፣

- *መምህራን ተማሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በጥንድ፣ በቡድን እና በግል ትምህርታቸውን እንዲማሩ አድርገዋል፣*
- *መምህራን ለሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣*
- *መምህራን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣*
- *መምህራን የመማር ማስተማሩን ችግር ለመፍታት የተግባር ምርምር አካሂደዋል።*

**ስታንዳርድ 14**

ትምህርት ቤቱ ለሴቶችና እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።

**አመልካቾች፡-**

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎች ትምህርት ቤቱ መዝግቦ ይዟል፤
- ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣
- ትምህርት ቤቱ የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣

**ስታንዳርድ 15**

*መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር /CPD/ ተግባራዊ አድርገዋል።*

**አመልካቾች፡-**

- *ነባር መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ቤቱን የመማር ማስተማር ችግር ለመፍታት የሚያስችል ችግሮችን በቅደም ተከተል ለይተው ሞጁል አዘጋጅተው ቢያንስ በዓመት ለ60 ሰዓት በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ላይ ተሳትፈዋል፣*
- *አዲስ ጀማሪ መምህራን አማካሪ መምህራን ተመድበውላቸው የሙያ ትውውቅ መርሃ ግብር /Induction Course/ አጠናቀዋል፣*

**ስታንዳርድ 16**

የትምህርት ቤቱ አመራር፣ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልማት ሠራዊት በመደራጀት በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው።

**አመልካቾች፡-**

- የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ተማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው የትምህርት ልማት ሰራዊት በመገንባት ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መልክ ተወጥተዋል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፣ እርስ በእርስም በውስጥ ሱፐርቪዥን አማካኝነት ተገነባብተዋል።
- የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጥሩ ስነ ምግባር የታነፁ፣ ለሙያቸው ተገቢ ክብር ያላቸው፣ትምህርት ቤቱን ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑ ናቸው፣

## 5.2.2. ሥርዓተ ትምህርት

**ስታንዳርድ 17**

ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው ፣ አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ መሆኑን መምህራን ይገመግማሉ፣ግብረ መልስ ይሰጣሉ፣ ያሻሽላሉ።

**አመልካቾች፡-**

- መምህራን በሥራ ላይ ያለውን ሥርዓተ ትምህርት ጠንቅቀው ያውቃሉ፣
- መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአገር አቀፍና በክልል የተዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርቶችን ያገናዘበ ነው፣
- መርሃ-ትምህርቶቹና ሌሎች የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች አሳታፊና ከተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃና ፍላጎት ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው ግብረ መልስ ተሰጥቶባቸዋል፣

## 5.2.3. ምዘና

**ስታንዳርድ 18**

ተማሪዎች በትክክል ተመዝነዋል፣ አስፈላጊው ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ የሚዘጋጅ ምዘና ስርአተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ በቢጋር /Table of Specifications/ የተዘጋጀ ነው፣
- ተማሪዎች በክልል/ከተማ አስተዳደር፣በዞን/ክፍለ ከተማ በወረዳና በጉድኝት ማዕከል በሚዘጋጁ ፈተናዎች ይመዘናሉ፣
- መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለመለካት በተቀመጠው ዝቅተኛ የመማር ብቃት /MLC/ መሠረት የንድፈ ሃሳብና የተግባር ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ፣
- መምህራን የተማሪዎችን ውጤት በመተንተን ድጋፍ ሰጥተዋል፣
- መምህራን ተማሪዎች ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ ግብረ-መልስ በመስጠት ድጋፍ ያደርጋሉ፣
- ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን ውጤት ለወላጆች በማሳወቅ ግብረ መልስ ይቀበላል።

## 5.2.4. ክትትልና ግምገማ

**ስታንዳርድ 19**

የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች ያቀዷቸው እቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላሉ።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ ማህበረሰቡ የተደራጁ የትምህርት ልማት ሰራዊት እቅዶች በአግባቡ መታቀዳቸውንና መከናወናቸውን ይከታተላል፣ለችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፣
- የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራምን አተገባበርን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣
- የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ኮሚቴ በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የተዘረጉ ስልጠናዎችን አፈፃፀማቸውንና መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች እየለየ ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣
- የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደትና የክበባት ዕቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣
- ት/ቤቱ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አካላትን ያበረታታል፣ ዕውቅና ይሰጣል፣

**ስታንዳርድ 20**

ትምህርት ቤቱ የሰው ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል።

**አመልካቾች፡-**

- ት/ቤቱ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፣
- መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ተመድበው ያስተምራሉ፣
- ርዕሰ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ ተመድበው ይሰራሉ፣
- በት/ቤቱ ያሉ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች እና ተጨማሪ ግብዓቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ውለዋል፣
- የት/ቤቱ በጀት ቅድሚያ ለተሰጣቸው የትምህርት ቤት መሻሻል እቅድ ላይ በተቀመጡና አግባብነት ያላቸው አካላት በወሰኑት መሠረት በተገቢ መንገድ ሥራ ላይ ውሏል።

### 5.2.5. የትምህርት ቤት፣ የወላጆችና የማህበረሰብ አጋርነት

**ስታንዳርድ 21**

ትምህርት ቤቱ ከተማሪ ወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው።

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ ወላጆች በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤ በትምህርት ቤትና በክፍል ደረጃ ወላጆች ትርጉም ያለው ተሳትፎ በተደራጀ መልኩ እንዲያደርጉ ያደርጋል።
- ትምህርት ቤቱ በየወቅቱ ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበልና ውጤት፣ ባህርይ፣ የፋይናንስ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃ ይሰጣል፣ ግብረ መልስም ይቀበላል፣
- ወላጆች ልጆቻቸው በቤት ውስጥ በትምህርታቸው እንዲበረታቱ ያግዛሉ፣
- ወላጆች በወላጅ፣ተማሪ፣ መምህር ህብረት(ወመህ/ወተመህ) እንቅስቃሴ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣
- ትምህርት ቤቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ በአንጻራዊነት የልህቀት ማዕከል በመሆን ያገለግላል፣
- ወላጆች በትምህርት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም መርካታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ፣

## 5.3. ውጤት (Output)

### 5.3.1. ትምህርት ቤቱና ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት

**ስታንዳርድ 22**

ትምህርት ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት/Internal efficiency/ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።

**አመልካቾች፡-**

- በትምህርት ቤቱ አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ተደርጓል፣
- ትምህርት ቤቱ የጥቅል ተሳትፎ ዕቅዱን አሳክቷል፣
- ትምህርት ቤቱ የንጥር ተሳትፎ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል፣
- የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ጾታዊ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል።፣

- የትምህርት ቤቱ መጠነ ማቋረጥ በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል፣
- የትምህርት ቤቱ መጠነ መድገም በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል።

**ስታንዳርድ 23**

የተማሪዎች የክፍል ፣ የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች ከሚጠበቀው ሃገራዊና ክልላዊ መመዘኛ ጋር ሲነፃፀር ተሻሽሏል።

**አመልካቾች፡-**

- ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣
- ትምህርት ቤቱ ለሁሉም ሴት ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣
- ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣
- የተማሪዎች የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች በትምህርት ቤቱ ዕቅድ መሰረት ተሳክቷል፣

## 5.3.2. የተማሪዎች ግለ-ስብዕና

**ስታንዳድ 24**

ተማሪዎች በስነ ስርዓት የታነጹ፣ መልካም እሴቶችና ባህልን የተላበሱ፣አካባቢን የመንከባከብ ሃላፊነት የሚሰማቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።

**አመልካቾች**

- ተማሪዎች በስነ ምግባር የታነጹ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያከብሩ፣እርስ በርስ የሚከባበሩ፣ የሚተጋገዙና ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚታገሉ ሆነዋል፣
- ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ንብረት ተንከባክበዋል፣
- ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን እሴቶች፣ደንቦችና መመሪያዎችን አውቀው ስራ ላይ በማዋል ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል።
- በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች መካከል የመቻቻልና ልዩነትን በውይይት የመፍታት ባህል ዳብሯል፣
- ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል።

## 5.3.3. የመምህራንና የትምህርት አመራር ግለ - ስብዕና

### ስታንዳርድ 25

በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ተፈጥሯል፣ ኪራይ ሰብሳቢነትን የመታገልና የተጠያቂነት ስሜት ዳብሯል ፡፡

**አመልካቾች፡-**

- የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩና ተግባቢ በመሆናቸው የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት አጎልብቷል፣
- በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣
- የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል፡፡

## 5.3.4. የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ

### ስታንዳርድ 26

ትምህርት ቤቱ ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል ፣

**አመልካቾች፡-**

- ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣
- ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በመጨመሩ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል፣

## 6. የት/ቤቶች ደረጃ ምደባ እንዴት ይካሄዳል?

የት/ቤት ደረጃ ምደባ ከተቀመጠለት ግብና ዓላማ አንፃር ይበልጥ ተአማኒነት ኖሮት የተፈለገውን ውጤት ማምጣት እንዲቻል ደረጃ ምደባው በሁለት መልኩ ይካሄዳል፡፡ አንደኛው በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄደው ደረጃ ምደባ በትምህርት ቤት ማሻሻያ የሚካሄደውን ግለ ግምገማና በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን የኢንስፔክሽን የት/ቤቶች ደረጃ ምደባ ስታንዳርድ መሠረት በማድረግ ይከናወናል ፡፡ ይህም የደረጃ ምደባ ከመምህራን ፣ ከተማሪዎች፣ ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና ከወላጆች ተወጣጥቶ በት/ቤቱ ርዕሰ መምህር አማካኝነት በሚቋቋም ኮሚቴ ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም ደረጃ ምደባው ት/ቤቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት በምን ደረጃ ላይ እንዳለ በመመዘን ጠንካራ አሰራሮችን እንዲጎለብቱና ደካማ አሰራሮች እነዲሻሻሉ ስልቶችን በመንደፍ ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡ ሁለተኛው ከትምህርት ቤቱ ውጭ ባሉ በሰለጠኑ፣ ብቃትና ልምድ ባላቸው ከወረዳ አስከ ፌዴራል ትም/ሚኒስቴር በሚገኙ የትምህርት ኢንስፔክተሮች ይካሄዳል፡፡

### 6.1. የት/ቤት ደረጃ ምደባ የአተገባበር ሥልት፡-

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የትምህርት ቤት ደረጃ ምደባ በትምህርት ቤቱና ከትምህርት ቤቱ ውጭ ባሉ አካላት ይካሄዳል፡፡ ከትምህርት ቤት ውጭ የሚካሄደው የትምህርት ቤት ደረጃ ምደባ አተገባበር ሂደት በአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ ውስጥ በዝርዝር ተካቷል፡፡ ስለሆነም በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄደው ደረጃ ምደባ ሂደት በትምህርት ቤት ደረጃ ምደባ ሰነድ የተቀመጡትን ስታንዳርዶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን አተገባበር ስልቶች በመከተል ይከናወናል፡-

- በቅድሚያ በርዕሰ መምህሩ/ሯ አማካኝነት ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ያሉት የት/ቤት ደረጃ ምደባ ኮሚቴ ማቋቋም፣
- ለትም/ቤቱ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እና ወላጆች ስለ ትም/ቤት ደረጃ ምደባ ምንነት ዓላማና ጠቀሜታ ላይ በቅድሚያ ግንዛቤ በመፍጠር የሁሉንም የጋራ ተሳትፎ አቀናጅቶ በጋራ መንቀሳቀስ፣
- የትም/ቤት ደረጃ ምደባ የሚካሄድበትን የጊዜ ሰሌዳ ማውጣት፡፡
- ለደረጃ ምደባው ግብአት የሚሆኑትን መረጃዎች በቅድሚያ መሰብሰብና ማደራጀት፣

- በተዘጋጀው የት/ቤት ደረጃ ምደባ ስታንዳርድ መሰረት የትም/ቤቱን ደረጃ ማውጣት፤ ለሚመለከተው አካላት ሪፖርት ማቅረብ።

**ማስታወሻ፡-**በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄደው የደረጃ ምደባ በዘመኑ የትምህርት ዓመት መጨረሻ ይሆናል።

## 6.2. የመለኪያዎች ክብደት አሰጣጥ፡-

ሀገራችን ለተማሪዎች መማር እና ውጤታማነት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች። በመሆኑም የትምህርት ጥራትና ውጤታማነትን በትምህርት ቤት ደረጃ ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ስልቶች አንዱ ትምህርት ቤቶችን በደረጃ በመለየት የውድድር መንፈስ በመፍጠር የአፈጻጸም ብቃታቸውን በማሳደግ ውጤታማነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ነው። ከዚህ አኳያ የትምህርት ቤት ደረጃ ምደባን ለማከናወን በመለኪያነት ለተቀመጡት ግብዓት ፣ ሂደት እና ውጤት ክብደት በመስጠት እንደሚከተለው ይከናወናል፡-

**መለኪያዎች** **ክብደት**

- ለግብዓት /Input/------------------- 25%
- ለሂደት /Process/ ----------------- 35%
- ለውጤት /Output/ ---------------- 40 % ድርሻ ተሰጥቷቸዋል::

በተመሳሳይ ለግብዓት፣ ሂደትና ውጤት በተሠጣቸው ክብደት መሠረት በስራቸው ለተቀመጡት ስታንዳርዶችና አመልካቾች ከይዘታቸው አኳያ ተከፋፍሎ በተቀጽላ-1 እና 2 ከዚህ በታች ተመልክቷል።

## 6.3. የደረጃ አሰጣጥ ሂደት

የትምህርት ቤት ደረጃ አሰጣጥ ሂደት በተዘጋጀው የትምህርት ቤት ደረጃ ምደባ ሰነድ ስታንዳርዶችና በውስጣቸው ያሉትን አመልካቾች መሰረት ያደረገ ሆኖ፡-

1. በተዘጋጀው ቼክሊስትና የአመልካች ገላጮችን/Descriptors/ መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ አመልካች/Indicator/ ደረጃ መስጠት፤
2. በእያንዳንዱ ስታንዳርድ ውስጥ የሚገኙ አመልካቾች አማካይ ውጤትን በመውሰድ ለስታንዳርዱ ደረጃ መስጠት፤
3. በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት ስር ያሉ ስታንዳርዶች አማካይ ውጤት እንደየቅደም ተከተላቸው የግብዓት፣ የሂደት እና ውጤት ደረጃ ይሆናል፤

4. የግብዓት፣ሂደት እና ውጤት ድምር የትምህርት ቤቱ ደረጃ ይሆናል።

በዚሁ መሠረት የሁሉም መለኪያዎች (ግብዓት ፣ ሂደትና ውጤት) ድምር ውጤት፦

- ከ50% በታች ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 1 ይመደባል።
- ከ50% - 69.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 2 ይመደባል።
- ከ70% - 89.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 3 ይመደባል።
- ከ90% - 100% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 4 ይመደባል።

በመጨረሻም የደረጃ አሰጣጥ ሂደት ዝርዝር አሰራሩ በዚህ ሰነድ መጨረሻ በተያያዘው ተቀጽላ 3 ይመልከቱ።

# ተቀጽላ-1 (Appendix -I)

## የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ /School Classification/ ስታንዳርዶች

1.ግብአት (Input) /25%/

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 1.1 የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች (School facility, physical, human and financial resources) | 1. ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል።/4%/ | ▪ ትም/ቤቱ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንፃዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ባካተተ መልኩ (በቂ ብርሃን፣ስፋት፣ወለል ወዘተ) የታነፁና የተሟሉ ናቸው፣<br>▪ ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍ ፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ የመምህሩ/ሯ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን፣ ብሬይል እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶችን አሟልቷል፣<br>▪ ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የስፖርት ሜዳ አሟልቷል።<br>▪ በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ፣ ገዥ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት ወዘተ እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣ | • የት/ቤቱን ህንፃና የመማሪያ ክፍሎቹን በመመልከት፣<br>• የትም/ቤቱን የተለያዩ ፋሲሊቲዎች/ ቁሳቁሶች/ በመቁጠር፣<br>• ተማሪዎችን፣ርእሰ መምህሩ/ሯንና የሚመለከታቸውን የአስተዳደር ሠራተኞች በመጠየቅ።<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| | 2. ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል።/4%/ | ▪ ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ቤት ጥቅል በጀት /Block grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤<br>▪ ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የት/ቤት ድጐማ በጀት /School grant/ ተቀብሎ በአግባቡ ሥራ ላይ አውሏል፤<br>▪ ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣ | • ስለ ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ ምንጭና አጠቃቀም የሚያሳዩ ሰነዶች፣ |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | ▪ ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል፣<br>▪ ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት አሰባስበዋል።<br>▪ ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ዶክመንቶች አሉት፣ | |
| | 3. ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል።/4%/ | • ሁሉም የትምህርት ቤቱ ርእሳነ መምህራንና መምህራን የሙያ ፈቃድና ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት አላቸው፣<br>• ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት፣<br>• ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ/Guidance and Counselling/ አገልግሎት የሚሰጥ/የምትሰጥ ባለሙያ አለው።<br>• ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት የሰለጠኑ መምህራን አሉት። | • የመምህራኖቹን ፕሮፋይል የሚያሳይ መዝገብ፣<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት፣ |
| 1.2 ምቹ የመማሪያ አካባቢ | 4. ትምህርት ቤቱ ለት/ ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታ ቸውን የሚያረጋግጥ የመማር - ማስተማር አካባቢ ፈጥሯል።/4%/ | • ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ አለው፣<br>• በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ህንፃዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው፣<br>• የትምህርት ቤቱ ግቢ በአጥር ተከብሯል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፣<br>• በትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር ተሟልቷል።<br>• ትምህርት ቤቱ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው። | • ምድረ ግቢውን በመመልከትና ካርታ በመመልከት<br>• መረጃዎችን በመመልከት<br>• ህንጻዎችን በመመልከት፣<br>• ጥገናን የሚመለከቱ ሪከርዶች<br>• ደህንነትን የተመለከቱ ሪፖርቶች<br>• የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በማወያየት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 5. ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል።/3%/ | • በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል ግብዐት፣አደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት ተፈጥሯል።<br>• በትምህርት ቤቱ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦችን ተልዕኮዎችን የተገነዘበና ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምንርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል።<br>• በትምህርት ቤቱ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል። | • ከተማሪዎች ጋር መወያየት፣<br>• ከመምህራንና ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት<br>• ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ጋር በመወያየት<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት |

## 1. 3 የትምህርት ቤቱ ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴቶችና ዕቅዶች

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| አመራር (Leadership) | 6. ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት።/3%/ | • የትምህርት ቤቱ አመራር ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አዘጋጅቷል፤ | • ከርእሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ሌሎች ሠራተኞች እንዲሁም ከተማሪዎችና ከወላጆች ጋር በመወያየት፡<br>• በወላጆች፣ መምህራንና ተማሪዎችን መጠይቅ አዘጋጅቶ በማስሞላት መረጃውን በማጠናቀር በሚገኝ ውጤት፣<br>• ትም/ቤቱን በሥራ ላይ በመመልከት፣<br>• የትም/ቤቱን መረጃ በመመልከት |
| | 7. ትምህርት ቤቱ አሳታፊ የት/ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፣/3%/ | • ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለይቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቷል፣ | • ርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት፣ ሰነዶችን በመመልከት፣የት/ቤት መሻሻል ኮሚቴን በማወያየት<br>• ትምህርት ቤቱ ራሱን የገመገመበት ሰነድ |

## II. ሂደት (Process) /35%/

### 2.1 መማር- ማስተማር /Learning and Teaching/

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 2.1.1. መማር (Learning) | 8. የተማሪዎች መማርና ተሳትፎ ጎልብቷል። /3%/ | • ተማሪዎች የተሰጧቸውን ሥራዎች በትጋት ይሰራሉ፣<br>• ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅና መልሶችን ለመመለስ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፣<br>• ተማሪዎች በ1 ለ 5 (ኔትወርክ) አደረጃጀት ተደራጅተው በትምህርታቸው ይረዳዳሉ፣<br>• ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ነው፣<br>• ተማሪዎች በህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል ተደራጅተው በመማር ማስተማር የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተሳትፎ እያደረጉ ነው። | • የተማሪዎች ደብተር በመመልከት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ በማካሄድ፣<br>• ተማሪዎች፣ መምህራንን እና ር/መምህራን ጋር በማወያየት<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| | 9. ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል።/3%/ | • ተማሪዎች የትምህርት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣<br>• ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር መፍጠር፣ መመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች መፍታት ችለዋል።<br>• ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ሁሉ ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ፣<br>• ተማሪዎች በፈተና/ምዘና የሚፈፀም ኩረጃ ጸያፍ መሆኑን ተገንዝበዋል፣ | • የተማሪዎች ስም መቀጣጠሪያ በመመልከት<br>• ያርፋጅ፣የቀሩ፣ያቋረጡና የደገሙ ተማሪዎች መመዝገቢያ ቅጽ እና የተማሪ ውጤት ማጠቃለያ/ሮስተር/ በመመልከት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ<br>• ከተማሪ፣መምህራን እና ር/መምህራን ጋር በመወያየት |
| | 10. ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው በጎ አመለካከት አላቸው።/2%/ | • ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ በሚሰጣቸው አገልግሎት ረክተዋል።<br>• ት/ቤቱ ለሚያከናውኗቸው ሥራዎች ድጋፍ አድርገዋል፣<br>• ተማሪዎች መምህሮቻቸውን በአግባቡ መመዘን ችለዋል፣<br>• ተማሪዎች ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት ይሰጣሉ፣<br>• ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ አድርገዋል፣ | • ሰነዶችን በመመልከት፣<br>• ከተማሪዎች፣መምህራን፣ር/መምህራን እና የአስተዳደር ሰራተኞች ጋር በመወያየት፣<br>• የተለያዩ የዲሲፒሊን ሰነዶችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 2.1.2 ማስተማር | 11. መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደ፣ በአመቺ የትምህርት መርጃዎች የተደገፈ እና ከፍተኛ የትምህርት ውጤትን ለማስገኘት አልሞ የተዘጋጀ ነው።/3%/ | • የመምህራን የትምህርት እቅድ የሚያስተምሩትን ትምህርት አላማ፣ ይዘት፣የማስተማር ስነ ዘዴ… ወዘተ በአግባቡ አካቷል፣<br>• መምህራን የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ አውለዋል፣<br>• መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ፕላዝማ፣ቴሌቪዥን፣ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ቤተ-ሙከራ በመጠቀም ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎቻቸው የአካባቢ ቁሳቁስ ተጠቅመው የፈጠራ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታታሉ፣<br>• መምህራን ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸውና በውጤታቸው እንዲሻሻሉ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እገዛ አድርገዋል። | • የትምህርት እቅድ፣<br>• የትምህርት ማእከሉን በመመልከት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ<br>• የኢ.ኮ.ቴ ማእከልን በመመልከት<br>• የቤተ-ሙከራ አጠቃቀም እቅዶችን በመመልከትና ተጠቃሚዎችን በማወያየት<br>• የተሰሩ ስራዎችን በመመልከት<br>• ተማሪዎችን፣መምህራንን እና ር/መምህራንን በማወያየት |
| | 12. መምህራን የሚስተምሩትን የትምህርት ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ። /3%/ | • መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት በቂ እውቀትና ክህሎት አላቸው፣<br>• መምህራን ለተማሪዎች በሚመጥን ቋንቋ እና አቀራረብ ይዘቱን ቀለል አድርገው ያቀርባሉ፡<br>• መምህራን በትምህርቱ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦችን ለተማሪዎች በግልጽና አብራርተው ያቀርባሉ | • የክፍል ምልከታ ፣<br>• የክፍል ውስጥምልከታ በማካሄድ ፣<br>• የተማሪዎችን ፓርላማ/ካውንስል፣መምህራ ንየትምህርት ክፍል ሃላፊዎችን እና ር/መምህራንን በማወያይት |
| | 13. የት/ቤቱ አመራርና መምህራን ለሁሉም ተማሪዎች ተስማሚና ዘመናዊ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ጎልብቷል።/3%/ | • መምህራን ተማሪዎች በትምህርታቸው ተመራማሪ፣ ፈጣሪ፣ ችግር ፈቺ እና ራሳቸውን የሚመሩ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፣<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር ዘመናዊና አሳታፊ የመማር-ማስተማር ስነ ዘዴ በት/ቤቱ እንዲተገበር ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፣<br>• መምህራን ተማሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በጥንድ፣ በቡድን እና በግል ትምህርታቸውን እንዲማሩ አድርገዋል፣<br>• መምህራን ለሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን የመማር ማስተማሩን ችግር ለመፍታት የተግባር ምርምር አካሂደዋል። | • የክፍል ውስጥምልከታ በማካሄድ ፣<br>• የተማሪዎችን ፓርላማ/ካውንስል፣መምህራ ንየትምህርት ክፍል ሃላፊዎችን እና ር/መምህራንን በማወያይት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 14. ትምህርት ቤቱ ለሴቶችና እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።/2%/ | • ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎች ትምህርት ቤቱ መዝግቦ ይዟል፤<br>• ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል እና ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ አድርጓል፣ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር በመወያየት፣<br>• መረጃዎችን በመመልከት |
| | 15. መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር /CPD/ ተግባራዊ አድርገዋል። /2%/ | • ነባር መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ቤቱን የመማር ማስተማር ችግር ለመፍታት የሚያስችል ችግሮችን በቅደም ተከተል ለይተው ሞጁል አዘጋጅተው ቢያንስ በዓመት ለ60 ሰዓት በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ላይ ተሳትፈዋል፣<br>• አዲስ ጀማሪ መምህራን አማካሪ መምህራን ተመድበውላቸው የሙያ ትውውቅ መርሃ ግብር /Induction/ አጠናቀዋል፣ | • የትም/ቤቱ የተሙማ ዕቅድ ግላዊ ግምገማ ሠነድ፣<br>• የመምህራን የግል ተሙማ ዕቅድ ግላዊ ግምገማና የሙያ ማሻሻያ ግል<br>• ማህደረ ተግባር /Portfolio/፣<br>• ከመምህራን ጋርመወያየት፣<br>• የክፍል ምልከታማድረግ። |
| | 16. የትምህርት ቤቱ አመራር ፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልማት ሠራዊት በመደራጀት በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው። /3%/ | • የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ተማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው የትምህርት ልማት ሰራዊት በመገንባት ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መልክ ተወጥተዋል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፣ እርስ በእርስም በውስጥ ሱፐርቪዥን አማካኝነት ተገነባብተዋል።<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጥሩ ስነ ምግባር የታነፁ፣ ለሙያቸው ተገቢ ክብር ያላቸው፣ትምህርት ቤቱን ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑ ናቸው፣ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር መወያየት።<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| 2..2 ሥርዓተ ትምህርት (Curriculum) | 17. ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው፣አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ መሆኑን መምህራን ይገመግማሉ፣ግብረ መልስ ይሰጣሉ፣ ያሻሽላሉ።/2%/ | • መምህራን በሥራ ላይ ያለውን ሥርዓተ ትምህርት ጠንቅቀው ያውቃሉ፣<br>• መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአገር አቀፍና በክልል የተዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርቶችን ያገናዘበ ነው፣<br>• መርሃ-ትምህርቶቹና ሌሎች የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች አሳታፊና ከተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃና ፍላጎት ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው ግብረ መልስ ተሰጥቶባቸዋል፣ | • የክፍል ምልከታ፣<br>• የሥርዓተ ትምህርት እቅዶችን ማቴሪያሎችን መፈተሽ፣<br>• የተጓዳኝ ትምህርት ሥራዎችን በመመልከት፣<br>• ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር መወያየት። |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 2.3 ምዘና (Assessment) | 18. ተማሪዎች በትክክል ተመዝነዋል፣አስፈላጊው ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል። /3%/ | • በትምህርት ቤቱ የሚዘጋጅ ምዘና ስርአተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ በቢጋር /Table of Specifications/ የተዘጋጀ ነው፣<br>• ተማሪዎች በክልል/ከተማ አስተዳደር፣በዞን/ክፍለ ከተማ በወረዳና በጉድኝት ማዕከል በሚዘጋጁ ፈተናዎች ይመዘናሉ፣<br>• መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለመለካት በተቀመጠው ዝቅተኛ የመማር ብቃት /MLC/ መሠረት የንድፈ ሃሳብና የተግባር ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ፣<br>• መምህራን የተማሪዎችን ውጤት በመተንተን ድጋፍ ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን ተማሪዎች ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ ግብረ-መልስ በመስጠት ድጋፍ ያደርጋሉ፣<br>• ትምህርት ቤቱ የተማሪዎችን ውጤት ለወላጆች በማሳወቅ ግብረ መልስ ይቀበላል። | • የትምህርት ክፍል ሃላፊዎችንና ይስርአተ ትምህርት ኮሚቴ አባላትን በማወያየት<br>• መምህራንን፣ ሱፐርቫይዘርና ር/መምህርራንን በማወያየት<br>• የተከታታይ ምዘና ሪከርዶችን በመመልከት<br>• ወላጆችን በማወያየት<br>• የተለያዩ ሰነዶችን በመመልከት |
| 2.4 ክትትልና ግምገማ-አመራር (Leadership) | 19. የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች ያቀዱቸው እቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላሉ። /2%/ | • በትምህርት ቤቱ ማህበረሰቡ የተደራጁ የትምህርት ልማት ሰራዊት እቅዶች በአግባቡ መታቀዳቸውንና መከናወናቸውን ይከታተላል፣ለችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፣<br>• በትምህርት ቤቱ የተደራጀው የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴ የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራምን አተገባበርን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣<br>• በትምህርት ቤቱ የተደራጀው የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ኮሚቴ በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የተዘረጉ ስልጠናዎችን አፈፃፀማቸውንና መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች እየለየ ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደትና የክበባት ዕቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣<br>• ት/ቤቱ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አካላትን ያበረታታል፣ ዕውቅና ይሰጣል፣ | • ትም/ቤቱ ራሱን የገመገመበት ሰነድ፣<br>• በወላጆች፣ በመምህራንና በተማሪዎች የተሞላ መጠይቅ ውጤት፣<br>• የአንድ እና የሶስት ዓመት የት/ቤት እቅድ ሰነድ፣<br>• የትም/ቤት መሻሻል በኮሚቴ ቃለ ጉባዔና ተዛማጅ መረጃዎች/ሰነዶች<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯና ከሌሎች አመራሮች ጋር ውይይት ማካሄድ፣<br>• ከጉድኝት ማእከሉ ሱፐርቫይዘር ጋር ውይይት ማካሄድ። |
| ክትትልና ግምገማ - አስተዳደር(Management | 20. ትምህርት ቤቱ የሰው ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል። /2%/ | ▪ ት/ቤቱ የመረጃ አሰባሰብ፣አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፣<br>▪ መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ተመድበው ያስተምራሉ፣<br>▪ ርዕሰ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ ተመድበው ይሰራሉ፣<br>▪ በት/ቤቱ ያሉ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች እና ተጨማሪ ግብዓቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ውለዋል፣<br>▪ የት/ቤቱ በጀት ቅድሚያ ለተሰጣቸው የትምህርት ቤት መሻሻል | • የትምህርት ቤቱን ህንፃ የውስጥ ግብዓቶችን በመመልከት፣<br>• ከርእሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ሌሎች ሠራተኞች ጋር በመወያየት፣ |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | እቅድ ላይ በተቀመጡና አግባብነት ያላቸው አካላት በወሰኑት መሠረት በተገቢ መንገድ ሥራ ላይ ውሏል። | • የገንዘብና ሌሎች መረጃ ቋቶችን በመፈተሽ |
| 2.5 የትምህርት ቤት፣የወላጆ ችና የማህበረሰብ አጋርነት /Engagement with parents and the community/ | 21. ትምህርት ቤቱ ከተማሪ ወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው።/2%/ | ▪ ትምህርት ቤቱ ወላጆች በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤ በትምህርት ቤትና በክፍል ደረጃ ወላጆች ትርጉም ያለው ተሳትፎ በተደራጀ መልኩ እንዲያደርጉ ያደርጋል።<br>▪ ትምህርት ቤቱ በየወቅቱ ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበልና ውጤት፣ ባህርይ፣ የፋይናንስ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃ ይሰጣል፣ ግብረ መልስም ይቀበላል፣<br>▪ ወላጆች ልጆቻቸው በቤት ውስጥ በትምህርታቸው እንዲበረታቱ ያግዛሉ፣<br>• ወላጆች በወላጅ፣ተማሪ፣ መምህር/ት ህብረት(ወመህ/ወተመህ) እንቅስቃሴ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣<br>• ትምህርት ቤቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ በአንጻራዊነት የልህቀት ማዕከል በመሆን ያገለግላል፣<br>• ወላጆች በትምህርት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም መርካታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ፣ | • ከወላጆች ጋር መወያየት፣<br>• ለወላጆች የቀረበ ሪፖርት፣<br>• ከወላጆች ጋር ውይይት የተደረገባቸው ቃለ ጉባዔ ሠነዶች፣<br>• ለቀረበላቸው መጠይቅ ወላጆች የሰጡት ምላሽ፣<br>• ከርእሰ መምህሩ/ሯና አግባብ ካለው የሥራ ባልደረባ ጋር ውይይት ማድረግ፣፣ |

## 3. ውጤት (Output) /40%/

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 3.1 ትምህርት ቤቱና ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት (Students' Attainment) | 22. ትምህርት ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት/Internal efficiency/ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።/10%/ | • በትምህርት ቤቱ አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ተደርጓል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የዋቅል ተሳትፎ ዕቅዱን አሳክቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የንጥር ተሳትፎ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል፣<br>• የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ጾታዊ ምጣኔ ዕቅዱን አሳክቷል።፣<br>• የትምህርት ቤቱ መጠነ ማቋረጥ በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል፣<br>• የትምህርት ቤቱ መጠነ መድገም በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል። | • የተማሪዎች የመዝገብ ሠነዶች፣<br>• የተማሪዎች መከታተየ ሠነዶች፣<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር ውይይት ማካሄድ፣ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበሰብ ውይይት ማካሄድ። |
| | 23. የተማሪዎች የክፍል ፣ የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች ከሚጠበቀው ሃገራዊና ክልላዊ መመዘኛ ጋር ሲነፃፀር ተሻሽሏል። 8%/ | • ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣<br>• ትምህርት ቤቱ ለሁሉም ሴት ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣ | • የተማሪዎች የሙከራና የማጠቃለያ ፈተናዎች መረጃ፣<br>• ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | • ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ሆኗል፣<br>• የተማሪዎች የክልልና የብሄራዊ ፈተና ውጤቶች በትምህርት ቤቱ ዕቅድ መሰረት ተሳክቷል፣ | |
| 3.1.2 የተማሪዎች ግለ-ስብዕና እድገት (Students' personal development) | 24. ተማሪዎች በሥነ-ስርዓት የታነጹ፣ መልካም እሴቶችና ባህልን የተላበሱ፣ አካባቢን የመንከባከብ ኃላፊነት የሚሰማቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።/10%/ | • ተማሪዎች በስነ ምግባር የታነጹ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያከብሩ፣እርስ በርስ የሚከባበሩና የሚተጋገዙና ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚታገሉ ሆነዋል፣<br>• ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ንብረት ተንከባክበዋል፣<br>• ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን እሴቶች፣ደንቦችና መመሪያዎችን አውቀው ስራ ላይ በማዋል ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል።<br>• በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች መካከል የመቻቻልና ልዩነትን በውይይት የመፍታት ባህል ዳብሯል፣<br>• ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል። | • ከተማሪዎች ጋር ውይይት ማድረግ፣<br>• የክፍል ምልከታ፣<br>• በትምህርት ቤት አካባቢ እየተዘዋወሩ ተማሪዎች የሚያደርጉትን ድርጊት መመልከት። |
| | 25. በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ተፈጥሯል፣ ኪራይ ሰብሳቢ ነትን የመታገልና የተጠያቂ ነት ስሜት ዳብሯል።/6%/ | • የትምህርት ቤቱ መምህራን ፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተማሪዎችን የሚያከብሩና ተግባቢ በመሆናቸው የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ዳብሯል፣<br>• በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣<br>• የትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል። | • የክፍል ምልከታ፣<br>• ከመምህራንና ተማሪዎች ጋር ውይይት ማካሄድ። |
| 3.4 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ | 26. ትምህርት ቤቱ ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል፣ /6%/ | • ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና አጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣<br>• ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በመጨመሩ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል፣ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራን እና ከሌሎችም የት/ቤቱ ሰራተኞች እንዲሁም ከአካባቢው ማህበረሰብ አባላት ጋር ውይይት ማድረግ<br>• የተከናወኑ ተግባራት መዝገብ ላይ<br>• የገንዘብ ወጪ መዝገቦች ላይ |

# ተቀጽላ-2 (Appendix-II)

## ገላጮች /Descriptors/

**ቁልፍ/key/፦** በውሳኔ አሰጣጥ /ደረጃ ምደባ ሂደት ላይ ውሳኔ ሰጪው አካል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተገንዝቦ ውሳኔ እንዲሰጥ ይጠበቃል። እንደ አጠቃላይ በዚህ ሰነድ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉና በአተረጓጎም ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ታስቦ በመስፈርትነት የተቀመጡ ቃላቶች ከዚህ በታች ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል።

- ከፍተኛ እጥረት/በጣም ዝቅተኛ/አነስተኛ /ውሱን ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር ከ50 በመቶ በታች ያገኘ፣
- አብዛኛው/አብዛኞቹ/ከፍተኛ ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር 50-69.99 በመቶ ያገኘ፣
- ሙሉ በሙሉ/ሁሉንም ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ 70-89.99 በመቶ ያገኘ፣
- በጣም ከፍተኛ የሚለው ከ90 ከመቶ እና በላይ ያገኘ፣በሚል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል።

I.ግብዓት /25%/

| 1.1- **የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች** | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ስታንዳርድ 1 ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል።/4%/** | | | | |
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትም/ቤቱ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንፃዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ባካተተ መልኩ (በቂ ብርሃን፣ስፋት፣ወለል ወዘተ) የታነፁና የተሟሉ ናቸው፣ /1%/ | በአብዛኛው ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የታነፁ የመማሪያና የመገልገያ ህንፃዎች የሉትም። | ትምህርት ቤቱ መማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንጻዎችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማሩ አስፈላጊ የሆኑ ህንፃዎች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ የተሟሉ የመማሪያ ክፍሎችና ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ ከተቀመጠው ስታንዳርድ ባለይ ህንፃዎች አሉት። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ የመምህር መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን፣ ብሬይል አሟልቷል፣ /1%/ | በትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መጽሐፍ፣ የመምህር መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሃፍት፣ ብሬይል ከፍተኛ እጥረት ይታያል። | በትምህርት ቤቱ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መጽሐፍና የመምህር መምሪያ እንዲሁም አጋዥ/ ማጣቀሻ መፃህፍት፣ ብሬይል በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው ተሟልተዋል። | በትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መጽሐፍ እንዲሁም አጋዥ/ ማጣቀሻ መፃህፍት የመምህር መምሪያ፣ ብሬይል በስታንዳርዱ መሰረት ተሟልተዋል። | ትምህርት ቤቱ ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ የተማሪ መፃህፍ፣ የመምህር መምሪያ ፣አጋዥ/ ማጣቀሻ መፃህፍት፣ ብሬይል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ነው |
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።/1%/ | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አላሟላም፡ | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በስታንዳርዱ መሠረት አሟልቷል። | ትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሃፍት፣ቤተ-ሙከራ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከልና የስፖርት ሜዳ እንዲሁም ሌሎች ፋሲሊቲዎችን ከስታንዳርዱ በላይ አሟልቷል። |
| በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ገዥ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች ህገ መንግስት እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣ /1%/ | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ዘርፉን አጠቃላይ አቅጣጫ ለመገንዘብ የሚያስችለው አገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው የሉትም ። | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ዘርፉን አጠቃላይ አቅጣጫ ለመገንዘብ የሚያስችለው አገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው አሉት፣ ሥራ ላይም አውሏቸዋል። | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ዘርፉን አጠቃላይ አቅጣጫ ለመገንዘብ የሚያስችለው አገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያ ዎችና መተዳደሪያ ደንብ ተሟልቶ ስራ ላይ ውሏል ። | በትምህርት ቤቱ ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ በዘመናዊ የመረጃ ማደራጃ ዘዴ በመጠቀም ባለድርሻ አካላት አውቀው እንዲጠቀሙበት አድርጓል። |
| **ስታንዳርድ 2 - ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል።** /4%/ | | | | |
| **አመልካች** | **ደረጃ** 1<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ** 2<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ** 3<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ** 4<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ቤት ጥቅል በጀት (Block Grant) በተማሪዎች ቁጥር መሠረት ተቀብሎ በአግባቡ ስራ ላይ አውሏል፤ /0.5%/ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት አልተቀበለም፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት የደረሰው ቢሆንም ለታለመለት አላማ አላዋለውም፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን ጥቅል በጀት ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ ተጨማሪ በጀት ከተለያዩ ምንጮች በማፈላለግ ሌሎች ተግባራትን አከናውኗል፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ቤት ድጐማ (School Grant) ተቀብሎ በአግባቡ ስራ ላይ አውሏል /0.5%/ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን የትምህርት ቤት ድጐማ አልተቀበለም፤ | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ቤት ድጐማ የደረሰው ቢሆንም ለታለመለት አላማ አላዋለውም፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን የትምህርት ቤት ድጐማ ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ | ትምህርት ቤቱ የሚገባውን የትምህርት ቤት ድጐማ ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ ተጨማሪ በጀት ከተለያዩ ምንጮች በማፈላለግ ሌሎች ተግባራትን አከናውኗል፤ |
| ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣/1%/ | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ የፈጠረው የግንዛቤ ማሳደግ ስራ ባለመኖሩ የተገኘ ድጋፍ የለም። | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ የፈጠረው ግንዛቤ ውስን በመሆኑ የተገኘ ድጋፍ አነስተኛ ነው፡ | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ በፈጠረው ግንዛቤ ከፍተኛ በመሆኑ በዕቅዱ መሰረት ሀብት አሰባስቧል | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ በፈጠረው ግንዛቤ ከፍተኛ በመሆኑ ከዕቅዱ በላይ ሀብት አሰባስቧል። |
| ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል፣/0.5%/ | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ያሰባሰበው ሀብት አነስተኛ ነው፣ | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ለማሰባሰብ ያቀደው ዕቅድ በአብዛኛው አሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ለማሰባሰብ ያቀደው ዕቅድ ሙሉ በሙሉ አሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ለማሰባሰብ ካቀደው በላይ አሳክቷል። |
| ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት አሰባስቧል።/1%/ | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት ለማሰባሰብ ያደረገው እንቅስቃሴ አነስተኛ ነው። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት ለማሰባሰብ ያቀደውን ዕቅድ በአብዛኛው አሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት ለማሰባሰብ ያቀደውን ዕቅድ አሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች /ከቀድሞ ተማሪዎች ፣ አካባቢ ተወላጆች…ወዘተ/ ሃብት ለማሰባሰብ ካቀደው በላይ አሳክቷል። |
| ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ዶክመንት አለው።/0.5%/ | ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ቤት ድጐማ፣ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት መጠንና አጠቃቀም የሚያመላክት መረጃ የለውም። | ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ቤት ድጐማ፣ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት ምንጭና መጠን የሚያመላክት መረጃ ያለው ቢሆንም የገቢና ወጪ አመልካች ሰነድ የለውም፡ | ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ቤት ድጐማ፣ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት ምንጭና መጠን የሚያመላክት የተደራጀ መረጃ ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ ገቢና ወጪን የሚያመላክት ሰነድ ስለመኖሩ በማስረጃ ተረጋግጧል። | ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ቤት ድጐማ፣ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት ምንጭና መጠን የሚያመላክት መረጃ ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ ገቢና ወጪን የሚያመላክት በአግባቡ የተደራጀ ዘመናዊ የፋይናንስ የአሰራር ስርአት አለው፡ |

| ስታንዳርድ 3 - ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን እና ድጋፍ ሰጪ በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል።/4%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ተግባር ጠቋሚ** | **ደረጃ 1<br>ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2<br>በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3<br>ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ ና የሙያ ፈቃድ ያላቸው ርእሳነ መምህራንና መምህራን አሉት፣ /1.5%/ | በትምህርት ቤቱ ከ79% በታች ርዕሰ መምህራን እና መምህራን ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ደረጃና የሙያ ፈቃድ አላቸው፤ | በትምህርት ቤቱ ከ80-99% ርዕሰ መምህራን እና መምህራን ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ደረጃ እና የማስተማር ፈቃድ አላቸው፤። | በትምህርት ቤቱ 100% ርዕሰ መምህራን እና መምህራን ተገቢው የትምህርት ደረጃ እንዲሁም የሙያ ፈቃድ አላቸው፤ | በትምህርት ቤቱ ሁሉም ርዕሰ መምህራን እና መምህራን ተገቢው የትምህርት ደረጃና የሙያ ፈቃድና ወቅታዊ እድሳት አላቸው። |
| ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው በቂ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት፣ /1%/ | በትምህርት ቤቱ ከ50% በታች የሚሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው። | በትምህርት ቤቱ ከ50-60% የሚሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው። | በትምህርት ቤቱ ከ61-99% የሚሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው። | በትምህርት ቤቱ 100% ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንደርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው። |
| ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ /Guidance and Counselling / አገልግሎት የሚሰጥ የሰለጠነ/ች ባለሙያ አለው።/0.5%/ | ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ /Guidance and Counselling / አገልግሎት የሚሰጥ/የምትሰጥ ባለሙያ የለውም። | ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ /Guidance and Counselling / አገልግሎት የሚሰጥ/የምትሰጥ ባለሙያ አለው፤ ነገር ግን በሙያው የሰለጠነ አንደለም ። | ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ /Guidance and Counselling / አገልግሎት የሚሰጥ/የምትሰጥ በሙያው የሰለጠነ ባለሙያ አለው። | ትምህርት ቤቱ የምክርና ድጋፍ /Guidance and Counselling / አገልግሎት የሚሰጥ የሰለጠነ/ች ባለሙያ አለው። በተጨማሪም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሙያዊ አገልግሎት ይሰጣል። |
| ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን አሉት።/1%/ | ት/ቤቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን የሉትም። | ት/ቤቱ የልዩ ፍላጎት መምህራን ያሉት ቢሆንም በሙያው የሰለጠኑ አይደሉም። | ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን አሉት። | ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን አሉት። በተጨማሪም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሙያዊ አገልግሎት ይሰጣል። |

| ስታንዳርድ 4 - ትምህርት ቤቱ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ የመማር - ማስተማር አካባቢ ፈጥሯል።/4%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አመልካች** | **ደረጃ 1<br>ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2<br>በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3<br>ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣ /0.5%/ | ትምህርት ቤቱ ከተቀመጠው ስታንድርድ አንጻር 50 ከመቶና በታች የቦታ ስፋት አለው፣ | ትምህርት ቤቱ ከተቀመጠው ስታንድርድ አንጻር 51-70 በመቶ የቦታ ስፋት አለው፣ | ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣ | ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ በላይ ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አለው፣ ጥቅም ላይም አውሏል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ትምህርት ቤቱ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አለው፣/0.5%/ | ትምህርት ቤቱ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የለውም፣ | ትምህርት ቤቱ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ለማግኘት በእንቅስቃሴ ላይ ነው፣ | ትምህርት ቤቱ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አለው፣ | ትምህርት ቤቱ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መሰረት ድንበሩን አስከብሯል፣ |
| በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ህንፃዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው፣ /0.5%/ | በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የመማሪያና ልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚሰጡ ህንፃዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ አይደሉም፡፡ | በትምህርት ቤቱ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የመማሪያና ልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚሰጡ ህንፃዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ናቸው፡፡ | በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ሁሉም የመማሪያና ልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚሰጡ ህንፃዎች በስታንዳርዱ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ናቸው፡፡ | በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ሁሉም የመማሪያና ልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚሰጡ ህንፃዎች ከሚጠበቀው ስታንዳርድ በላይ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለመማር ማስተማር ምቹ ናቸው፡፡ |
| የትምህርት ቤቱ ግቢ በአጥር ተከብሯል፣ /0.5%/ | የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በአጥር ባለመከበሩ ግቢውን በአግባቡ ማስከበር አልተቻለም፡፡ | የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ የታጠረ ቢሆንም ግቢውን በአግባቡ ማስከበር በሚያስችል ሁኔታ የተሰራ አይደለም፡፡ | የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በስታንዳርዱ መሰረት ታጥሯል፣ | የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ከተቀመጠው ስታንዳርድ በላይ ተጠናክሮ ተከብሯል፣ |
| ትምህርት ቤቱ አካባቢ የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፣ /1%/ | የትምህርት ቤቱ አካባቢ ለመማር ማስተማሩ ስራ የማያመችና ለተማሪዎች ደህንነት የሚያሰጋ ነው፡፡ | የትምህርት ቤቱን አካባቢ ለመማር ማስተማር ምቹ ለማድረግ በአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመተጋገዝ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም የተገኘው ውጤት አመርቂ አይደለም፡፡ | የትምህርት ቤቱን አካባቢ ለመማር ማስተማር ምቹ ለማድረግ ትምህርት ቤቱ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በቅንጅት በመስራቱ ከአዋኪ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፡፡ | ትምህርት ቤቱ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመተባበር የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ በማድረጉ በሌሎች ዘንድ በአርአያነት የሚታዩ ተግባራትን አከናውኗል፤ ይህም በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ |
| በትምህርት ቤቱ በቂ፣ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር ተሟልቷል፡፡ /0.5%/ | ትምህርት ቤቱ በቂና በፆታ የተለዩየመምህራንና ሰራተኞች በየጊዜው የሚፀዱ መፀዳጃ ቤቶች፣ የመታጠቢያ ውሃና ሳሙና አቅርቦት ያሟላ አይደለም፡፡ | ትምህርት ቤቱ በቂና ደረጃቸውን የጠበቁ መፀዳጃ ቤቶች ቢኖሩትም በፆታ የተለዩ፣ በየጊዜው የሚፀዱ እና የመታጠቢያ ውሃና ሳሙና አቅርቦት የላቸውም፡፡ | ትምህርት ቤቱ በቂ፣ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር አሟልቷል፡፡ | ትምህርት ቤቱ በቂ፣ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች እንዲሁም አስተማማኝ የውሃ ፣የሳሙና ለሴት ተማሪዎች ንጽህና መጠበቂያ/ሞዴስ/ና መታጠቢያ ቤት … ወዘተ አሟልቷል፡፡ |
| ትምህርት ቤቱ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው፡፡/0.5%/ | ትምህርት ቤቱ የውሃ አቅርቦት የለውም፡፡ | ትምህርት ቤቱ የውሃ አቅርቦት ቢኖረውም ለመጠጥ አገልግሎት የሚውል አይደለም ፡፡ | ትምህርት ቤቱ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው፡፡ | ትምህርት ቤቱ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ ለመታጠብ የሚያገለግል አስተማማኝ የቧንቧ ውሃ አቅርቦት አለው፡፡ |

| ስታንዳርድ 5 - ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል።/3%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል ግብዐት፣ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት ተዘርግቷል። /1%/ | በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል የግብዐት ፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት አልተፈጠረም። | በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል ግብዐት እና አደረጃጀት የተፈጠረ ቢሆንም የአሰራር ስርዐት አልተዘረጋም። | በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል የግብዐት፣የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት ዘርግቷል። | በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የተፈጠረው የግብዐት፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዐት ዝርጋታው ለሌሎች ትምህርት ቤቶች በአርዓያነት የሚጠቀስ ነው። |
| በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) በማቀናጀት ት/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎችና ግቦችን የተገነዘበና ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምህርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል።/1%/ | በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) በማቀናጀት ት/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎችና ግቦች ተገንዝቦ ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምህርት ልማት ሰራዊት አልተፈጠረም። | በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) በማቀናጀት ት/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎች ግቦችና ተልዕኮዎችን ተገንዝቦ ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምህርት ልማት ሰራዊት ለመፍጠር በጅምር ላይ ነው ። | በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) በማቀናጀት ት/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎችና ግቦች ተገንዝቦ ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምህርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል ። | በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) በማቀናጀት ት/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎችና ግቦች ተገንዝቦ ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምህርት ልማት ሰራዊት በመፍጠር ረገድ ያለው ተሞክሮ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርዐያ ሆኗል ። |
| በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) አቀናጅቶ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል። /1%/ | በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) አቀናጅቶ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት አልተፈጠረም። | በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) አቀናጅቶ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ለመፍጠር ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል። | በትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) አቀናጅቶ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል ። | ትምህርት ቤቱ ሶስቱን የልማት አቅሞች (የድርጅት፣የመንግስትና የህዝብ) አቀናጅቶ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት በመፍጠር ረገድ ያለው ተሞክሮ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው ። |

| ስታንዳርድ 6 - ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት። /3%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| የትምህርት ቤቱ አመራር ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አዘጋጅቷል፤ /3%/ | ትምህርት ቤቱ የተዘጋጁ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች የሉትም፡ | ትምህርት ቤቱ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች ያሉት ቢሆንም ዝግጅቱ የትምህርት ቤቱን ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ አይደለም። | ትምህርት ቤቱ ተገቢ የሆኑ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች የትምህርት ቤቱን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ አዘጋጅቷል። | ትምህርት ቤቱ ተገቢ የሆኑ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶችን የትምህርት ቤቱን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ያዘጋጀ ከመሆኑም በተጨማሪ ሁሉም የትምህርት ቤቱ ባለድርሻ አካላት ትምህርት ቤቱ የሚጓዝበትን የወደፊት አቅጣጫ ተገንዝበዋል። |

| ስታንዳርድ 7 - ትምህርት ቤቱ አሳታፊ የት/ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፣ /3%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለይቷል፣ /1%/ | ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች አለየም፣ | ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፍ ለይቷል | ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለይቷል፣ | ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የለየበት ስልት ለሌሎች ትምህርት ቤቶች በአርያነት የሚጠቀስ ነው። |
| ትምህርት ቤቱ የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቷል፣ /2%/ | ትምህርት ቤቱ አመታዊ ዕቅድ ቢኖረውም የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የለውም | ትምህርት ቤቱ ዓመታዊና የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅዶች ቢኖሩትም ባለድርሻ አካላትን አላሳተፈም፣ | ትምህርት ቤቱ ዓመታዊና የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅዶች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ አዘጋጅቷል፣ | ትምህርት ቤቱ ዓመታዊና የ3 ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅዶች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ያዘጋጀበት ሂደት ለሌሎች ትምህርት ቤቶች በአርአያነት ይወሰዳል፣ |

## II. ሂደት /35%/

| ስታንዳርድ 8፡- የተማሪዎች መማርና ተሳትፎ ጎልብቷል።/3%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ተማሪዎች የተሰጧቸውን የክፍልና የቤት ሥራዎች በትጋት ይሰራሉ፣ /0.5%/ | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ሥራዎች አይሰሩም፣ | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ሥራዎች ይሰራሉ፣ | ሁሉም ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ሥራዎች በአግባቡ ይሰራሉ፣ | በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ሥራዎችን የመስራት ልምድ ዳብሯል፤ ለሌሎች ትምህርት ቤቶችም ተምሳሌት ሆኗል፣ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅና መልሶችን ለመመለስ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፣ /1%/ | በክፍል ውስጥ አብኛዎቹ ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅና በመመለስ አይሳተፉም፣ | በክፍል ውስጥ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅና በመመለስ ይሳተፋሉ፣ | በክፍል ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅና በመመለስ ይሳተፋሉ፣ | ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ጋር በሚደረጉ የጥያቄና መልስ ውድድሮች አመርቂ ውጤት አስመዝግበዋል፣ |
| ተማሪዎች በአንድ ለአምስት (ኔትወርክ) አደረጃጀት ተደራጅተው በትምህርታቸው ይረዳዳሉ፣ /0.5%/ | ተማሪዎች በአንድ ለአምስት ተደራጅተው ወደ ስራ አልገቡም፣ | በትምህርት ቤቱ አብዛኞቹ ተማሪዎች በአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች እርስ በርስ መረዳዳት ጀምረዋል፣ | በትምህርት ቤቱ ሁሉም የተማሪዎች የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች እርስ በርስ ይረዳዳሉ። | በክፍል ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ተደራጅተው እርስ በርስ የሚረዳዱበት ስርአት ተፈጥሯል። |
| ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ነው፣/0.5% | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ ክበባት አይሳተፉም፣ | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ ክበባት ይሳተፋሉ፣ | ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ ክበባት ይሳተፋሉ፣ | ትምህርት ቤቱ ሁሉንም ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በንቃት በማሳተፉ በእንቅስቃሴአቸው ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆነዋል፣ |
| ተማሪዎች በህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል ተደራጅተው በመማር-ማስተማር የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተሳትፎ እያደረጉ ነው /0.5%/ | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኘው የህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል አይሳተፉም፣ | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኘው የህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል በመማር-ማስተማር ላይ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣ | ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኘው የህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል እንቅሰቃሴ ውስጥ በመማር-ማስተማር ላይ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣ | ትምህርት ቤቱ ሁሉንም ተማሪዎች በህፃናት ፓርላማና በተማሪ ካውንስል በማደራጀቱና በትምህርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ በመማር-ማስተማር ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማስቻሉ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆኗል |

| ስታንዳርድ 9፡- ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል።/3%/ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አመልካች** | **ደረጃ 1<br>ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2<br>በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3<br>ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ተማሪዎች የትምህርት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣ /1%/ | በአብዛዎቹ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የትምህርት ክፍለ ጊዜያቸውን ያባክናሉ፣ | የተወሰኑት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የትምህርት ክፍለ ጊዜያቸውን ያባክናሉ፣ | ሁሉም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የትምህርት ክፍለ ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ይጠቀማሉ፣ | ሁሉም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የትምህርት ክፍለ ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ይጠቀማሉ፤የትምህርት ክፍለ ጊዜያቸውን አለማባከንን የትምህርት ቤቱ እሴት አድርገዋል |
| ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገርን መፍጠር፡ መመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች መፍታትችለዋል።/0.5%/ | ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር የመፍጠር፡ የመመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች የመፍታት ልምድ አላዳበሩም። | ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር የመፍጠር፡ የመመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች የመፍታት ልምድ ጀምረዋል። | ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር የመፍጠር፡ የመመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች የመፍታት ልምድ አዳብረዋል። | የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አዲስ ነገር የመፍጠር፡ የመመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች የመፍታት ልምድ በላቀ ደረጃ ዳብሯል። |
| ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ሁሉ ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ፣ /0.5%/ | አብዛኛዎቹ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ተመጣጣኝ ክብደት አይሰጡም፣ | አብዛኛዎቹ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ፣ | ሁሉም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ | ሁሉም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ። በትምህርት ቤቱ ባህል ሆኗል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተማሪዎች በፈተና/ምዘና፣ የሚፈፀም ኩረጃ ጸያፍ መሆኑን ተገንዝበዋል፣ /1%/ | አብኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ በሚሰጡ የቤትና የክፍል ስራዎች፣ የፕሮጀክት ስራዎች እና የተለያዩ ፈተናዎች ራሳቸውን ችለው የመስራት ልምድ አልፈጠሩም፣ | አብዛኞዎቹ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ የሚሰጡ የቤትና የክፍል ስራዎች፣ የፕሮጀክት ስራዎችን እና የተለያዩ ፈተናዎችን ሳይኮራረጁ ራሳቸውን ችለው ይሰራሉ፣ | ሁሉም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ የሚሰጡ የቤትና የክፍል ስራዎች፣ የፕሮጀክት ስራዎችን እና የተለያዩ ፈተናዎችን ሳይኮራረጁ ራሳቸውን ችለው ይሰራሉ፣ | ሁሉም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ የሚሰጡ የቤትና የክፍል ስራዎች፣ የፕሮጀክት ስራዎችን እና የተለያዩ ፈተናዎችን ራሳቸውን ችለው በመስራታቸው መኮራረጅ ፀያፍ ድርጊት መሆኑን ሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ባህል አድርጎ ተቀብሎታል፣ |
| **ስታንዳርድ 10፡ - ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው በጎ አመለካከት አላቸው።**/2%/ | | | | |
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**በመሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ** |
| ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ በሚሰጣቸው አገልግሎት ረክተዋል። /0.5%/ | አብዛኞቹ ተማሪዎች ፣ በመምህራን አቅርቦትና ብቃት፣ በመማሪያና ማጣቀሻ መፃህፍት አቅርቦት፣ በትምህርት ቤቱ የመልካም አስተዳደር ስርአት ወዘተ እርካታ የላቸውም፣ | አብዛኞቹ ተማሪዎች ፣ በመምህራን አቅርቦትና ብቃት፣ በመማሪያና ማጣቀሻ መፃህፍት አቅርቦት፣ በትምህርት ቤቱ የመልካም አስተዳደር ስርአት ወዘተ እርካታ አላቸው፣ | ሁሉም ተማሪዎች ፣ በመምህራን አቅርቦትና ብቃት፣ በመማሪያና ማጣቀሻ መፃህፍት አቅርቦት፣ በትምህርት ቤቱ የመልካም አስተዳደር ስርአት ወዘተ እርካታ አላቸው፣ | ሁሉም ተማሪዎች ፣ በመምህራን አቅርቦትና ብቃት፣ በመማሪያና ማጣቀሻ መፃህፍት አቅርቦት፣ በትምህርት ቤቱ የመልካም አስተዳደር ስርአት ወዘተ ከፍተኛ እርካታ አላቸው፣ለአካባቢው ትምህርት ቤቶች በአርአያነት ይጠቀሳሉ፣ |
| ተማሪዎች ት/ቤቱ ለሚያከናውኗቸው ሥራዎች ድጋፍ አድርገዋል፣ /0.25%/ | ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን በጉልበት ስራ፣ በዲሲፕሊን አጠባበቅ፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት በመንከባከብ፣ ወዘተ የሚያደርጉት ድጋፍ በጣም ዝቀተኛ ነው፣ | አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን በጉልበት ስራ፣ በዲሲፕሊን አጠባበቅ፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት በመንከባከብ፣ ወዘተ ከፍተኛ ድጋፍ ያበረክታሉ፣ | ሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን በጉልበት ስራ፣ በዲሲፕሊን አጠባበቅ፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት በመንከባከብ፣ ወዘተ ከፍተኛ ድጋፍ ያበረክታሉ፣ | ሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን በጉልበት ስራ፣ በዲሲፕሊን አጠባበቅ፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት በመንከባከብ፣ ወዘተ በሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ለአካባቢው ትምህርት ቤቶች ተምሳሌት ሆነዋል፣ |
| ተማሪዎች መምህሮቻቸውን በአግባቡ መገምገም ችለዋል፣ /0.5%/ | አብኛዎቹ ተማሪዎች የሚያስተምሯ ቸውን መምህራን በትክክል አይገመግሟቸውም። | አብዛኞዎቹ ተማሪዎች የሚያስተምሯቸውን መምህራን በአግባቡ ይገመግሟቸዋል። | ሁሉም ተማሪዎች የሚያስተምሯ ቸውን መምህራን በአግባቡ ይገመግሟቸዋል። | ተማሪዎች የሚያስተምሯ ቸውን መምህራን በአግባቡ ይገመግሟቸዋል።የግምገማው ሂደት ግልፅና ወጥነት ያለው በመሆኑ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆኗል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት ይሰጣሉ፣ /0.25%/ | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት አይሠጡም። | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት ይሰጣሉ። | ሁሉም ተማሪዎች ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት ይሰጣሉ። | የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በሚያሳዩት አክብሮት ለአካባቢው ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆነዋል። |
| ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ አድርገዋል፣ /0.5%/ | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ አያደርጉም | አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ ያደርጋሉ | ሁሉም ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ ያደርጋሉ | ሁሉም ተማሪዎች የት/ቤቱን ህግና ደንቦች ተቀብለው ተግባራዊ በማድረጋቸው ለሌሎች ተምሳሌት ሆነዋል |

**ስታንዳርድ 11፡- መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደ፣ በአመቺ የትምህርት መርጃዎች የተደገፈ እና ከፍተኛ የትምህርት ውጤትን ለማስገኘት አልሞ የተዘጋጀ ነው።**/3%/

| አመልካች | ደረጃ 1<br>ደረጃውን ያላሟላ | ደረጃ 2<br>በመሻሻል ላይ ያለ | ደረጃ 3<br>ደረጃውን ያሟላ | ደረጃ 4<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ |
|---|---|---|---|---|
| የመምህራን የትምህርት እቅድ የሚያስተምሩትን ትምህርት አላማ፣ ይዘት፣የማስተማር ስነ ዘዴ፣ ወዘተ በአግባቡ አካቷል፣ /0.5%/ | የአብኛዎቹ መምህራን የትምህርት እቅድ ቢኖራውቸውም የትምህርት አላማ፣ ይዘት፣የማስተማር ስነ ዘዴውን በተጣጣመ ሁኔታ አላከተተም። | የአብኛዎቹ መምህራን የትምህርት እቅድ የትምህርት አላማ፣ ይዘት፣የማስተማር ስነ ዘዴውን በተጣጣመ ሁኔታ አካቶ ተዘጋጅቷል። | የሁሉም መምህራን የትምህርት እቅድ የትምህርት አላማ፣ ይዘት፣የማስተማር ስነ ዘዴውን በተጣጣመ ሁኔታ አካቶ ተዘጋጅቷል። | ትምህርት ቤቱ በመምህራን የትምህርት እቅድ አዘገጃጀት ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆኗል። |
| መምህራን የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ አውለዋል፣ /0.5%/ | አብዛኛዎቹ መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አያዘጋጁም | አብዛኛዎቹ መምህራን የትምህርቱን መርጃ መሳሪያዎች ቢያዘጋጁም ጥቅም ላይ አላዋሉም | ሁሉም መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ አውለዋል። | የትምህርት ቤቱ መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀትና ጥቅም ላይ በማዋል ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆነዋል |
| መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ፕላዝማ፣ቴሌቪዥን፣ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም ሰጥተዋል፣ /0.5%/ | አብዛኛው መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ፕላዝማ፣ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም አይሰጡም፣ | አብዛኛው መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ፕላዝማ፣ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም ይሰጣሉ፣ | ሁሉም መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ፕላዝማ፣ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር … ወዘተ) በመጠቀም ይሰጣሉ፣ | ሁሉም መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሬዲዮ፣ፕላዝማ፣ቴሌቪዥን፣ኮምፒውተር … ወዘተ) በመደገፍ በመስጠታቸው የተማሪዎች የመማር ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፣ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ቤተ-ሙከራ በመጠቀም ሰጥተዋል፣ /0.5%/ | አብዛኛዎቹ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዕቅዳቸው መሰረት በቤተ-ሙከራ አስደግፈው አይሰጡም | አብዛኛዎቹ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዕቅዳቸው መሰረት በቤተ-ሙከራ አስደግፈው ይሰጣሉ | ሁሉም መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዕቅዳቸው መሰረት በቤተ-ሙከራ አስደግፈው ይሰጣሉ | ሁሉም መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ በዕቅዳቸው መሰረት በቤተ-ሙከራ አስደግፈው በመስጠታቸው ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርአያ ሆነዋል |
| መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎቻቸው የአካባቢ ቁሳቁስ ተጠቅመው የፈጠራ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታታሉ፣ /0.5%/ | አብዛኛዎቹ መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎችን በአካባቢያቸው በቀላሉ የሚገኙ ቁሳቁሶችን እንዲጠቀሙ አያበረታቱም። | አብዛኛዎቹ መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን እንዲጠቀሙ ያበረታታሉ፡ | ሁሉም መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የፈጠራ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታታሉ። | ሁሉም መምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን እንዲጠቀሙ ያበረታታሉ፤ ተጨባጭ የተማሪዎች የፈጠራ ስራ ውጤቶችም ተመዝግበዋል። |
